ስለ ፍች የነበራቸው ነገረ መለኮት በዘዳግም 24÷1-4 ላይ የመተመሠረተና ትውፊትንም መከራሪያ ነጥብ ያደረገ ነበር:: ኢየሱስ ግን በተለመደው ግልጽነቱ ላይ በመመሥረት በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለወንድና ለሴት የነበረውን ዕቅድ አመለከተ:: ወንድና ሴት ይጋቡ ዘንድ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ያቀደ መሆኑን ገለጸ:: ይህም (ዘፍ 1÷27ን በመጥቀስ ሲሆን፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ቃል በቃል ነው):: የተጋቡ ጥንዶች በአካል፣ በስሜትና በመንፈስ አንድ ናቸው::

ሁለተኛ የጋብቻ ትስስር ሁለት ነገሮችን ያካትታል:: «መተውና መጣበቅ» (ዘፍ 2÷24 ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም):: ያን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ዓለም ውስጥ አባትንና እናትን መተው ማለት የግድ የተለየ ቤተ ሰብን መመሥረት ማለት አልነበረም:: ቢያንስ በአበው ዘመን ይህ ሁኔታ እንደ ብርቅ ይቈጠር ነበር:: ይልቁን «መተው» ማለት ቀዳሚ ዐደራህን (ኀላፊነትህን) መለወጥ ማለት ነው:: እናትና አባት ከእንግዲህ ከልጆቻቸው ቅድሚያ ታማኝነትን አያገኙም:: ሁለተኛው የጋብቻ ትስስር አንድ አካል መሆንን ያካትታል:: ይህ ሙሉ በሙሉ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባይሆንም፣ ስለ አካል አንድነት ከዚህ የላቀ ሥዕል የለም::[70] ስለዚህ ጋብቻ የተሣለው በሁለት ምሰሶዎች ላይ የቆመ ቃል ኪዳን ሆኖ ነው (ምሳ 2÷17):- (ሀ) ሙሉ መስጠትና (ለ) አንድ

---

70 የግብረ ሥጋ ግንኙነት ራሱን ችሎ ጋብቻን እውን አያደርግም:: ጋብቻ ቅርርብንና (በግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍጹም ይሆናል) ዐልፎ መስጠትን ይጠይቃል:: 1ቆሮ 6÷16 ከዝሙት አዳሪ ጋር የሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የላቀ አንድነት አለው ቢልም፣ ጥንዶቹ ባልና ሚስት ይሆናሉ አላለም:: ይህን ቢል ኖሮ ኢየሱስ ከውሃው ጉድጓድ ላገኛት ሴት አሁን አብራው የምትኖረው ሰው ባሏ አለመሆኑን (ዮሐ 4÷18) ሲገልጽላት አባባሉ ስሕተት በሆነ ነበር:: ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደገኛ የሚሆነውም ከዚህ የተነሣ ነው:: ጥንዶቹ አንዳቸው ለሌላቸው ዐልፈው ባልተሰጡበት ሁኔታ በሁለት ሰዎች መካከል አንድነት ይፈጠራል:: መዘዞቹ ምንጊዜም አጥፊዎች ናቸው::



አካልነት፤ ይህ ብርቱ ታማኝነት ማለት ነው:: ከእነዚህ አንዱ ሲጠፋ ጋብቻ ይፈርሳል::

በነዚህ ሁለት አምዶች ላይ መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ጥንድን «ያገናኛል»:: ኢየሱስ፣ «በአንድ ላይ መጠመድ» [ሲይኔዚይክሰን - Synezeuksen] በሚለው ሐረግ ይጠቀማል:: ስለዚህ ባልና ሚስት የዕድሜ ልክ አጋሮችና በጋራ ጥረው ግረው የሚያድሩ ይሆናሉ:: ይህ በዔደን ገነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው:: አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ሳይሆን ሰዋዊ ነው:: ይህ የእግዚአብሔር «የፍጥረት ሥርዐት» ነው:- አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ዕድሜ ልክ::

7 እነርሱም፣ «ታዲያ፣ ሙሴ አንድ ወንድ የፍቺውን የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሚስቱን እንዲያሰናብት ለምን አዘዘ?» አሉት:: **ማቴ 19÷7-8**

8 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ሙሴ የልባችሁን ጥንካሬ አይቶ ሚስቶቻችሁን እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም::»

ፈሪሳውያን በዘዳግም 24÷1-4 ትርጉም ላይ ተከራከሩ:: ጽሑፉን ግን በሚገባ አልያዙትም:: ለጀማሪዎች አንድ ወንድ ሚስቱን ይፍታ ብሎ «አላዘዘም::» ይልቁን አንድ ወንድ የፈታትን ሴት ለሁለተኛ ጊዜ እንዳያገባት ከለከለ:: ይህ በዋናነት ለሴቷ ከለላ ለመስጠት ነው:: እንዲህ የወንድ የበላይነት በነገሠበት ኅብረተ ሰብ ውስጥ ሴቶች እንደ ንብረት (ዕቃ) ይታዩ ነበር:: በመካከላቸው ጠብ በመፈጠሩ ምክንያት ወንዱ ሴቷን ወዲያውኑ እንዳያባርራት ይህ ሕግ ያግደዋል:: የሚያባርራት ከሆነ ለዘለቄታው ያባርራታል ማለት ነው:: አንድ ልጅ ወደ ላይ ያንናትን ኳስ እንደሚቀልባት መልሶ ሊቀልባት አይችልም::

ሂሌል ከሸማይ ጋር ይቃረናል በሚለው ክርክር ቀዳሚው ጥያቄ «ነውር» የሚለው ቃል ትርጉም ነው:: ቃል በቃል «ራቁትነት» ሲሆን፣ በተለይ ኀፍረተ ሥጋን ማጋለጥ (ብዙ ጊዜ ደግሞ ሴቶችን በተመለከተ ነው) ማለት ነው:: ዝሙትን ብቻ የሚመለከት አይደለም፤ ሕጉ ዝሙት ሲፈጸም የሞት ቅጣት እንዲፈጸም ያዛልና (ዘሌ 20÷10፤ ዘዳ 22÷22):: አንድ ወንድ የሞተችን ሴት አይፈታም:: አይሁድ ሰዎችን ከዝሙት ኀጢአት የተነሣ በሞት የሚቀጡት ከስንት አንድ ጊዜ ቢሆንም (በተለይ በአዲስ ኪዳን ዘመን) በተጻፈው ሕግ ውስጥ እንዲህ ያለ መንትዮሽ መለኪያ ማስቀመጡ ከሙሴ ሕግ ጋር የሚስማማ አይደለም:: በሌላ በኩል ግን «ነውር የሆነ» ማለት «አስጸያፊ» ወይም ሂሌላውያን እንደሚጠቀሙበት «መጥፎ ወጥ ሠሪ» ማለት አይደለም:: «ነውር የሆነ» ሲባል ዝሙትን ጨምሮ ልዩ ልዩ የሩካቤ ሥጋ (የወሲብ) ኀጢአትን የሚያካትት ነው:: ይህም ከዕብራይስጡ ቃል ጋርና ፓርኔያ - Pornia ከሚለው ግሪክኛ ከተተረጐመው ቃልና ኢየሱስ ከተጠቀመበት ቃል ጋር የሚስማማ ነው:: ስለዚህ የከፋ የዝሙት ኀጢአት «አንድ አካል» የሚለውን የጋብቻ ቃል ኪዳን ምሰሶ ይሰብራል::

ወደ ፈሪሳውያን ጥያቄ እንመለስ:: ሙሴ ፍች እነዲፈጸም ባያዝም፣ የሰጣቸው ደንቦች በመሠረቱ ይፈቅዳሉ:: ሙሴ ግን ፍችን መደገፉ አይደለም:: ይልቁን እየተቈጣጠረው ነው:: ሊያቆመው አልቻለም፤ ሆኖም ገደብ ሊያበጅለት ይችላል:: መመሪያ ከሌለ በተለይ ሴቶችና ልጆች፣[71] ኢየሱስ «የልባችሁን ጥንካሬ»[72] በማለት የገለጸው ሐሳብ ሰለባዎች ይሆናሉ::

[71] ምናልባት ይህ አጋጣሚ ብቻ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ፍችን በተመለከተ ይህን ትምህርት ተከትለው የመጡት ሁለት ምንባቦች በልጆችና በገንዘብ ላይ የሚያተኵሩ ናቸው:: እነዚህ ደግሞ ፍችን በተመለከተ ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው::



| | |
|---|---|
| ማቴ 19÷9<br>ከማር 10÷11 ጋር | 9«እላችኋለሁ፤ በትዳሯ ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል (በእርሷ ላይ ያመነዝራል፤ ማር)» |
| ማር 10÷12 | 12«እርሷም ባሏን ፈትታ ሌላ ብታገባ ታመነዝራለች ...።» |
| ሉቃ 16÷18 | 18«ከባሏ የተፋታችውንም ሴት የሚያገባ ያመነዝራል።» |

ይህ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በጣም አስቸጋሪ ሐሳብ ነው:: በመሆኑም ጽሑፉን ከማየታችን በፊት፣ ይህን ጽሑፍ ለማብራራት በምናደርገው ጥረት ላይ አንዳንድ መለኪያዎችን ማስቀመጥ ይኖርብናል:: በመጀመሪያ ነገር ይህ በኢየሱስና በፈሪሳውያን መካከል የሚገኝ ክርክር ነው:: ኢየሱስን ለማጥመጃነት የታለመው ጥያቄ በተለይ ሚስቱን ስለሚፈታ አንድ ባል ነው::[73] ስለዚህ በሌሎች «የክርክር» ጽሑፎች[74] ላይ እንደምናደርገው ሁሉ በዚህም ላይ ሁሉን ዐቀፍ የሆነ ሕግ ከመደንገግ መጠንቀቅ ይኖርብናል::

[72] እግዚአብሔር ፍችን የፈቀደው የሕዝቡ ደንዳና ልብ ልቅ እንዳይሄድ ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እነዚህ ሁለቱ ከመጀመሪያውኑ የእርሱ ዕቅዶች ባይሆኑም የንጉሥ አስተዳደርንና የቤተ መቅደስን መሠራት ፈቀደ::

[73] በአይሁድ ኅብረተ ሰብ ውስጥ ሴት ባሏን የምትፈታ ስለ መሆኗ ተሰምቶ አይታወቅም:: በግሪክ ወሮማን ኅብረተ ሰብ ውስጥ ግን የተለመደ ነበር:: ማርቆስ ቃሎቹን ያከለበት ምክንያት (10÷12) ለወንዱ የሚሆነው ለሴቱም ይሠራል ከማለት የተነሣ ሳይሆን አይቀርም:: ይህ ከማቴዎስ አንባቢያን ይልቅ ለማርቆስ አንባቢያን ሊሠራ የሚችል ነው::

[74] ሲ. ብሎምበርግ የተባለው ጸሐፊ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል:- በሌሎች አከራካሪ ሐሳቦች ወይም የመግለጫ ታሪኮች ላይ የተሰጡትን ዐዋጆች አንዳንዶች ቋሚ ሕጎች ለማድረግ ይጥራሉ (ለምሳሌ ከማቴ 19÷11:9-15 በተለይም ከ13÷57 ጋር ያነጻጽሩ፤ ይህም ልዩ የሆነው ሐረግ ስለሚያሳየው ማራኪ የሆነ ጉድኝት ነው)፤ ስለዚህ ማንም 19÷9ን በማለት ወይም ማር 10÷11-12ን ወደ ቋሚ ሕግ ደረጃ እንዳያሳድግ መጠንቀቅ አለበት ("Marriage, Divorce, Remarriage and Celibacy: An Exegesis of Matthew 19:3-12" *TrinJ* 11NS [1990]: 162::

ሁለተኛ ማቴዎስ ይህን በሚጽፍበት ጊዜ በደል የፈጸመ ወንድምን ይቅር ስለ ማለትና ንስሐ የማይገባን ወንድም ስለ መጋፈጥ ከተጻፈው ከ18÷18-35 ብዙ የራቀ አይደለም:: ፍች በእጅጉ የግል ጉዳይ ቢሆንም፣ በግል መፈጸም የለበትም:: ክርስቲያኖች የአንድ አካል ብልቶች ናቸው:: ስለዚህ ወደ ፍች የሚንደረደሩ ጥንዶች አንድነት ያገኙበትን የሰፊውን ክርስቲያናዊ ኅብረት ምክርና ድጋፍ የመሻት ግዴታ አለባቸው::

ሦስተኛ ጠንካራ የሆነውን ፍታቴና ነባራዊውን ትግበራ ማመዛዘን አለብን:: በምናቀርበው ሐሳብ፣ በምክንያታችንና በባህላችን ላይ ዋናው ጽሑፍ ሚዛን የሚደፋ ቢሆንም እንኳ፣ ወደ ጭቆና፣ ወደ ጠባብነትና አክራሪነት የሚመራ ገለጻ እንዳይሆን በጥርጣሬ መታየት አለበት:: ዋናውን ጽሑፍ የማብራራቱ ብቻ ሳይሆን ዳር ድንበሩን መዝነን ሥራ ላይ የማዋሉ ጉዳይም የእኛ ተግባር ነው:: ይህ ከተባለ በኋላ ጥቅሱ ቢያንስ ከሁለት ዐበይት ጥያቄዎች ጋር ያጋፍጠናል:-

**1. የትዳር ጓደኛህ ታማኝ ባትሆን ፍች ይፈጸም ዘንድ ኢየሱስ ይፈቅዳል?**

አንዳንዶች «የለም አይሰጥም!» ይላሉ:: ይህ ልዩ ሐረግ የሚገኘው ማቴዎስ 5÷32 እና 19÷9 ውስጥ ብቻ ነው:: አንዳንዶች ማርቆስና ሉቃስ ውስጥ የሌለ ልዩ ሐረግ ማቴዎስ ውስጥ አይገኝም ይላሉ:: ምክንያቱም ይህ ከሆነ የማቴዎስ አንባቢዎች ፍች ሲፈቀድላቸው፣ የሉቃስና የማርቆስ አንባቢያን ግን አይፈቀድላቸውም ማለት ነው:: ይሁን እንጂ ማርቆስና ሉቃስ አስቀድመው በጻፉላቸው ግሪካውያንና ሮማውያን ዘንድ ዝሙት ፍችን ለመፈጸም፣ በቂ ምክንያት ነው ተብሎ ባጠቃላይ ይታመን ነበር:: በዝምታም ይደረግ ነበር:: በሌላ አነጋገር፣ ማርቆስና ሉቃስ በሳይሆን አይቀርም ያለፉትን ጉዳይ ማቴዎስ በግልጽ አመለከተው::



ከዚህም በላይ ማቴዎስ 5÷32ን በትኩረት ብንመለከት ዝሙት፣ ፍችን ለመፈጸም ያበቃል አይልም:: የሚለው አንድ ወንድ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ቢፈታ፣ ዘማዊ እንድትሆን ገፋፍቷታል ነው:: በሌላ አነጋገር አንድ ጊዜ ዘማዊ ከሆነች ሌላ ነገር ልናደርጋት አንችልም:: የነገር አካሄዱ (ተጠየቁ) ለማቴዎስ 5÷32 በሚገባ ይሠራል::[75] ለማቴዎስ 19÷9 ግን አይሠራም:: ሚስቱን በመፍታት ዝሙት የሚፈጽም ሰው እንዲህ ነው::

ይህን መሠረት በማድረግ፣ አንድ «አመንዝሪ» የትዳር አጋር ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ እንድትፈታ ኢየሱስ ፈቅዷል ብለን በልበ ሙሉነት ለመናገር እንችላለን:: ይሁን እንጂ ይህ «አለመታመን» ወይም «አመንዝረኝነት» በትክክል ምንድን ነው? ማቴዎስ 5÷32 እና 19÷9 ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለው ቃል *ፖርኔያ - Porneia* የሚለው ነው:: ቢያንስ «ዝሙት» *[ሞይኮስ - moichos]*[76] ማለት ይሆናል:: ከዚህም በላይ ማለትም ሊሆን ይችላል:: ዘዳ 24÷1 ውስጥ እንደሚገኘው እንደ ብሉይ ኪዳኑ አቻው *[ፖርኔያ - ervah]* ልዩ ልዩ የወሲብ ኀጢአትን ሊያካትት ይችላል:: ይህም ወሲብ መፈጸምን፣ ነውረኛ መጋለጥን፣ ግብረ ሰዶምን፣ ለዝሙት ማባበልን፣ በቤተ ዘመድ መካከል የሚፈጸም ዝሙትን ወዘተ ሊያካትት ይችላል:: በጋብቻ ቃል

---

[75] ይሁን እንጂ፣ P.H. Wiebe, "Jesus' Divorce Exception," *JETS* 32/3 (1989): 327-333 በሚለው ጽሑፉ ውስጥ እንዲህ ይላል:- በሥነ ልሳን ደረጃ አኳያ የልዩነት ማሳያ ሐረጉ ሁለቱንም ሐረጎች ሊገልጽ ይችላል፤ ማለትም «ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ» ወይም «እንድታመነዝር ያደርጋታል» የሚለውንም ይገልጻል በማለት ያሳያል:: ስለዚህ ማቴ 5÷32 ውስጥ እንኳ ለፍች ምክንያት ፋይዳ ያለው ልዩነት ሆኖ ሊታይ ይችላል::

[76] *ፖርን - Porn* ሥረወ ቃላቱ ከወንዶች ወሲባዊ ቅሌት ይልቅ ለሴቶች ወሲባዊ ቅሌት የተለመዱ ናቸው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ዝሙትን ለመግለጽ፣ ሐሳብን በግልጽ በሚመለክተውና *ሞይኬዎን- moicheo* የሚለውን ቃል ከመጠቀም ይልቅ *ፖርኔያን - porneia* በሚለው ቃል የተጠቀመበት ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል::

ኪዳን የቆመውን «አንድነት» ለማፍረስ ግን እጅግ የከፋ ድርጊት ነገር መሆን አለበት::

ነገር ግን ወሲባዊ አለመታመን ለፍች ብቸኛው ምክንያት ነውን? አይደለም:: ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 7÷15 ውስጥ ሌላ ይጨምራል:: የማያምን የትዳ ጓደኛ ክርስቲያን ሚስትን ትቶ ቢሄድ፣ አማኝ የሆነችው ሚስት ያ ሰው ትቶ ይሄድ ዘንድ ታድርግ:: ይሁን እንጂ አንድ ክርስቲያን የትዳ ጓደኛዋ(ው) ትቶ(ታ) ቢሄድ (ብትሄድ) እርሷ(ሱ) በንጽሕና እየኖረች(ረ) ለዕርቅ መጣር ይኖርባ(በ)ታል (1ቆሮ 7÷11):: በማያምን የትዳር ጓደኛ የተተወች ሴትም ወሲባዊ ፈተና ብርቱ እስካልሆነበት ድረስ (1ቆሮ 7÷9)፣ በንጽሕና መኖር ይገባታል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል (1ቆሮ 7÷8):: ዝሙት ከመፈጸም ዳግም ጋብቻ የሚመረጥ መሆኑ ግልጽ ነው::

በማጠቃለያም ፍች ይፈጸም ዘንድ ሁለት በቂ ምክንያቶች አሉ:- (1) የጋብቻ ቃል ኪዳን የመጀመሪያ ምሰሶ፣ «አንድ አካልነት» የሚያፈርስ ወሲባዊ ኢታማኝነት ሲከሰት፣ (2) የጋብቻ ቃል ኪዳን ሁለተኛ ምሰሶ «መሰጠትን» ቃል ኪዳንን የሚያፈርስ ፍች በማያምን (በማታምን) የትዳር ጓደኛ ሲፈጸም:: ትቶ ከመሄድ ወይም ከማመንዘር ሌላ ኢየሱስ ለፍች ምክንያት ይሆናሉ የሚላቸው አጋጣሚዎች ይኖሩ ይሆን? አንዳንዶች በሙሉ ልብ «አሉ»[77] ይላሉ:: ይሁን እንጂ ከኖሩ ከጋብቻ ቃል ኪዳን ሁለት ምሰሶዎች አንዱን የሚያፈርሱና ብርቱ መሆን አለባቸው:: አንዳንዶች እንደ ድብደባ፣ ወሲባዊ ሕገ ወጥነት፣ ዕብደት፣በከዕድሜ መግፋት የሚመጣ የአእምሮ ድካም፣ የማይድን

[77] R.H. Stein, "Is It Lawful For a Man to Divorce His Wife?" *JETS* 22/2 (1979): 115-121 and M.J. Molldrem "A Hermeneutic of Pastoral Care and the Law/Gospel Paradigm Applied to the Divorce Text of Scripture," *Int* 45 (1991): 43-54.



ድካም፣ የመጠጥ ሱስ፣ የዕፅ ሱስ ወዘተ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ ብለዋል:: እዚህ ላይ መጠንቀቅ ይኖርብናል::

የኢየሱስም ሆነ የጳውሎስ ሐሳቦች ለጋብቻ ውስብስቦችና ለፍች አጋጣሚዎች ሁሉ መግትሄ ለመሆን የታለሙ አለመሆናቸው ቢታወቅም፣ እግዚአብሔር ለሚፈቅደው የፍች ወሰን መሠረቶች ናቸው:: ቅዱስ መጽሐፍ ለሚያስተምረው ታማኞች መሆን አለብን ማለት ነው:: በሌላም በኩል ይህን ትምህርት በአስተዋይነት፣ በርኅራኄና በምክንያት መተግበር አለብን:: ስለዚህ የማቴዎስን 18÷15-35 ዐውድ መሠረት በማድረግ፣ ፍች በቀላሉ እንዳይፈጸም ይህን ማስጠንቀቂያ እናቀርባለን:: በኢየሱስና በጳውሎስ ከተወሱት ሁለት ምክንያቶች ሌላ ለፍች ብዙ ፋይዳ ያላቸው ምክንያቶች ቢኖሩም እንኳ፣ ይህ የግል ውሳኔ አይደለም:: በጋብቻ የተሳሰሩ ሰዎች የጋብቻ ችግር ሲገጥማቸው ምክርና ጸሎት ይሹ ዘንድ ለአካሉ (ለቤተ ክርስቲያን) ግዴታ አለባቸው:: ጥንዶች ግጭት ሲያጋጥማቸው ችግራቸውን ማጋነናቸው አይቀርምና ልዩነታችን ዕርቅ የማይገኝለት ነው በማለት ይደመድማሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ ቅዱሳን ክርስቲያን መሪዎች ከጥንዶቹ ይልቅ የተሻለ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይችላሉ:: ፍች መላውን አካል ስለሚነካ የግል ውሳኔ ማድረጉ ትክክል አይደለም::

ፍች ምንጊዜም መጥፎ ነው (ሚል 2÷16):: የግል ውድቀትና መንፈሳዊ ሽንፈት ተደርጎ መቈጠር አለበት:: አንዳንድ ጊዜ ግን በዚህ በወደቀው ዓለም በደካማ አማራጮች ውስጥ ራሳችንን እናገኘዋለን:: ያለን ዕድል ከመልካምና ከመጥፎ አማራጮች መካከል ዝቅተኛውን መጥፎ የመምረጥ ጉዳይ ነው:: ተጋብቶ ከመኖር ይልቅ ፍች የላቀ ምክንያታዊና ጤነኛ አማራጭ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: ይሁን እንጂ ያሉንን አማራጮች በጥንቃቄ መመዘን አለብን:: ፍችንም እንደ መፍትሄ መቀበል ያለብን፣ ያሉት አማራጮች ሁሉ የማይሠሩ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው::

## 2. በፍችና በዳግም ጋብቻ በደለኛው ማን ነው?

ኢየሱስ ፍቺ ምንዝር ነው አላለም:: ፍቺ እንደ ማመንዘር ነው ነው የሚለው:: ሁለቱም የቃል ኪዳን ጋብቻን ያፈርሳሉ:: ዘይቤያዊም ንግግር ነው::[78] ኢየሱስ እንዲህ ባለ ምሳሌያዊ ንግግር ዘወትር ይጠቀም ነበር:: ለምሳሌ በተራራው ስብከት ጊዜ በፍች ጉዳይ ላይ (5÷32) ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርት ሲያቀርብ በሌሎች ዘይቤዎች አጅቦ ነበር:- ቍጣ = መግደል፤ ፍትወት = ማመንዘር፤ «ቀኝ ዐይንህ ... አውጥተህ ጣለው፤» ጨውና ብርሃን ወዘተ::

ራሷ ባላመጣችው ጥፋት ሴቷ ዘማዊት ትሆናለች (ማቴ 5÷22):: እንዴት? በኢየሱስ ዘመን አንዲት የተፈታች ሴት የነበራት ምርጫ ጥቂት ነበር:: ዕድለኛ የሆኑት እንደ ገና ያገቡ ነበር:: ያልታደሉትም ወደ ዝሙት አዳሪነት እንዲገቡ ይገደዱ ነበር:: ሁለቱም አማራጮችም «ምንዝር» ተብሎ በሚጠራው ወሲባዊ ተግባር ይካተቱ ነበር:: ሳታገባ የቀረችው ሴትስ ምን ትሆን ነበር (ምናልባት ከአንድ የቤተ ሰብ አባልን እርዳታ አግኝታ ሊሆን ይችላል)? ከፍች በፊትም ሆነ በኋላ ከሌላ ወንድ ጋር ካልተኛች፣ «ዘማዊት» ብሎ እርሷን መጥራቱ ትክክል አይሆንም:: ቢሆንም እንደ ዘማዊት ትታይ ነበር:: ዘማውያን የሚያጋጥማቸው ብቸኝነትና መገለልም ዘወትር ይደርስባታል:: ስለዚህ በብዙ መልኩ ሲታይ ወንጀሉን ባትፈጽመውም እንኳ፣ የቀድሞ ባሏ ነው ዘማዊት እንድትሆን ያስገደዳት::

ታዲያ እንዴት ነው ፍቺ እንደ ዝሙት የሚቈጠረው? ፍች በጋብቻ ውስጥ ያለውን «የመስጠት» ምሰሶ ያፈርሳል:: ዝሙት በጋብቻ ውስጥ ያለውን «አንድ አካልነት» ያፈርሳል:: በዚህም ሆነ በዚያ ጋብቻው ጉዳት ደርሶበታል:: ስለዚህ ፍችና ዝሙት ተመሳሳይ የሆነ

[78] በብሉይ ኪዳን «አመንዝራነት» ብዙ ጊዜ ከጣዖት አምልኮ ጋር በዘይቤአዊ መንገድ ጥቅም ላይ ውሎ ነበር (ሆሴ 2÷4፤ 4÷12፤ ኤፌ 5÷7፤ ሕዝ 16÷32፤ 23÷37)::



መጥፎ ውጤት አላቸው:: ዝሙት ለማይፈጽሙት ግን ስሜታቸው እንደ መራቸው ለመፍታት ፍጹም ነጻነት አለን ብለው ለሚያስቡት ጭንቀትም ፈሪሳውያን አስደንጋጭ ነገር ነው:: ከዚህም በላይ እነዚሁ ወገኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠ መብት ነው ብለው በሚያስቡት ዳግም ጋብቻ አማካይነት ዕርቅ ሊመጣ ይችላል የሚሉትን የተስፋ ጭላንጭል ያጠፋዋል:: ስለዚህ ዳግም ጋብቻ እንደ ዝሙት ያለ ነው::[79] ፍች፣ ዝሙትና ዳግም ጋብቻ ሦስቱም እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን የሚለያዩ ናቸው::

የዚህ ትርጉሙ ዳግም ጋብቻ ኀጢአት ነው የሚል ነውን? የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በሙሉ ድምፅ (በአንድ ድምፅ) «አዎን!» ኀጢአት ነው ብላለች:: ኢየሱስ ምን ብሏል? ለዕርቅ የተደረገው ሙከራ ሁሉ ሳይሳካ ቢቀር ኀጢአት ላይሆን ይችላል:: ዋና ነገር አይደለም:: የግብረ ገባዊ ውድቀት ምልክት ነው:: ያለፈውን የሕይወት አለመስተካከል ሽክም ይዟል:: ፍችን በተመለከተ ግን ጥሩ አማራጮች የሉንም:: ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ከሁለት መጥፎ ነገሮች ውስጥ በመጠኑ መጥፎ የሆነውን እንመርጥ ዘንድ እንገደዳለን:: ይህ ማለት ግን ሁለተኛ ጋብቻዎች መልካም አይሆኑም ማለት ባይሆኑም ዋና ነገር ሊሆኑም አይችሉም:: ጳውሎስ ያላገቡ ሰዎች ሁሉ ሳያገቡ ቢኖሩ ይወዳል:: ብዙዎች ብቸኝነትን ሊቋቋሙት እንደማይችሉም ያውቃል (1ቆሮ 7÷8-0):: ይህ ከሆነ ከዝሙት ዳግም ጋብቻ ይሻላል:: በተጨማሪም ልጆችን በተመለከተ ከአንድ ወላጅ ይልቅ ሁለት ወላጆች ቢኖሩ ይሻላል::

ነገር ግን ጥንዶች ዳግም ቢያገቡ በቀጣይ የዝሙት ሕይወት ውስጥ አይኖሩምን? አይኖሩም! ዳግም ጋብቻ ዝሙት አይደለም፤ እንደ

[79] ሁሉም ዝሙት ይፈጽማሉ (1) ሚስቱን የሚፈታ ወንድ (ማቴ 19÷9)፤ (2) ባሏን የምትፈታው ሴት (ማር 10÷12)፤ ባሏ የፈታት ሴት (ማቴ 5÷32)፤ (4) የተፈታችውን ሴት የሚያገባ ወንድ (ማቴ 5÷32)::

ዝሙት ያለ እንጂ:: በመጀመሪያው ጋብቻ የሬሳ ሣጥን ላይ ምስማር እንደ መምታት ነው:: «ዝሙት» የተሳሰረው ከፍች ጋር እንጂ ከሁለተኛዎቹ ጥንዶች ወሲባዊ ግንኙነት ጋር አይደለም::[80] አንዳንዶች ግን «ዝሙት ይፈጽማል» የሚለው የግሪኩ ሐረግ የአሁን ጊዜ ግስ በመሆኑ ጥንዶች በሕይወት እስካሉ ድረስ ዝሙት በመፈጸም ይኖራሉ በማለት ሐሳብ ያቀርባሉ:: ሆኖም የአሁን ጊዜን የሚያመለክተው ግሪክኛ ግስ የአማርኛው የአሁን ጊዜ ግስ ከሚለው በላይ አይልም:: አንድ ሁኔታ በቀጣይነት የሚዘልቅ ወይም የማይዘልቅ መሆኑን ሳያመለክት እንዲሁ ይገልጻል::[81] እንዲህ ያለው ሀሳብ የሚያመለክተው ሀሳብ አስከፊ ነው::

በዳግም ጋብቻ የተጣመሩ ሰዎች በቀጣይ ዝሙት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ ያለው ብቸኛ አማራጭ ሁለተኛውን ጋብቻ አፍርሶ የመጀመሪያውን ጋብቻ ዕርቅ መሻት ነው:: ይህም የሚከተለውን ማለት ሊሆን ይችላል፡- (1) በሁለተኛው ፍች በኩል ዝሙት መፈጸም፣ (2) የመጥፎ ጋብቻን የማይቻል ዕርቅ ለመሻት መልካም ጋብቻን ማፍረስ፣ (3) ሁለት ግንኙነቶችን ማወክና፣ (4) በሁለተኛው ጋብቻ የተገኙትን ልጆች መበተን::

---

[80] አንድ ሰው በጥንት ዘመን ዳግም ጋብቻ የአይሁድ ሁሉ መሠረታዊ መብት ተደርጎ ይታይ እንደ ነበር በይበልጥ ሲያስተውል (*m.Git. 9:3*) ኢየሱስ ዳግም ጋብቻን የከለከለ መሆኑን ከአድማጮቹ መካከል ማንኛውም ሰው ይገነዘብለት ዘንድ ቢፈልግ ኖሮ ይህንኑ ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ አድርጎ በሰፊው መናገር እንደ ነበረበት ይገነዘባል (C.L. Blomborg, "Marriage, Divorce, Remarriage ..." *TrinJ* 11NS [1990]: 179-180)::

[81] በግሪክኛ ቋንቋ የአሁን ጊዜ ግስ በትእዛዛዊ አንቀጽ ሁኔታን ሲያመለክት በንኡስ አንቀጽ ገብቶ የሚገኝ ከሆነ ደግሞ ቀጣይ ድርጊትን ያሳያል:: እዚህ ላይ እንዳለው አመልካች ሁኔታን የሚያሳይ ከሆነ ምንጊዜም ቀጣይ ድርጊትን ያሳያል ማለት አይደለም፤ መናገር የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ ዘዐውዱ ብቻ ነው (C.D. Osburn, "The Present Indicative of Matthew 19:9," *RestQ* 24 [1981]: 193-203)::



ከዚህም በላይ ኢየሱስ ብዙ ጋብቻዎችን ዝሙት ናቸው ብሎ ሳያወግዝ ወይም ሳያጸድቅ እውቅና ሰጥቷቸዋል (ዮሐ 4፥18):: ሙሴም እንዲህ አድርጓል (ዘዳ 24፥1-4):: እኛም ማድረግ ያለብን ይህንኑ ነው:: በተለይ በፍች ተመክሮ ውስጥ ዐልፈው ወደ ክርስቶስ በሚመጡት ዘንድ ይህ እውነት ነው (1ቆሮ 7፥17):: በመጀመሪያው ጋብቻ ላይ ዕርቅ ይወርድ ዘንድ የማይሳካ ጥረት ለማድረግ ሲባል የሁለተኛውን ጋብቻ ህልውና ማጥፋት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የሚያመራ እርምጃ አይመስልም::

**ማቴ 19፥10-12 ከማር 10፥10 ጋር**

[[10]እንደገና ወደ ቤት ከገቡ ጊዜ^ማር] [10]ደቀ መዛሙርቱም፣ «የባልና የሚስት ጉዳይ እንዲህ ከሆነ አለማግባት ይሻላል» አሉት::

[11]ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ ከተሰጣቸው በስተቀር ይህንን ትምህርት ማንም ሊቀበል አይችልም፤ [12]ምክንያቱም አንዳንዶች ጃንደረባ ሆነው ይወለዳሉ፤ ሌሎች በሰው እጅ ተሰልበው ጃንደረባ ይሆናሉ፤ ደግሞም ለመንግሥተ ሰማይ ራሳቸውን ጃንደረባ የሚያደርጉ አሉ:: ይህን መቀበል የሚችል ይቀበል::»

የጋብቻ ቅዱስነትና ከፍች በኋላ አንድ ክርስቲያን ሳያገባ ይኑር ማለቱ ብርቱ ጉዳይ ነው:: በአስተናጋጃቸው ቤት ከኢየሱስ ጋር ብቻቸውን በነበሩበት ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ጉዳይ ኢየሱስን ጠየቁት:: ምናልባት አግባብ ባልሆነ አነጋገር እንዲህ ብለውት ይሆናል፤ «ጋብቻ ይህን ያህል ከባድ ከሆነ፤ ለብቻ መኖር ይመረጣል::»

ኢየሱስም የተሰነዘረውን የነቀፋ ሐሳብ በማለሳለስ ፈንታ እንዲህ አለ፤ «ትክክል ናችሁ ሳያገቡ መቅረት የተሻለ ነው፤ ይህ ግን ለሁሉ የሚቻል አይደለም::» ጳውሎስም ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማል (1ቆሮ 7፥7-9):: በዘመናችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ለብቻው የሚኖር ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርገውን አስተዋፅኦም በሚገባ ሳይመዝኑ በምፀት ፈገግታ

«እውነት ነው፤ ይህ ግን ለእኔ አይሆንም» ይላሉ::[82] ግንኙነቶች ውብ ናቸው፤ የእግዚአብሔር ዕቅድም ናቸው:: ይሁን እንጂ ለወንጌል ሊውል የሚገባውን ብዙ ጊዜና ጉልበት ይሻማሉ (1ቆሮ 7÷32-35)::

ሳያገቡ ብቻን መኖር ግን ከእግዚአብሔር የሆነን ስጦታ ይጠይቃል:: ኢየሱስ ባስተማረው መሠረት ሦስት ዐይነት የጃንደረቦች (የስልቦች) መድቦች አሉ:: የመጀመሪያው ወሲብ የመፈጸም ተፈጥሮአዊ ችሎታ ሳይኖረው የተወለደ ሰው ነው:: ሁተኛው በቀዶ ጥገና (ለምሳሌ በመኮላሸት) የወሲብ ፈላጎቱን ያጣ ሰው ነው (ለምሳሌ ሐሥ 8:27):: ሦስተኛው ለክርስቶስ ዓላማ ሲል ላለማግባት ውሳኔ ያደረገ ሰው ነው:: በካቶሊክ ሃይማኖት ውስጥ ካህን ለመሆን፣ በድንግልና የመኖር እምነት ወይም ትምህርት በፕሮቴስታንቶችና በካቶሊኮችም መካከል ሳይቀር ጥያቄ ያስነሣ ነገር ነው (1ጢሞ 4÷1-3) በወንጌላውያን ዘንድ ግን የድንግልና ስጦታ በሚያሳዝን ሁኔታ እንደ ቀላል ነገር ተቈጥሮ ነበር::

እኩያዎቻችን የሆኑትና ያላገቡ ሰዎች እንዳልታደሉና እንደ ልዩ ሰዎች ነው የሚታዩት:: ስብራት የደረሰባቸው ይመስል «እነርሱን ለመጠገን» ከፍተኛ ሙከራዎች ተደርገዋል::[83] ወሲብን በሚያመልከውና ሚዛናዊነት በጐደለው ማግባቢያ ከመጠመድ ይልቅ፣ ሚዛናዊ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ ለመስጠት ያላገቡ ሰዎች

---

ንቷ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ጉዳይ ብርቱ ትኩረት ሰጥታ ነበር:: ሙሉ ጊዜያቸውንና ሐሳባቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማዋል ሲሉ ዕድሜ ዘመናቸውን ሳያገቡ የኖሩ አያሌ ሰዎች ነበሩ (W.A. Heth, "Unmarried 'For the Sake of the Kingdom' (Mt 19:12) in the Early Church," *GTJ* 8/1 [1987]:55-58)::

83 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተሉትን ጨምሮ ውጤታማ የሆኑ፣ ትዳር ሳይመሠርቱ የኖሩ ብዙ ሰዎችን እናገኛለን:- ኢየሱስ፣ ኤርምያስ፣ ጳውሎስ፣ ሐና ምናልባትም መጥምቁ ዮሐንስ፣ ልድያና ማርያም መግደላዊት (F. Stagg, "Biblical Perspectives on the Single Person," *RevExp* 74 [1977]: 5-19 ጋር ያነ)::



አገልግሎት የተሻለ ተግባር ያከናውናል:: ከግላዊ ወሲባዊ እርካታ ይልቅ አስፈላጊና የላቁ ነገሮች አሉ:: ጥያቄው መሆን ያለበት «የትኛው ነው ይበልጥ ደስተኛ የሚደርገኝ ሳይሆን፣ «ለክርስቶስ ይበልጥ ፍሬያማ የምሆነው ባገባ ነው ወይስ ሳላገባ?» ነው::

**§ 123**
**ኢየሱስ በመንግሥት ውስጥ ስላሉ ልጆች**
**(ማቴ 19÷13-15፤ ማር 10÷13-16፤ ሉቃ 18÷15-17**

ማቴዎስና ማርቆስ ይህን ክፍል ኢየሱስ ስለ ፍች ካስተማረው ትምህርት ጋር ያያይዙታል:: የቤተ ሰብን ቅድስና ጉልሕ አድርገው ለማሳየት ዐቅደው ይሆናል ይህን ያደረጉት:: በሌላ በኩል ሉቃስ ጸሎትን ከሚመለከቱ ጥንድ ምሳሌዎች ጋር ያያይዘዋል - ከመበለቷና ቀረጥ ሰብሳቢው:: ሁለቱም ምሳሌዎች እግዚአብሔር «የዝቅተኛ ሰዎችን» ጸሎት እንዴት እንደሚሰማ ያሳያሉ:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃናት ወደ ኢየሱስ እንዳይመጡ በመከልከላቸው ይህን ትምህርት አልተረዱትም::

**ማር 10÷13**
**ከማቴ 19÷13-15፤**
**ከሉቃ 18÷16 ጋር**

[ከዚያም[ማቴ]] 13ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው፣ ሰዎች
ሕፃናትን ወደ እርሱ ለመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን
ገሠጿቸው:: 14ኢየሱስም ይህን ሲያይ ተቆጥቶ [ሕፃናቱን
ወደ ራሱ ጠርቶ[ሉቃ]] እንዲህ አላቸው፤ «ሕፃናት ወደ
እኔ ይምጡ፤ አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔርን
መንግሥት [መንግሥተ ሰማይ[ማቴ]] እንደ እነዚህ ላሉት
ናትና::
15እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበል ሁሉ ከቶ
አይገባባትም:: «ሕፃናቱንም አቀፋቸው፤ እጁንም ጭኖ ባረካቸው [ከዚያ ስፍራ
ተነሥቶ ሄደ[ማቴ]]::

የኢየሱስን ጊዜ የሚያጣብበው ሕዝብ ብዛት ቊጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ ሄደ (ከማቴ 19÷2፤ ከማር 10÷1 ጋር ያነ)::

ኢየሱስ ልብ እንዲላቸውና እንዲዳስሳቸው ከሚሻሙ ሰዎች መካከል ልጆቻቸውን የያዙ ሴቶች ይገኙ ነበር::[84]

የደቀ መዛሙርቱ ክልከላ ምክንያቶች ምናልባት በጎ ሳይሆኑ አልቀሩም:: ኢየሱስ በአገልግሎቱ ዕንቅፋት እንዳይገጥመው፣ የወትዋች እናቶች ጥያቄ እንዳያስቸግረውና ውር ውር የሚሉ ልጆች እንዳይቀርቡት ፈልገው ይሆናል:: በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወቅት ጥቂት የማይባሉ ልጆችን ይዞ የሚንከባከብ አገልጋይ የደቀ መዛሙርቱን ችግር ሊረዳ ይችላል:: ልጆች ከቦታ ቦታ በመሯሯጥና በመጯጯህ በአቅራቢያቸው ያለን ሰው ሐሳብ ይሰርቃሉ:: በሚወደድ ሁኔታቸው ይህን ያደርጋሉ:: ኢየሱስ በነበረበት ስፍራም የነበሩ ልጆችም በዕድሜ የበሰሉ ሰዎች የኢየሱስን ትምህርት እንዳያዳምጡ ዕንቅፋት በመሆን ላይ ነበሩ::

አይሁዳውያን የሆኑ ልጆች ጭምቶችና ታዛዦች እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፤ በዕድሜ የበሰሉ እስከሚሆኑ ድረስም እንደ አገልጋይ ይታዩ ነበር (ከገላ 4፥1-2 ጋር ያነ):: ይህ ቢሆንም ተወዳጅ የአይሁድ ኅብረተ ሰብ አባላት ነበሩ:: ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ታዋቂ ሰዎች በመውሰድ፣ እነዚሁ ሰዎች እጆቻቸውን በራሳቸው ላይ ጭነው እንዲጸልዩላቸው ማስደረጉ እንግዳ ነገር አልነበረም:: ደቀ መዛሙርቱ ይህን በተሻለ ሁኔታ ማወቅ ሲገባቸው ሕጻናቱን ገሠጿቸው:: ኢየሱስ ቀደም ሲል ገሊላ ውስጥ ልጆች የመንግሥት ዜጎች ውብ ምሳሌዎች መሆናቸውን ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮዋቸዋል (ከክፍል 90

---

[84] ማቴዎስና ማርቆስ ሁለቱም ቀደም ሲል የኢያኢሮስን የዐሥራ ሁለት ዓመት ሴት ልጅ ለመግለጫነት በዋለውና ፓይዲያ - *paidia* በሚለው ቃል ይጠቀማሉ፡ ሉቃስ ግን ብሬፌ - *brephe* (ቍ 15) የሚለውን ቃል ተጠቅሟል (ሉቃ 2፥12:16፤ ሐሥ 7፥19፤ 2ጢሞ 3፥15፤ 1ጴጥ 2፥2)፤ በማሕፀን ያለን ሽልም ለመግለጫነት ውሏል (ሉቃ 1፥41:44):: ስለዚህ የኢየሱስ ጥሪ የልጆችን ሰፋ ያለ የዕድሜ ክልል ያካትታል::



ማብራሪያ፤ ከማቴ 18፥1-5፤ ከማር 9፥33-37፤ ከሉቃ 9፥46-48 ጋር ያነ)::[85]

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን ድርጊት ባየ ጊዜ ተቈጣ፤ «ክእርሱ ዘወር እንዲሉም» ነገራቸው [ሜ ክለዩቴ - me kloyete][86] ይህ ብዙ ጊዜ የሚከሠት ነገር አይደለም:: ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ባነጻ ጊዜ በሊቃነ ካህናቱ ላይ ተቈጥቶ እንደ ነበር ኢርቱዕ በሆነ መልክ ሁለት ጊዜ ተገልጾአል (ዮሐ 2፥14-17፤ ማቴ 21፥12-13፤ ማር 11፥15-17፤ ሉቃ 19፥45-46)፤ ኢየሱስ ተቈጥቶ እንደ ነበር በግልጽ የተነገረው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን ይኸውም በሰንበት ዕለት እጁ የሰለለችበትን ሰው በፈወሰ ጊዜ ነው (ማር 3፥5):: የተቈጣው ፈሪሳውያን ከዚህ ምስኪን

---

[85] የኒለኞቹ የይሁዳና የዮርዳኖስ ማዶ የኢየሱስ አገልግሎቶች እንደ ገሊላው አገልግሎቱ ተመሳሳይ ቃላትና ጉዳዮችን ያካትታል:: አንዳንዶቹ ተመሳሳይነቶች የሚከተሉት ናቸው:- (1) 72ቱንና (ሉቃ 10፥1-16) 12ቱን (ማቴ 10) መላክ:: (2) ምሳሌ የሆነ ጸሎት (ሉቃ 11፥1-4:9-12 እና ማቴ 6፥9-13፤ 7፥7-11):: (3) ብዔል ዜቡልና መንፈስ ቅዱስን መሳደብ (ሉቃ 11፥14-36 እና ማቴ 12፥22-37፤ ማር 3፥20-30):: (4) በምግብ ወቅት ከፈሪሳውያን ጋር የተደረገ ግጭት (ሉቃ 11፥37-54፤ 14፥1-24 እና ማቴ 15፥1-20፤ ማር 7፥1-23):: (5) ለደቀ መዝሙርነት የቀረበ ማስጠንቀቂያ (ሉቃ 12፥1-12፤ 14፥25-35፤ 17፥1-10 እና ማቴ 10፥18-33:37-38፤ 18፥6-7:21-22):: (6) ስለ ገንዘብ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች (ሉቃ 12፥22-34 እና ማቴ 6፥19-34:: (7) ከቤተ ሰብ አስበልጦ ለኢየሱስ ስለ መገዛት የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች (ሉቃ 12፥49-53 እና ማቴ 10፥34-36):: (8) ጊዜውን ስለ መገንዘብ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች (ሉቃ 12፥54-59 እና ማቴ 16፥2-3፤ 5፥25-36):: (9) በሰንበት ስለ ተደረገው ፈውስ የተነሣ ውዝግብ (ሉቃ 13፥10-21፤ 14፥1-24 እና ማቴ 12፥1-14፤ ማር 2፥23-3፥6፤ ሉቃ 6፥1-11):: (10) ምሳሌዎችን በቀጣይነት ስለ መጠቀም (ሉቃ 15-16፤ 18፥1-14 እና ማቴ 13፤ ማር 4፤ ሉቃ 8):: (11) አንድን ሰው ከሞት ማስነሣት (ሉቃ 7፥11-17፤ 8፥40-56፤ማቴ 9፥18-26፤ ማር 5፥21-43፤ እና ዮሐ 11፥17-44)::

[86] ይኸው የግሪክኛ ዐረፍተ ነገር አመሠራረት በጥምቀት ዐውድ ውስጥም ጥቅም ላይ ውሎአል (ማቴ 3፥14፤ ሐሥ 8፥36፤ 10፥47፤ 11፥17):: ይሁን እንጂ ትስስሩ ነገረ መለኮታዊ ሳይሆን፣ አጋጣሚያዊ (ሁኔታዊ) ነው:: በሌላ አባባል ይህ ጥቅስ ስለ ሕፃናት ጥምቀት ሐሳብ ለመሰንዘር ወይም ለማስተማር አልታለመም::

ሰው ችግር ይልቅ ለሃይማኖታቸው ሥርዐት ቅድሚያ በመስጠታቸው ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ የተቈጣው በምናውቃቸው በሦስት ቡድኖች ላይ ብቻ ነበር:- በፈሪሳውያን፣ በሰዱቃውያንና በደቀ መዛሙርቱ:: «ኀጢአተኞች» የአያሌ «ክርስቲያናዊ» መራራ ጥላቻ ዒላማ መሆናቸው ታዲያ እንዴት የሚገርም ነገር ነው::[87]

ርኅራኄ ከሞላበት ከዚህ ትዕይንት የላቀ ነገር ሊኖር አይችልም:: ኢየሱስ ሕፃናትን ጠራ፤ ታቀፋቸውም:: ለመንግሥቱ ዜጎች ምሳሌ የሆኑት በቀላሉ የሚታለሉና ደካሞች በመሆናቸው አይደለም፤ ምክንያቱ፣ (ሀ) ትሑታን በመሆናቸው፤ (ለ) ማዕረግ ወይም ሹመት ፈላጊዎች ባመሆናቸው፤ (ሐ) እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በቀላሉ በመገንዘባቸው ነው::

ትዕይንቱ ዕጥር ምጥን ያለ ነው፤ ኢየሱስ መንዝ አለበት፤ በፋሲካ በዓል ላይ መገኘት ይኖርበታል::

**§ 124ሀ**
***ሀብታሙ ወጣት አለቃ***
***(ማቴ 19÷16-30፤ ማር 10÷17-31፤ ሉቃ 18÷18-30***

ይህ ታሪክ ቀላል ነው:: አንድ ዝነኛ ባለሀብት (የንግድ ሰው) ኢየሱስን ለመከተል ተነሣስቷል:: ሆኖም ራሱን ከገንዘቡ ጋር ማላቀቁ አልሆነለትም:: ስለዚህ ሀብቱን ወደ ኢየሱስን ሳይከተል ቀረ:: ለአሁኗ ቤተ ክርስቲያን በጣም አሳዛኝ የሚሆኑ ታሪኮች ጥቂት ናቸው:: ለዚህ ነው ነገሩን በቀጥታ መግለጥ የሚኖርብን:: «ወዳጄ ይህ ታሪክ ለባለጸጎች ብርቱ ነው» እንላለን:: እኛን ይመለከታል ብለን አናስብም:: ልብ በሉ «ሀብታም» የሚባሉት ሰዎች እኛ ከያዝነው ከፍ ያለ ሀብት ያላቸው ናቸው::

[87] የኢየሱስ ስሜት የእግዚአብሔርን ቅደም ተከተል ገለጠው:: ውስጣዊ ስሜቶች ሰዋዊ ድክመቶች አይደሉም፤ የግንኙነታችን አካሎች ናቸው እንጂ:: ድካማችን የሚመጣው ውስጣዊ ስሜቶቻችንን ለመቈጣጠር ካለመቻላችን ወይም ወደ ተገቢ ሰዎችና ሁኔታዎች ለመመለስ ካለመቻላችን የተነሣ ነው (W. Hanser, "The Emotions of Jesus," *CT* [Feb 3, 1997]: 43-46 ጋር ያነ)::



ወይም «ኢየሱስ ሀብት ያለው ሁሉ ሀብቱን እንዲተው አይጠይቅም፤ ሀብታቸውን እንዲተዉ የሚጠይቀው በሀብታቸው ላይ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ብቻ ነው» እንላለን:: ኢየሱስን ስንከተል ገንዘብ የቱን ያህል መሰናክል እንደሚሆንብን አንገነዘብም::

***ማር 10÷17-18***
***ከማቴ 19÷16፤***
***ከሉቃ 18÷18 ጋር***

[17]ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀምር፣ አንድ ሰው [ከ... አለቆች አንዱ[ሉቃ]] ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም በጉልበቱ ተንበርክኮ «ቸር መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ [ምን መልካም ነገር[ማቴ]] ይገባኛል» አለው::

[18]ኢየሱስም «ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ምንም የለም ...» አለው::

ኢየሱስ በዮርዳኖስ ማዶ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ እንደገና ከአንድ ሰው ጥያቄ ገጠመውና ቆመ:: ይህ ጠያቂ ወጣትና ተዋካቢ ነው:: ኢየሱስ ከባረካቸው ሕፃናት ጋር ተነጻጻሪነት አለው (ማቴ 19÷13-15፤ ማር 10÷13-16፤ ሉቃ 18÷15-17):: ወጣት ቢሆንም እንኳ ምናልባት (20-24) በሀብት በኩል ተሳክቶለታል (ሉቃ 18÷23)::[88] በማኅበረ ሰቡ ውስጥም የተከበረ አለቃ ነው ይህ የሆነው በምኩራቡ በኩል ሳይሆን አይቀርም (ሉቃ 18÷18)፤ የታፈረ (ማር 10÷17)፤ ሃይማኖተኛና (ማር 10÷20) ለትምህርት ልቡን ያቀና ሰው ነው (ሉቃ 18÷18):: የተዋጣለት «ዕጩ» ሰው ይመስላል::

[88] ማቴዎስና ማርቆስ ብዙ ንብረት ነበረው ቢሉም እንኳ *[ክተማታ ፖላ - Ktemata Polla]*፣ የተባለው ጸሐፊ ግን እንዲህ ሲል ባለጸጋ የነበረ ነው ማለቱ አይደለም:: ሉቃስ ግን ለላይኛው መደብ ኅብረተ ሰብ ብቻ የሚያገለግለውን [*ፕላውስዮስ ስፎድራ - plousios sphodra*] የሚል ሐረግ ተጠቀመ::

ይህ ወጣት ለማጥመድ ዓላማቸው (ማቴ 19÷3፤ ማር 10÷2) የኢየሱስን ጉዞ በጥያቄ እንደ ገቱት ፈሪሳውያን አይደለም:: ቅን ይመስላል:: እንዲያውም እኮ በአቀራረቡ (ተንበርክኮ)፣ በክብሬታ አጠራሩ («ቸር መምህር»)፣ በሐቀኝነቱ («ከዚህ ሌላ የሚጎድለኝ ምን አለ?») ወደ ኢየሱስ የመወጣው በታላቅ አክብሮት ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ «ወደደው» (ማር 10÷21):: ከዚህም በላይ ጥያቄው ጥሩ ብቻ ሳይሆን እጅግ ውብ ነው:- «የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል?» የሚል::

ኢየሱስ ጥያቄውን ከመመለሱ በፊት ሁለት አስፈላጊ ጉዳዮችን ግልጽ ማድረግ ነበረበት:- 1ኛ ኢየሱስ ማን ነው? 2ኛ እንዴት ነው የምንድነው? ስለ እነዚህ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ግንዛቤ ከሌለው፣ ኢየሱስ ለጥያቄው የሰጠውን መልስ በሚገባ አይረዳም::

**ርእስ ጉዳይ ቁጥር 1:- ኢየሱስ ማን ነው?** ወጣቱ ኢየሱስን የጠራው «ቸር መምህር»[89] በማለት ነው:: ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ እንዲያስተውል «ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር የለም» በማለት ኢየሱስ አስገነዘበው:: ይህን ሲል ቸር አይደለሁም ማለቱ አይደለም:: ከዚያ ይልቅ የእግዚአብሔር ቸርነት ኢየሱስ የሚጋራ የመሆኑን

---

[89] D.A. Carson የተባለው ጸሐፊ በሰፊው እንዳብራራው፣ በማቴዎስ አገላለጽና በማርቆስ አገላለጽ መከከል ግምት ውስጥ የሚገቡ ልዩነቶች አሉ:: ("Redaction Criticism: On the Legitimacy and Illegitimacy of a Literary Tool," In *Scripture and Truth,* ed D.A. Carson and J.D. Woodbridge [Grand Rapids: Zondervan, 1983], 131-137):: በእነዚህ ልዩነቶች ላይ ማብራሪያ አይሰጥም:: ምክንያቱም፣ (1) የዚህ ሥራ ዓላማ ምጡቅ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሒስ ቴክኒካዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል ለማሳየት አይደለም፤ (2) የንባቡን ምንነት በጉልሕ መልኩ አይለውጡም፤ (3) ሁለቱ አገላለጾች እርስ በርስ የሚጣረሱ አለመሆናቸውን በማመልከት፣ የማርቆስን አገላለጽ አስመልክቶ ማቴዎስ በቊ 17 ላይ ሐሳብ ሰንዝሮአል፤ J.W. Wenham, "Why Do You Ask Me About the Good? A Study of the Relation Between Text and Source Criticism," *NTS* 28 (1982): 116-125, «ቸር መምህር ሆይ፤ ምን መልካም ነገር ልሥራ» የሚለው በማቴዎስ የመጀመሪያ ጽሑፍ አንድ ጉዳይ ይዞ ይገኛል::



እውነት እንዲያስተውል ሲያሳስበው ነው:: በዚህ መሠረትና ይህንኑም በመገንዘብ ብቻ ነበር ይህ ወጣት ላቀረበው ጥያቄ የሚሰጠውን መልስ ሊሰማ የሚችለው::

ይህ ቸርነት ከግብረ ገባዊ ፍጹምነት ይልቅ (2ቆሮ 5፡21፤ ዕብ 4፡15)፣ ከኢየሱስ እውነትን የማስተማር ችሎታ ጋር ግንኙነት አለው:: በሌላ አነጋገር እርሱ መልካም መምህር ነው፤ ምክንያቱም ትክክል የሆኑ መልሶች ሁሉ የእርሱ ናቸው:: ሆኖም የእውነት ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ ምንጊዜም እውነትን የሚናገር ከሆነ የእግዚአብሔር ተወካይ ሆኖ እውነትን ይናገራል (ዮሐ 8÷28፤ 12፡49-50):: ስለዚህ ይህ ወጣት በደንብ ለመስማት መዘጋጀት ይኖርበታል::

[«ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ» አለው:: ሰውየውም፣ «የትኞቹን ትእዛዛት» ሲል ጠየቀ:: ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ማቴ]
[19]ትእዛዛትን ታውቃለህ፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ አታታልል፤ አባትህንና እናትህን አክብር፤ [ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ::ማቴ]

ማር 10÷19-20 ከማቴ 19÷17-20 ጋር

[20]ሰውየውም [ጕልማሳውም] «መምህር ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ» አለው:: [ከዚህ ሌላ የሚጐድለኝ ምን አለ፧ማቴ]

*[ማር 10:]19 ዘፀአት 20÷12-16፤ ዘዳ 5÷16-20 [ማቴ 19:]19 ዘሌ 19÷18*

**ርእስ ጉዳይ ቁጥር 2:- እንዴት ነው ድነት ያገኘነው?** አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚያገኘው በራሱ መልካም ጠባይ ነው ብለው አይሁድ ሙሉ በሙሉ አምነው ነበር (ዘዳ 30፡15-16):: ስለዚህ ኢየሱስ «ትእዛዛቱን ጠብቅ» በማለት የተለመደውን አይሁዳዊ መልስ በመጀመሪያ ሰጠ:: ከአምስተኛው ጀምሮም እስከ ዐሥረኛው ያሉትን

ትእዛዛት ዘረዘረ (ዘፀ 20፥16፤ ዘዳ 5፥16-20)።[90] ከዚያም ማቴዎስ በሚገባ ተገንዝቦ እንዳሰፈረው፣ ኢየሱስ ከዘሌዋውያን 19፥18 ጋር በማያያዝ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለውን ቃል ጨምሮ ሙሉውን ዝርዝር አጠቃለለው፤ (ከማቴ 22፥34-40 ጋር ያነ)።

እነዚህ የመጨረሻ ስድስት ትእዛዛት የአንድን ሰው የጉንዮሽ ግንኙነት (ይኸውም ሰው ከሰው ጋር) ይመለከታሉ። ይህ ሀብታምና ወጣት ገዥ ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ነቀፋ የለበትም (ቍ 20)። እንዲያ ማለት ግን ፍጹም ኀጢአት አልባ ነው ማለት አይደለም (ሮሜ 3፥23)። ነገር ግን ከልብ የሆነ ንስሐ እና በቤተ መቅደስ የሚቀርብ መሥዋዕት በየጊዜው የሚከሠቱትን መተላለፎች ያስተካክላሉ። ሃይማኖቱን በእጅጉ የሚጠብቅ በመሆኑ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር «ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ ከሆነም ያለ ነቀፋ ነበርሁ» (ፊል 3፥6) ለማለት ይችላል።

የውጫዊው ጽድቁ ነቀፋ አልባ ቢሆንም እንኳ ልቡና ሐሳቡ (አእምሮው) ትክክል አይደሉም። አንድ ነገር ይጎድለዋል፤ እርሱም ዐውቆታል። በጥልቅ መንፈሱ ውስጥ እነዚህ የኢየሱስ ቃሎች ይሰሙታል፤ «ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ መምህራን ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ መንግሥተ ሰማይ መግባት አትችሉም» (ማቴ 5፥20)። ስለዚህ «እንዴት ነው ድነት የምናገኘው?» ለሚለው ጥያቄ ኢየሱስ የተለመደውን አይሁዳዊ መልስ በሰጠው ጊዜ፣ «ልክ ነው፤ ልክ ነው፤ ይህንማ ከዚህ ቀደምም ሰምቸዋሁ፤ ግን ለእኔ እውን አልሆነልኝም፤ የጐደለኝ ምንድ ነው?» አለ። ይህ ወጣት ከዚህ ቀደም ያከናወናቸው

[90] ማርቆስ «አታታልል» ሲል የዐሥረኛው ትእዛዝ ማለትም «አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ በተግባር ሲገለጽ ነው በማለት ዐስቦ ይሆናል።



በጎ ተግባሮች የዘላለም ሕይወት[91] እንዳላስገኙለት ቢያውቅም፣ ሌላ የማያውቀው ነገር ስለሌለ ሕግ ፈጻሚነቱን የሙጥኝ አለ።

ማር 10፥21-22
ከማቴ 19፥21፤
ከሉቃ 18፥22
ጋር

[ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ[ሉቃ]] [21]ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤ እንግዲያው አንድ ነገር ይጐድልሃል [«ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ[ማቴ]]፤ ሂድና ያለህን ሁሉ ሸጥ፤ ለድኾችም ስጥ፤ በሰማይ የተከማቸ ሀብት ታገኛለህ፤ ከዚያ በኋላ ና፤ ተከተለኝም» አለው። [22]ሰውየው ይህን ሲሰማ ከፋኛ አዘነ፤ ብዙ ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ።

ይህ ወጣት በመጀመሪያ ገንዘቡን ሁሉ ትቶ ደቀ መዝሙሩ ይሆን ዘንድ ኢየሱስ ጠራው። አንድ ሰው ካለው ሀብት ከመቶ ሃያ ይበልጥ እንዳይሰጥ ከሚከለክሉት አይሁዳውያን አንጻር ሲታይ ይህ በተለይ እንግዳ የሆነ ግዴታ ነው። ደቀ መዝሙር ሁሉ ኢየሱስን በእምነት እንዲከተል ጥሪ ቀርቦለታል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በእኛና በኢየሱስ መካከል መሰናክሎች አሉ። ስለዚህ ከእነዚህ መሰናክሎች ራሳችንን ነጻ ካላደረግን፣ ልንከተለው አንችልም። ለዚህ ወጣት መሰናክሉ ገንዘብ ነበር። ለሌሎች መሰናክሉ ሥራ፣ ዝና ወይም ራስ ወዳድነት ሊሆን ይችላል። የእኛ መሰናክል የተለየ በመሆኑ ግዴታችን ለስለስ ያለ (ሙሉ በሙሉ ያልሆነ) ወይም ሥር ነቀል ያልሆነ ሊሆን አይችልም (ገላ 2፥20፤ ማቴ 10፥37-39፤ ፊል 3፥7-11)።

በሉቃስ ትረካ ውስጥ በተከታታይነት የቀረቡት ሁለት ታሪኮች እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድኾች ይሰጥ ዘንድ

[91] ድነትን ለመግለጽ ይህ ጽሑፍ ሦስት አባባሎችን መጠቀሙ አስፈላጊ ሳይሆን አልቀረም፦ 'የዘላለም ሕይወት'፣ 'ወደ መንግሥቱ መግባት' እና 'ዳነ'። ቢያንስ የዘላለም ሕይወት የአሁን ገጽታ እንዳለው ያሳያል። ለዘላለም ይዘልቃል፤ ነገር ግን አሁን ይጀምራል።

አለመጠራቱን ያሳያሉ። ዘኬዎስ ካለው ሀብት ግማሹን ሰጠ (19፥1-10)። በምሳሌው ውስጥ ታማኝ አገልጋዮች ደግሞ ለጌታቸው ብለው ገንዘባቸውን በብልኀት እንዲሠሩበት ተጠርተዋል። ይሁን እንጂ በሁሉም ሁኔታዎች እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ያለው አተያይ ግልጽ ነው። ሁሉ የእርሱ ነው። እኛ የእርሱን ሀብት ለራሱ ዓላማ የምናውል መጋቢዎች ነን። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ የሥጋ አምሮትን ለማሟላት በሚጣደፍ ኅብረተ ሰብ ውስጥ የምትገኝ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ማከማቸትን ትታ እርሱን ትከተል ዘንድ የኢየሱስን ጥሪ መስማት ይኖርባታል። ይህ ምንባብ እኛን የሚመለከት መሆኑን የምናስበው እጅግ አነስተኛ በሆነ መልኩ ነው (ያዕ 2፥14-17፤ 1ዮሐ 3፥17)።

አንድ ሰው ሕግን እየጠበቀ ሌላ ነገር የሙጥኝ ብሎ ላይዝ ይችላል (ገንዘብን፣ ወሲብን፣ ሥልጣንን)። ወደ ኢየሱስ ስንመጣ ግን የምንወዳቸውን ሌሎች ነገሮች ሁሉ እንተዋለን። ይህ ሰው ከኢየሱስ ጋር ከሚኖረው ግንኙነትና ለገንዘቡ ባለው ፍቅር መካከል ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለበት፤ «አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም» (ማቴ 6፥24)። ለድኾች ቸርነት ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ዋናው ነገር ይህ አይደለም፤ ለኢየሱስ መገዛት ነው። ሰውዬው ገንዘቡ በመንገዱ ላይ ደንቃራ ሆኖበት ቆሞአል። ኢየሱስ ከገንዘቡ እንዲላቀቅ ጠየቀው።

አልሆነለትም፣ እያዘነ ሄደ። ሉቃስ፣ «በሐዘን ተከበ» የሚለውን ሐረግ ቃል በቃል ይጠቀማል። ማቴዎስ «እያዘነ» [ላይፔዎ - lypeo] ይላል። ያዘነው ድነቱን በማጣቱ አይደለም። እርግጥ ነው በአእምሮው ገንዘብን ከዘላለም ሕይወት አብልጦ አልወደደም። ይልቁንስ ያዘነው



ጥያቄው ሳይመለስ በመቅረቱ ነው። ገንዘቡን እንደ ያዘ ድነት የሚያገኝበትን መንገድ አሁንም በመፈለግ ላይ ነው።

ድነት ከመሲሑ ጋር ግላዊ ግንኙነት በማድረግ የሚገኝ መሆኑን ከመረዳት ይልቅ፣ የጽድቅ ሽልማት አድርጎ በተሣሣተ መንገድ ተረዳው። ድነት የሽልማት ሥርዐት ተደርጎ የሚታይ ከሆነ፣ አንድ ሰው ሀብት ወይም ሥልጣን የማያገኝበትና ብሎም ድነትን የማያተርፍበት ምክንያት የለም። ድነት ከኢየሱስ ጋር ያለ ግንኙነት ተደርጎ የሚታይ ከሆነ፣ እንግዲያው ጊዜህንና ትኩረትህን ለማን መስጠት እንደሚኖርብህ ምርጫ ማድረግ አለብህ። ለገንዘብ ወይም ለጌታ።

**ማር 10፥23-27**
**ከማቴ 19፥23:25፤**
**ከሉቃ 18፥24 ጋር**

23 ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት (ሰውየውን ተመልክቶ[ሉቃ]) ደቀ መዛሙርቱን፣ «ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት (መንግሥተ ሰማይ[ማቴ]) መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው!» አላቸው።

24 (ይህን ሲሰሙ[ማቴ]) ደቀ መዛሙርቱም በንግግሩ ተገረሙ፤ ኢየሱስ ግን እንደ ገና መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ልጆች ሆይ፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው፤ 25 ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀለዋል።»

26 ደቀ መዛሙርቱም ይበልጥ በመገረም፣ «ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?» ተባባሉ።

27 ኢየሱስም አያቸውና፣ «ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል» አላቸው።

*[ማ]24 አንዳንድ ቅጆች በሀብት ለሚታኑ የሚል ሐረግ አላቸው።*

ኢየሱስ ይህ ሰው አቀርቅሮ ሲሄድ እየተመለከተ ደቀ መዛሙርቱን፣ «ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው!» አላቸው:: ይህን ዐይነቱን ንግግር ለደምደነዋል:: የኢየሱስ አይሁዳዊ አድማጮች ግን ተገረሙ:: እንግዲህ አስተውሉ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ድጋፍ አድርገው ሀብት ከእግዚአብሔር የመጣ በረከት ነው እያሉ አምነው ነበር:: እግዚአብሔር ስለ ወደዳቸው ሀብታሞች ከሰዎች ሁሉ ይልቅ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ብቁዎች ናቸው ብለው ያምኑ ነበር:: እንዲህ የሚያምኑ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት የማያገኙ ከሆነ፣ ታዲያ «የምስኪኖች» ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነው?

ሕዝቡ ግራ ተጋብተዋል:: ኢየሱስ እንቆቅልሻቸውን በመፍታት ፈንታ፣ ሀብታሞች ወደ መንግሥተ ሰማይ ከሚገቡ ይልቅ ግመል[92] በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል በማለት ይበልጥ ግራ አጋባቸው:: ይህ እንደማይቻል የታወቀ ነው! ግመል[93] በፓለስቲና ምድር እጅግ ግዙፍ የሆነ እንስሳ ነበር:: የመርፌ ቀዳዳ[94] ደግሞ በማንኛውም ሰው ዘንድ አገልግሎት ላይ የሚውል እጅግ አነስተኛ ቀዳዳ ነበር::

አንዳንድ የዘመኑ አስጎብኚዎች ኢየሩሳሌም ውስጥ «የመርፌ ቀዳዳ ነው» በማለት የቅጥሩ በር ነው የተባለውን መተላለፊያ ያሳዩዋቸዋል:: ግመል ራሱን አጩናንቆ እንዲያውም ተንበርክኮ በበሩ ሊያልፍ ስለሚችል ኢየሱስ ያመለከተው ይህን መተላለፊያ ነው ብሎ ማመልከቱ የተለመደ ነው:: ይህን ትርጓሜ የሚደግፍ ማስረጃ

---

[92] በአራማይክ ቋንቋ «ግመል» [ጋማል - *gamal*] ገሚሉዝ - *gemiluth* የሚለው ቃል ሌልኛ አገላለጽ ሲሆን ሀብታሞች ችላ ያሉት «የቸርነት ሥራ» መሆኑን J.D.M. Derrett ("A Camel through the Eye of a Needle" *NTS* 32 [1986] 465-70) ላይ አመልክቶአል::

[93] ባቢሎን ውስጥ ዝሆን በአገሪቱ ውስጥ ግዙፍ እንስሳ በመሆኑ፣ ይህ አባባል ዝሆን በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ ቢያልፍ ይቀላል ተብሎ ተለውጦአል::

[94] ማቴዎስና ማርቆስ የማይጠቀሙበትን ሉቃስ የቀዶ ጥገና መርፌ መጠሪያ የሆነውን ልዩ ቃል ይጠቀማል::



ካለመኖሩም በላይ፣ ዘይቤውን ዋጋ ቢስ ያደርገዋል:: ዋናው ሐሳብ ሀብታም ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት አስቸጋሪ ይሆንበታል ሳይሆን አይቻልም የሚል ነው::[95]

የኢየሱስ አድማጮች ደንግጠዋል:: ጥያቄያቸው የታወቀ ነው፤ «ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?» ኢየሱስ ዋናውን ሐሳብ ያላገኘው ሊመስል ይችላል፤ እንዲያውም የጉዳዩን እምብርት አግኝቶታል:: ሀብታሙ ወጣት አለቃ፣ «የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል?» በማለት ጠየቀ:: ኢየሱስም፣ የቱንም ያህል በጎ ነገር መሥራት፣ የዘላለምን ሕይወት አያስገኝም በማለት መለሰ:: የቱንም ያህል ሕግን መጠበቅ «ክፍተትን አይሞላም» (ማቴ 19÷20):: በእኛና በኢየሱስ መካከል የቆመውን መሰናክል ሁሉ ማስወገድ አለብን፤ ብሎም እርሱን ብቻና ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርን ማመን ይገባናል:: ድነት የእምነት አፀፋ በመስጠት የምንቀበለው (ማር 10÷21) የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ ነው (ማር 10÷27)::

28ጴጥሮስ፣ «እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ» አለው:: **ማር 10÷28**

28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ:: **ማቴ 19÷28**

---

[95] የኋለኞቹ አንዳንድ ቅጆች በ«ግመል» ምትክ «ገመድ»ን ይተካሉ:: ይህ የአይቻሌነትን ባሕርይ እንደ ያዘ ሆኖ ዘይቤውን ዘይቤ ያደርገዋል፤ ይሁን እንጂ የቅጅ ድጋፍ ደካማ በመሆኑ ጉሉሩን የማይመስል ያደርገዋል::

**ማር 10፥29-31**
**ከሉቃ 18፥29 ጋር**

29እስ እኔና ስለ ወንጌል (ስእግዚአብሔር
መንግሥት[ሉቃ]) ቤቱን (ወይም ሚስቱን[ሉቃ]) ወይም
ወንድሞቹን ወይም እኅቶቹን ወይም እናቱን ወይም
አባቱን ወይም ልጆቹን ወይም ዕርሻውን የተወ ሁሉ፤ 30አሁን በዚህ ዘመን ከስደት
ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና ዕርሻን መቶ ዕጥፍ
የማይቀበል፣ በሚመጣውም ዓለም የዘለዓለም ሕይወት የማይወርስ የለም። 31ነገር
ግን ብዙ ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፣ ኋለኞች የሆኑም ፊተኞች ይሆናሉ።»

ጴጥሮስ ጮሌ ነው! ወደ ራሱም ማሰላሰል ጀመረ፤ «ድነት የሚገኘው ይህን ዓለም ሙሉ በሙሉ በመተውና ኢየሱስን ለመከተል ሙሉ በሙሉ በመስጠት ነው፤ እኔ ደግሞ ይህንኑ ፈጽሜአለሁ!» ስለዚህ ዐሥራ ሁለቱን በመወከል የታወቀውን ጉዳይ ለኢየሱስ አመለከተ። አነሣሽ ምክንያቱ ራስ ወዳድነት ሳያጠላበት አልቀረም። አእምሮውም ወደ ሕግ አክራሪነት ያደላበት ይመስላል፤ ይሁን እንጂ የነገር አካሄዱ (ተጠየቁ) ይበጅ የሚሰኝ ነው። ኢየሱስ የማያወላውልና ተገቢ መልስ ሰጠው። የሐዋርያቱ ዋጋ (ሽልማት) አራት ዕጥፍ ይሆናል። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ከአራቱ ጥቅሞች ውስጥ የቀሩትን ሦስቱን ጥቅሞች ይካፈላሉ፦

በመጀመሪያ ሐዋርያቱ በዐሥራ ሁለቱ ዙፋኖች ላይ ተቀምጠው በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ላይ ይፈርዳሉ (ማቴ 19፥28፤ ከሉቃ 22፥28-30 ጋር ያነ)። ይኸውም ኢየሱስ ሲመለስና ፍርድ ሲጀመር ዐሥራ ሁለቱ የይሁዳ ነገዶች በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፊት ለፍርድ ይቀርባሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ ክርስቲያኖች በቀረው ዓለም ላይና በመላእክት ላይ እንኳ ሳይቀር ለመፍረድ ያግዛሉ (1ቆሮ 6፥2-3)። ኢየሱስ ይህን ጉዳይ «የነገሮች ሁሉ መታደስ» ይለዋል (ከኢሳ 34፥4፤ 51፥6፤ 65፥17፤ ከዳን 7፥9፥9:14:18:27፤ ከ2ጴጥ 3፥10-13፤ ከራእ 21-22 ጋር ያነ)። በመጨረሻ በዔደን ገነት ወደ ተጀመረው ወደ እግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅድ እንመለሳለን።



በዚህ በአሁኑ ሕይወት እውን የሚሆነውን ሁለተኛ ሽልማት (ማር 10፥30)፣ እንተወው ዘንድ የተጠየቅነው ነገር ሁሉ ብዜት ነው (ቤትን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ ልጆችንና ዕርሻን) የማርቆስ ዝርዝር ጠቃሚ ጉዳይ ነው። «ቤት» ሲባል ሁለቱን ማለት ሰዎችንና ሀብት (መሬትን) ያካትታል። ሰዎቹ የተዘረዘሩት በሚሰጡት ፋይዳ ቅደም ተከተል መሠረት ነው፦ መንትዮች፣ ወላጆች፣ ልጆች። በመሆኑም ኢየሱስ ለእኛ ውድ የሆኑትን ሰዎችና ልዩ ልዩ ሀብታችንን እንተው ዘንድ እየጠየቀን ነው። ማቴዎስና ማርቆስ ሽልማቱ የተተወው ነገር ሁሉ በመቶ ሲባዛ የሚያስገኘው ውጤት ይህ ነው በማለት በግልጽ ያመለክታሉ። ይህም 10000% ወለድ ማለት ነው። ይህ ተስፋ ቃል በቃል የሚፈጸመው፣ ቤተ ክርስቲያን ሀብቷን ከክርስቶስ አካል ጋር በምትካፈልበት ጊዜ ነው።


ሦስተኛ ከዚህ ታላቅ ሀብት ጋር ስደት ይመጣል (ማር 10፥30)። ከክርስቶስ ጋር ሲወገን የሚሆን ነገር ነው (ዮሐ 15፥18-25)። በመጨረሻም በምድራዊ ሕይወት ካለው ስደት ባሻገር የዘላለም ሕይወት ተስፋ አለ። ይህም በምድር የምንቀበለውን መከራ ሁሉ ምንም እንዳልሆነ ያደርገዋል (ሮሜ 8፥18)።

**§ 124ለ**
**ምሳሌ፦ ፊተኛው ኋለኛ ይሆናል፤ ኋለኛው ፊተኛ ይሆናል**
**(ማቴ 20፥1-16)**

በመጽሐፍ ቅዱሶቻችን አዲስ ምዕራፍ የሚጀምሩት እዚህ ላይ መሆኑ እንደ ዕድል የሚቈጠር ነገር አይደለም። ይህ ምሳሌ ቀደም ያለው ሐሳብ ቀጣይ ነው። በማቴዎስ 19፥30 እና 20፥16ን ስናነብ ይህ ግልጽ ይሆናል፤ «ነገር ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች ብዙ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።» መጽሐፈ ምሳሌ «ሲያበቃ» ይህ ሐረግ ያገለግላል።

በዚህ ሁኔታ ነው ይህ ምሳሌ ፊተኞች ኋለኞች፣ ኋለኞችም ፊተኞች የሚሆኑበትን መንገድ አጒልቶ የሚያሳየው:: በዐውዱ ረገድ ሲታይ ግን የደቀ መዝሙርነት ዋጋ ምን መሆኑን ጴጥሮስ ላቀረበው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠውንም መልስ ያጠቃልለዋል:: ሀብታሙ ሰው ኢየሱስን፣ «የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል» በማለት ጠየቀው:: ኢየሱስም ትእዛዛትን ከመፈጸም ጋር ያለውን ሁሉ ትቶ እንዲከተለው ነገረው:: ይህ ሀብታም አለቃ እያዘነ ኢየሱስን ትቶት ሄደ፤ ጴጥሮስ ግን፤ «ጌታ ሆይ፤ እኛ ይህን ፈጽመናል፤ ታዲያ የምናገኘው ምንድን ነው?» በማለት ጠየቀ:: ኢየሱስ የሚያስደንቅ ዝርዝር ነው ለጥያቄው ያቀረበው መልስ:: ደቀ መዝሙርነት ጥቅሞች አሉት:: የታሪኩ መጨረሻ ግን ይህ አይደለም:: ድነት በእምነት እውን የሚሆን ጸጋ ነው:: አለዚያ ጴጥሮስ እነዚህን ሁሉ በጥረቴ አገኝቻቸዋለሁ ብሎ ሊያስብ ይችላል:: በመሆኑም በክርስቶስ ያገኘነው ሁሉ በጥረታችን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ቸር ለጋሽነት መሆኑን ለማስገንዘብ ጌታ እንዲህ አለ:-

**ማቴ 20፥1-7**



1«መንግሥተ ሰማያ ለወይኑ ቦታ ሠራተኞችን
ለመቅጠር ማልዶ የወጣን የአትክልት ስፍራ ባለቤት
ትመስላለች:: 2በቀን አንዳንድ ዲናር ሊከፍላቸው
ከተስማሙ በኋላ ሠራተኞቹን በወይኑ ቦታ
አሰማራቸው::
3ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመውጣት ሥራ ፈትተው በገበያ ቦታ የቆሙትን
ሌሎች ሰዎች አገኘ፣ 4'እናንተም ሄዳችሁ በወይኔ ቦታ ሥሩ፤ ተገቢውን ክፍያ
እሰጣችኋለሁ' አላቸው፤ 5እነርሱም ሄዱ::
«ከቀኑ በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት ላይ ወጥቶ ሌሎች የቀን
ሠራተኞችን ቀጠረ:: 6ከሰዓት በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ወጥቶ ቆመው



የነበሩ ሌሎች ሰዎች አገኘና፣ 'ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ እዚህ ለምን ትቆማላችሁ?'
በማለት ጠየቃቸው:: 7«እነርሱም፣ 'የሚቀጥረን ሰው ስለ አጣን ነው' አሉት::
እርሱም፣ 'እናንተም ሄዳችሁ በወይኔ ቦታ ሥሩ' አላቸው::

በመኸር ወቅት አንድ ገበሬ መኸሩ ማሳ ላይ እንዳለ ከመበላሸቱ በፊት መኸሩን ወደ ጎተራ ለማስገባት ረዳት መቅጠር አለበት:: አስደሳች ደግሞም አስጨናቂ ጊዜ ነው:: ኢየሱስ በፖለስቲና አገር በጊዜው ተዘዋዋሪ ሠራተኞች የሚቀጥራቸውን ለመጠበቅ ወደሚበሰቡበት የገበያ ስፍራ ሄደ::

ታሪካችን የሚነሣው ሥራ በሚጀመርበት የፀሐይ መውጫ ጊዜ በገበያ ስፍራ ነው:: የተወሰኑ ሰዎችን ቀጥሮ በዕለቱ ወይን እንዲሰበስቡለት ወደ ወይን ዕርሻው[96] የሚልካቸውን ገበሬ እዚያው እናገኘዋለን:: የዕለቱ ዋጋ በቀን፣ ለዐሥራ ሁለት የሥራ ሰዓት አንድ ዲናር ነበር::[97] ባለቤቱ ለእነዚህ ቅጥር ሠራተኞች ለመክፈል ቃል የገባውም ይህንኑ ነው:: የዕለቱ ሥራ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሲታይ ወይኑ የታሰበውን ያህል በፍጥነት አልተሰበሰበም:: ስለዚህ ገበሬው ተጨማሪ ሠራተኞችን ለመቅጠር ወደ ገበያ ሥፍራ ተመለሰ:: ሠራተኞቹ ሥራ የሚጀምሩት ዘግይተው ቢሆንም «ተመጣጣኝ ዋጋ» እንጂ አንድ ዲናር እከፍላችኋለሁ ብሎ ቃል አልገባላቸውም:: በዚህ ዐይነት ቀኑን ሙሉ ሠራተኞችን ሲቀጥር ዋለ:- በእኩለ ቀን፣ በዘጠኝ ሰዓት፣ እና የዕለቱ የሥራ ሰዓት ከማለቁ በፊት በዐሥራ አንድ ሰዓትም ቀጠረ:: ይህ ግልፅ የሆነ ግነት ነው፤ ቢሆንም ቊልጭ ያለ ምስል ይሥላል::

---

[96] የወይን ቦታ እስራኤልን የሚወክልና ዘወትር የሚቀርብ ምሳሌ ነበር (በተለይ ኢሳ 5፥1-7)::

[97] የወታደር ደመወዝ፣ ለደመወዝ ደረጃ የተቀመጠለት ይመስላል:: ያኔ ወታደሮች በቀን አንድ ዲናር ይከፈላቸው ነበር (Tobit 5:14; Tacitus, *Annales*, 1.17; Pliny 33:3)::

*ማቴ 20፥8-16*

8«በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ባለቤት
የሠራተኞቹን ተቆጣጣሪ፣ 'ኋላ ከመጡት ጀምረህ
መጀመሪያ እስከመጡት ድረስ ያሉትን ሠራተኞች በሙሉ
ጥራና ደመወዛቸውን ክፈላቸው' አለው።
9«በዐሥራ አንደኛው ሰዓት ገደማ የተቀጠሩት ሠራተኞች ቀርበው፣
እያንዳንዳቸው አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። 10በመጀመሪያ የተቀጠሩት ሲቀርቡ ብልጫ
ያለው ክፍያ የሚያገኙ መስሎአቸው ነበር፤ ነገር ግን እነርሱም አንዳንድ ዲናር
ተከፈላቸው። 11ክፍያውን ሲቀበሉ በባለቤቱ ላይ በማጉረምረም፣ 12'እነዚህ በመጨረሻ
የተቀጠሩት አንድ ሰዓት ብቻ ሲሠሩ፣ ቀኑን ሙሉ በሥራ ስንደክምና በፀሐይ
ስንንቃቃ ከዋልነው ጋር እንዴት እኩል ትከፍለናለህ?' አሉት።
13«እርሱም አንደኛውን ሠራተኛ እንዲህ አለው፤ 'ወዳጄ ሆይ፤ በደል
አላደረስሁብህም፤ በአንድ ዲናር ለመሥራት ከእኔ ጋር ተስማምተህ አልነበረምን?
14በል ድርሻህን ይዘህ ሂድ፤ ለአንተ የሰጠሁትን ያህል በመጨረሻ ለመጣው ሰው
መስጠት እፈልጋለሁ። 15ታዲያ በራሴ ገንዘብ የፈለግሁትን ማድረግ አልችልምን? ወይስ
ቸር በመሆኔ ምቀኝነት ያዝህን?'
16«ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።»

በዚያ ዘመን ሠራተኞች የሚከፈላቸው በእያንዳንዱ የሥራ ቀን መጨረሻ ላይ ነበር (ከዘሌ 19፥13 ጋር ያነ)። ገንዘባቸውን ለመቀበል ሁሉም ተሰለፉ። በሰልፉ ላይ በመጀመሪያ የተሰለፉት በመጨረሻ የተቀጠሩት ሰዎች ናቸው። የገበሬው አሠሪ ገንዘቡን መክፈል ጀመረ። ጀምበር ስትወጣ የተቀጠሩት ሠራተኞች ሁሉ ምን ያህል እንደሚከፈላቸው አያውቁም ነበር፤ በእርግጥም ከአንድ ዲናር ያነሰ ይከፈለናል ብለው አስበው ነበር። አንድ ሰዓት ብቻ የሠሩ ሰዎች የሠሩበት አንድ ሰዓት በዐሥራ ሁለት ተሰልቶ የሙሉ ቀን ክፍያ ሲሰጣቸው ምን ያህል ይደነግጡ!



ይህ ሁሉንም አስገርሞአል። ምን ያህል ሊከፈላቸው እንደሚቻል ማሰላት ጀመሩ። ለመቀበል እጃቸውን ሲዘረጉ ግን አሠሪው አንድ ዲናር ብቻ ነው የሰጣቸው። ፀሐይ ስትወጣ ጀምሮ ሲሠሩ የነበሩት ተስፋ መቍረጥ ብቻ ሳይሆን ተቈጡ። በልጅነታቸው ሲያስሙት እንደ ነበረው ዐይነት የገደል ማሚቶ፣ «ልክ አይደለም» አሉ። ገበሬው እነርሱ ካሳዩት ቍጣ በሚመጥን መልኩ እንዲህ በማለት መለሰ፤ «ትክክል ናችሁ፤ ተመጣኝ አይደለም ... ቸርነት ነው። ይህ ደግሞ የእኔ ጉዳይ እንጂ እናንተን አያገባችሁም!»[98]

በተመሣሣይ መንገድ፣ «ብዙ ፊተኞች ኋለኞች፣ ብዙ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ» (19፥30)። በአሁኑ ጊዜ ይህን ተስፋ የምናገኘው በውልብታ መልኩ ብቻ ነው። ኢየሱስ ሲመለስ ግን የሰው ይዞታ ሁሉ ይገለባበጣል። በዚህ ዓለም ላይ ከላይ ያሉት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከታች ይሆኑ ዘንድ የክብር ምልክት የሆነው ምስሶ ይገለበጣል።[99]

ዓለማችን ውበትን፣ ሀብትንና ሥልጣንን ያከብራል። የተለየ ክብካቤ ለመቀበል በግንባር መሥመር ላይ የሚሰለፉት እነዚህ ባለ ሀብቶች ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር እምነትን፣ ውርደትንና እንደ ሕፃን ገር መሆንን ይወዳል። ስለዚህ ያ መንግሥት ሲመጣ ከአሁኖቹ «ክቡራን» ይልቅ የማይታሰቡት ዕጩዎች ተመጣጣኝ ወይም የላቀ ክብካቤ ያገኛሉ። ድኾች ሀብታሞች ይሆናሉ፤ የተጨቈኑት ነጻ ይወጣሉ፤ ሕፃናት ይከብራሉ፤ አካል ጉዳተኞች ይፈወሳሉ፤ ያልተማሩት እንዲያውቁ ይደረጋሉ። ነገር ግን አሁንና እዚህ ባለብንበት ወቅት እንደ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንነታችን በተቻለ መጠን

---

98 «ወዳጅ ሆይ፤ [*ሄታሬ - hetaire*] የሚለው አነጋገር የፍቅር መግለጫ አይደለም (ከማቴ 11፥16፤ 22፥12፤ 26፥50 ጋር ያነ)፤ «ጓደኛ!» ብለን ከምንጠራበት ቃል ጋር ጉድኝት አለው።

99 «ብዙ» የሚለው ቃል የማያወላውል ነው ማለት ስላልሆነ በእግዚአብሔር መንግሥት የሁሉም ማዕረግ (ሚና) ይገለባበጣል ማለት አይደለም።

የእግዚአብሔር የሆነውን መተግበር የእኛ ድርሻ ነው:: እርግጥ ነው ሁሉን ለማከናወን አንችልም:: ሆኖም ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ሃዴቱን ይፈጽመዋል::

### § 125ሀ
### ስለ ኢየሱስ ሕማማት ሦስተኛ ትንቢት
### (ማቴ 20፥17-19፤ ማር 10፥32-34፤ ሉቃ 18፥31-34)

[ማር 10፥32]ወደ ኢየሩሳሌም በመውጣት በመንገድ ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ተገረሙ፤ ሌሎች የተከተሉት ደግሞ ፈርተው ነበር:: ደግሞም ዐሥራ ሁለቱን (ደቀ መዛሙርት[ማቴ]) ከሕዝቡ ለይቶ ምን እንደሚደርስበት ነገራቸው፤ [33]እንዲህ አላቸው፤ «ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን! (ነቢያት ስለ ሰው ልጅ የጻፉትም ሁሉ ይፈጸማል[ሉቃ])፤ የሰው ልጅ ለካህናት አለቆችና ለጸሐፍት አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም የሞት ፍርድ ይፈርዱበታል፤ አሳልፈው ለአሕዛብ ይሰጡታል፤ [34]ያፌዙበታል (ያንገላቱታል[ሉቃ])፤ ይተፉበታል፤ ይገርፉታል፤ ከዚያም ይገድሉታል (እንዲሰቅሉት)፤ እርሱ ግን ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል::»

ሉቃ 18፥34

[34]ደቀ መዛሙርቱ ግን ከዚህ ሁሉ የተረዱት አንድም ነገር አልነበረም፤ አባባሉም ተሰውሮባቸው ነበር፤ ስለ ምን እንደ ተናገረም አላወቁም::

ይህ ሥዕላዊ ትዕይንት ነው:: ከፈሪሳውያን (19፥3)፣ ከደቀ መዛርቱና (19፥13) ከሀብታሙ ወጣት አለቃ ጋር (19፥16) ግጭት አነሣሽ ሁኔታዎች ከገጠሙት በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ በመንገድ ላይ ነበር:: የመጨረሻ መዳረሻው ወደ ሆነው ዋና ከተማ በበቀል መንፈስ የሚራመድ ይመስላል:: ቡድኑን በታላቅ እርምጃ እየመራ ከፊት ከፊት ይሄዳል:: ደቀ መዛሙርቱም በመገረም በቅርብ ርቀት ይከተሉታል:: ለእርሱ ያልተገዙት ሕዝብ ግን ፍርሃትን አንግበው በርቀት ይከተሉታል:: በአእምሮአቸው ምን ይመላለስ እንደ ነበር ከቶ ልናውቅ አንችልም:: እነዚህ ወቅቶችና እንቅስቃሴዎች የቱን ያህል ብርቱዎች መሆናቸውን የሚያመለክቱና የሚጮኹ ነገሮች



በኢየሱስ አረማመድና ቊርጠኝነት ይታይ ነበር:: ይህች ቅድስት ከተማ ለእነዚህ ሰዎች የምትወክለው ነገር ምንም ሆነ ምን ለኢየሱስ ግን የመሞቻ ሥፍራ ናት::

ዳግም ብቻቸውን ሊያስተምራቸው ዐሥራ ሁለቱን ለብቻ ወሰዳቸው (ከ16፥21 እና ከ17፥22-23 ጋር ያነ):: ከሕዝቡ ካራቃቸው በኋላ፣ ያ ሁኔታ ሁሉ ምን ማለት መሆኑን ለታማኞቹ ገለጸላቸው:: ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በጨረፍታ ሲያመለክታቸው ቢቆይም፣ ስለ ሞቱ በቅድሚያ ሲነግራቸው ይህ ሦስተኛ ጊዜው ነው (ከክፍል 83፣ 86፣ 88 ጋር ያነ):: የአሕዛብን ልዩ ተሳትፎና በምን ዐይነት ሞት ማለት በስቅላት እንደሚሞት በመግለጹ ይሄኛው ትንቢት ከሁለቱ ለየት ያለ ነው::

በመሠረቱ በዚህ ትንቢት ውስጥ ስድስት ዋና ዋና ነገሮች ይገኛሉ፦

1. ኢየሩሳሌም ውስጥ መፈጸም አለበት፤
2. ሰዎች ይከዱታል፤
3. ሊቃነ ካህናቱና የሃይማኖት ሕግ መምህራን (ይኸውም የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን አለቆች (መሪዎች) ለሞቱ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፤
4. ሞት ይፈረድበት ዘንድ ለአሕዛብ ዐልፎ ይሰጣል፤
5. ያላግጡበታል (ይሰድቡታል፤ የተፉበታልም)፤ ይገርፉታል፤ ይሰቅሉታልም፤
6. በሦስተኛው ቀን ይነሣል::[100]

[100] ማቴዎስና ሉቃስ የትንሣኤን ሦስት ቀን በተመለከተ ኢ-ተሻጋሪ አመልካች የሆነውን «በ»ን መጠቀማቸውን፣ ማርቆስ ግን «በኋላ» [ሜታ - meta] የሚለውን መስተዋድድ መጠቀሙን ልብ ይበሉ:: ይህም ኢየሱስ ስለሆነው የጊዜና የሁኔታ ቅደም ተከተል ሙሉ በሙሉ አለመናገሩን ያስገነዝባል::

ብዙዎች የዚህን ታሪክ ሐቀኝነት ተጠራጥረዋል:: አስቀድሞ በግልጽ የተነገረ ጉዳይ ነውና ኢየሱስ ከሞተ በኋላ የእርሱ ታሪክ ነው ተብሎና ተጽፎ እንዲረጋገጥ አድርገዋል:: ኢየሱስ እንዳለው ሆኖ ከተገኘ፣ የወንጌል ጸሐፊዎች እንደ ተናገሩትም የፈጸመ ከሆነ፣ ትንቢት ለኢየሱስ ይህን ያህል አስደናቂ ተአምር አይደለም:: እንግዲህ ዋና ጉዳይ እንዲህ የሚል ይሆናል:- ኢየሱስ ተራ ሰው ነበርን? ወይስ ሕይወቱ የእግዚአብሔር ተወካይ (መልእክተኛ) መሆኑን ያሳያል?

ሉቃስ ለዚህ ታሪክ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን አስተዋፅኦዎችን ያቀርባል:: በመጀመሪያ ነቢያት ሞቱን መተንበያቸውን ለደቀ መዛሙርቱ ያስታውሳቸዋል (ቍ. 31):: መዝሙር 16÷10፤ 118÷22፤ ዘፍጥረት 3÷15ን ጨምሮ ኢሳይያስ 53 እና መዝሙር 22 ወደ ትውስታው መጥተው መሆን አለበት:: ደግሞም በሁለተኛው የሕማማት ትንቢት እንዳደረገው ሁሉ (ሉቃ 9÷45) አላዋቂነታቸውን አጉልቶ አሳይቷል: ይህ ጉዳይ ከእነርሱ ተሰውሮ ነበር:: [ክርይፕቶ - krypto] የሚለው ቃል እግዚአብሔር ያን ጉዳይ ከሐዋርያቱ ሰውሮት እንደ ነበር ያስገነዝባል እንጂ የማይገባቸው ፈዛዛዎች ነበሩ ማለቱ አይደለም::

**§ 125ለ**
**ያዕቆብና ዮሐንስ የክብር ስፍራን ጠየቁ**
**(ማቴ 20÷20-28፤ ማር 10÷35-45፤ ከሉቃ 22÷24-27 ጋር ያነ)**

ያዕቆብና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር የክብር ስፍራ ይኖራቸው ዘንድ በጠየቁ ጊዜ፣ ሐዋርያት ባይሆኑ ኖሮ፣ ራስ ወዳድ ቂሎች ልንላቸው እንቃጣ ነበር:: ሥቃይ ወዳለበት የሞት ፍርድ እየሄዱ ወደ «ምረቃ ድግስ» የሚጓዙ መሰላቸው::

ማር10፥35 ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ወደ እርሱ ቀርበው (በመንበርከክ)፣ «መምህር ሆይ፤ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን» አሉት::

36 እርሱም፣ «ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?» አላቸው::

37 እነርሱም፣ «በክብርህ ጊዜ (በመንግሥትህ[ማቴ]) አንዳችን በቀኝህ፣ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድልን (ፍቀድ[ማቴ])» አሉት::



ማቴዎስ በጻፈው መሠረት ይህን ጥያቄ ያቀረበችው የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ሰሎሜ ነበረች (ማቴ 27÷55-56 ከማቴ 15÷40 ጋር):: በኢየሱስ ዘንድ ተሰሚነት አላት ብለው በመገመት ሁለቱ ልጆቿ ሳይገፋፏት አልቀሩም:: ሰሎሜ የኢየሱስ አክስት የነበረች ሳትሆን አትቀርም (ከዮሐ 19÷25 ጋር ያነ)፤ ሴት እንደ መሆኗ መጠንም ከእነርሱ ይልቅ የርኅራኄ ልብ ልታገኝ ትችል ነበር:: በተጨማሪም ጥያቄው ከእናታቸው የሚመጣ ከሆነ የራስ ወዳድነት ሀሜታን ይቀንሳል:: ኢየሱስ ግን ዕቅዳቸውን አስተውሎ ነበርና ያዕቆብንና ዮሐንስን በቀጥታ ተናገራቸው::[101]

ጥያቄያቸው ገደብ የሌለው ነው:- «የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን፤» ይላል:: በመጠኑም ቢሆን ጥያቄያቸው ከመሥመር የወጣ መሆኑን የተረዱ ይመስላሉ:: እንዲያውም እኮ ኢየሱስ ማዕረግንና ሹመትን ስለ መፈለግ ጉዳይ ቀደም ሲል ለዐሥራ ሁለቱ ትምህርት ሰጥቶአል (ክፍል 90):: እንደ ሕፃናት የመሆንንና (ክፍል 123) ሊመጣ ስላለው ሞቱ (ክፍል 125 ሀ) ደጋግሞ ተናገረ:: እንደ ተለመደው አልሰሙትም:: ይልቁንም ዐልፎ እስከሚሰጥበት ሌሊት ድረስ እንኳ ሳይቀር ማን እጅግ የከበረ ሰው እንደ ሆነ በመጠየቅና በመከራከር ይቀጥላሉ (ሉቃ 22÷24-27)::

---

101 ማቴዎስ 20÷22 ውስጥ ኢየሱስ ሁለተኛ መደብ ብዙ ቍጥርን፣ «የምትለምኑትን» (እናንተ) የሚለውን መጠቀሙን ያመለክታል:: ይህም በቀጥታ ለያዕቆብና ለዮሐንስ እንደ ተናገረ ወይም ለሰሎሜ መልስ ሲመልስ እነርሱንም እንዳከላቸው ያመለክታል::

ኢየሱስ የራስ ወዳድነት ጥያቄያቸውን አያስተናግድም:: «የምትፈልጉት ምንድን ነው?» በማለት ጠየቃቸው:: «በመንግሥት ውስጥ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን መቀመጫ እንፈልጋለን» በማለት መለሱ:: በዚህ ጊዜ በአሥጊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ወደ ኢየሩሴም ቀርበዋል:: ለኢየሱስ ኢየሩሳሌም አደጋን ያዘለች ከተማ ናት:: እርሱ ግን እንደ ታምረኛው ሰው (Superman) ከተደጋጋሚ ጥይት ያመልጣል:: የአይሁድ ሤራ፣ የባሕር ማዕበል ወይም የአጋንንት ኀይል አላሸነፉትም:: ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ሲደርስ መንግሥቱን ይመሠርታል የሚለውን የሕዝብ ተስፋ ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ይጋሩታል:: ስለዚህ ያዕቆብና ዮሐንስ ሌሎቹን ለማስወገድ እና በሚመጣው መሲሓዊ መንግሥት ከፍተኛውን የአስተዳደር ኀላፊነት ለመጨበጥ ፈለጉ:: ለምን አያገኙም? ለኢየሱስ በጣም ቅርብ ከሆኑት ሦስት ደቀ መዛሙርት መካከል እነርሱ አብላጫ ድምፅ አላቸው!

ማር 10÷38-40
ከማቴ 20÷23 ጋር

[38]ኢየሱስም፣ «የምትለምኑትን አታውቁም፤
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ የምጠመቀውንስ
ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?» አላቸው
[39]እነርሱም፣ «አዎን እንችላለን» አሉት::
ኢየሱስም፣ «እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ፤ እኔ የምጠመቀውን
ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤ [40]ነገር ግን በቀኜ ወይም በግራዬ መቀመጥ ለተዘጋጀላቸው
(አባቴ ላዘጋጀላቸው[ማቴ]) የሚሆን እንጂ እኔ የምሰጠው ነገር አይደለም» አላቸው::

ሥቃይን የሚወክሉ ሁለት ዘይቤዎችን በመጠቀም ኢየሱስ ዐይናቸውን ለመግለጥ ሞከረ:- ጥምቀት (ማቴ 3÷11-12) እና ጽዋ (መዝ 75÷8፤ ኢሳ 51÷17፤ ኤር 25÷15-28):: ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱት ድልን ለማክበር ሳይሆን ሥቃይን ለመቀበል ነው:: ያዕቆብና ዮሐንስ የኢየሱስ የቅርብ ሰዎች ተብለው እንዲታወቁ ይፈልጋሉ::



በዚህ ጊዜ ያ ሁኔታ ሹመት ሳይሆን ስደት ነው:: ባለማስተዋልና በሙሉ ልብ የኢየሱስን የማይቀር መከራ እንጋራለን አሉ::

ርግጥ ነው ሁለቱም በስደት እሳት ይጠመቃሉ:: ያዕቆብ የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ሰማዕት ይሆናል (ሐሥ 12÷2):: ዮሐንስ ደግሞ በሕይወት የሚቆይ የመጨረሻ ሐዋርያ ይሆናል:: በአፈ ታሪክ መሠረት የሰማዕት ሞት ያልሞተ እርሱ ብቻ ነው:: በሕይወት ቢኖርም እንኳ፣ ከሥቃይ ያመለጠ ሰው አልነበረም:: በመጨረሻ የሕይወት ዘመኑ ራእይን ባየበት ፍጥሞ ደሴት ውስጥ ተግዞ ነበር (1÷1)::

ኢየሱስ ሊሰጣቸው የሚችለው ተስፋ ሹመትን ሳይሆን ስደትን ነው:: ሹመት መስጠት የአባቱ ሥልጣን ብቻ ነው:: ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ሥልጣንን ሁሉ የሚቀበል ቢሆንም (ማቴ 28÷18)፣ በአገልግሎቱ ዘመን ግን ለአባቱ በመገዛት ይኖር ነበር (ዮሐ 14÷28):: ይህ ብቻ ሳይሆን ለኀጢአተኛው የሰው ዘር ቁዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ራሱን አስገዛ:: አገልጋይ ሆኖ መጣ፤ ደቀ መዛሙርቱንም ከፍ ላለ ማዕረግ አልጠራቸውም::

ማር 10÷41-45
ከማቴ 20÷28
ከሉቃ 22÷26
ጋር

[41]ዐሥሩ ይህን ሲሰሙ፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን
መቈጣት ጀመሩ:: [42]ኢየሱስም በአንድነት ሰብስቦ
እንዲህ አላቸው፤ «የአሕዛብ አለቆች ተብለው
የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው፣ ሹማምቻቸውም በእነርሱ ላይ
ሥልጣናቸውን እንደሚሠሩ ታውቃላችሁ፤ [43]በእናንተ
ዘንድ ግን እንዲህ
አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ (እንደ ታናሽ[ሉቃ])
ይሁን:: [44]ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ [45]የሰው ልጅ
ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል
አልመጣምና::»

ለመገመት እንደሚቻለው ዐሥሩ ተቈጡባቸው፤ የተቈጡት የኢየሱስን ትምህርት በትክክል ባለመተርጐማቸው ሳይሆን ብልጣ ብልጥ ስለሆኑባቸው ነው:: ዐሥራ ሁሉተም እነዚህን ዋና ዋና መቀመጫዎች ይፈልጓቸዋል:: እርሱ ሲያገለግል ቢያዩም፣ ሲሰብክ ማስታወሻ ቢይዙም፣ ሦስት ዓመት ሙሉ አብረውት ቢመላለሱም እንኳን፣ የአገልግሎቱን መሠረታዊ ዓላማና መንገድ (ዘዴ) ማለት የሰው ዘር አገልጋይ ሆኖ መምጣቱን አልተረዱም ነበር:: የኢየሱስ የቅርብ ደቀ መዛሙርት የተሻለ ያውቃሉ ብላችሁ ታስቡ ይሆናል:: ሆኖም ከ2000 ዓመታት በኋላም እንኳ ትምህርቱ በላቀ መልኩ ግንዛቤ አላገኘም አልተተገበረም::

እንግዲህ ችግሩ ይህ ነው፡- የኢየሱስን መንገድ ከመከተል ይልቅ የዓለምን (የአሕዛብን) መንገድ በመከተል ላይ ነን:: የአብያተ ክርስቲያናችን አሠራር እንደ መንግሥትና እንደ ንግዱ ዓለም ነው:: በማዕረግ፣ በደመወዝ፣ በዝና፣ በምርጫ፣ በማበረታቻ ሽልማት አማካይነት ለሥልጣንና ለሹመት እንፎካከራለን:: የኢየሱስ ልብ አዝኗል::

በመንግሥቱ ውስጥ ወደ ትልቅነት የሚመራው መንገድ የኅብረት መሰላል አይደለም:: እውን የሚሆነው በማስታጠቢያ ሣህንና በማድረቂያ ፎጣ ነው (ዮሐ 13፥1-17):: ይህን መገንዘቡ አያስቸግርም:: እንድንረሳው ኢየሱስ ደጋግሞ ነግሮናል:: በእግዚአብሔር መንግሥት ትልቅ ለመሆን አገልጋይ መሆን ነው የሚለው ትልቅ እውነት እንዳይፈጸም የእኛ የታወቀ ቸልተኛነት ችግሩን ይገልጸዋል (1ቆሮ 9፥19፤ 2ቆሮ 4፥5፤ 1ጴጥ 5፥2-3)::

ራስን ስለ ማዋረድ የተገለጠው የኢየሱስ ነገረ መለኮት በቅርብ ርቀት **በመስቀል** ላይ ይገኛል:: ሊብራል የነገረ መለኮት ሊቃውንት ማርቆስ 10፥48ን (እና ማቴ 20፥28) ለማስወገድ ሞክረዋል:: ቃሉ ግን



ግልጽ በመሆኑ የሚያሻማ ትርጒም የለውም:: በጥብቅ መሠረት ላይ ቆሟል:: የኢየሱስ የተልእኮ ሐሳብ የሚከተለው ነው፡- ለኀጢአታችን (ለእኛ ኀጢአት) በመሞት የሰውን ዘር ማገልገል:: «ቤዛ» [ላይትሮን - lytron] የሚለው ቃል በግሪኮች ዘንድ ተዘውትሮ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረ ቃል ሲሆን፣ ባሪያን ወይም እረኞችን ነጻ ለማውጣት የሚከፈል ዋጋ ነበር::[102] አንዳንድ ጊዜም በአጋንንት ከመያዝና ከባዕድ የአምልኮ ርግማን ነጻ ለወጡ ሰዎች የሚከፈል ዋጋ ነበር:: ከዚህም በላይ በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ውስጥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተደረገውን «ትድግና» ለመግለጫነት አገልግሎት ላይ ውሎአል (ዘፀ 30፥12፤ መዝ 49፥7-9):: ኢየሱስ ምርኮኞችን ከኀጢአት ባርነት ነጻ ማውጣቱን በሚያሳየው መግለጫ (ሮሜ 6፥16-18፤ ኢሳ 53፥10-12) የአሕዛብና (ግሪክ) የአይሁድ (የዕብራውያን) ዓለማት አንድ ይሆናሉ::

ማርቆስ 10፥45 ውስጥ «ለ ...» የሚለውን መስተዋድድ [አንቲ - anti] እናገኛለን፤ ይህም «ምትክ ሆኖ» ማለት ነው:: ኢየሱስ «በብዙዎች ፈንታ ሞተ» ቢል ኖሮ ይህን ያህል ግልጽ አይሆንም ነበር:: የእርሱ ሞት ምትክ ነው፤ የእኛ ምትክ መሆን::

**§ 126**
**በኢያሪኮ ዐይነ ስውሩን በርጤሜዎስን መፈወስ**
**(ማቴ 20፥29-34፤ ማር 10፥46-52፤ ሉቃ 18፥35-43)**

ዐይነ ስውሩን በርጤሚዎስን መፈወስ (ተምሳሌት) ይመስላል:: በአንድ በኩል ወዳለፉት ሦስት ዓመታት መለስ ብሎ በመመልከት የኢየሱስን መሲሐዊ አገልግሎት በምሳሌነት ያሳያል (ሉቃ 4፥18):: በሌላ በኩልም ወደ ኢየሩሳሌም ዐይነ ስውርነት ወደፊት ይመለከታል (ከዮሐ 9፥39-41 ጋር

[102] A.Y. Collins, "The Significance of Mark 10:45 among Gentile Christians," *HTR* 90/4 (1997): 371-382.

ያነ)፣ ተቃራኒ መስል እውነትንም ገልጦ ያሳያል:: ዐይነ ስውሩ ለማኝ ያያል፤ የእስራኤል አለቆች ግን ዐይነ ስውሮች ናቸው::

ማር 10፥46 ከሉቃ 18፥35፤ ከማቴ 20፥30 ጋር

46 ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ:: ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጡ (ወደ ኢያሪኮ በቀረቡ ጊዜ[ሉቃ]) ዐይነ ስውሩ የጤሜዎስ ልጅ በርጤሜዎስ (ሁለት ዐይነ ስውሮች ነበሩ[ማቴ]) በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር::

ሉቃ 18፥36-39

36 ዐይነ ስውሩም ሕዝቡ በዚያ ሲያልፍ ሰምቶ ስለ ሁኔታው ጠየቃቸው:: 37 እነርሱም «የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚህ እያለፈ ነው» ብለው ነገሩት::

38 እርሱም፣ «የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ ሆይ፤ ማረኝ!» እያለ ጮኸ::

39 ከፊት የሚሄዱ ሰዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን፣ «የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረኝ!» እያለ ጮኸ::

የኢያሪኮ ከተማ ከሰሜን ምሥራቅ ኢየሩሳሌም ሃያ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች:: ወደ ዐረቢያ በሚወስደው የንግድ መሥመር ላይ ከሚገኙት ዐበይት ማረፊያዎች አንዷ ናት:: ለፋሲካ በዓል ከሶርያ፣ ከገሊላ፣ ከዐሥሩ ከተማዎች፣ ከመስጴጦምያና ከዐረቢያ ለሚመጡት የእምነት ተጓዦች የመጨረሻዋ ማረፊያ ናት:: ዘንባባ፣ የበለስ ዛፍ፣ የአትክልት ቦታ፣ የዐይን ሕመምን ለመፈወስ የሚያገለግል ዕፅም የሞላበት ለም ሥፍራ ናት (Strab 16:2. 41)፤ (Carson, p. 435)::



ኢየሱስ ከከተማዋ ውጭ መንፈሳዊ ተጓዦችን እየመራ ሳለ ሁለት ዐይነ ስውሮችን ድንገት አገኘ::[103] ማርቆስና ሉቃስ በወንጌላቸው የሚገልፁት አንድን ሰው፣ በርጤሜዎስን ብቻ ነው (ማር 10፥46):: ወደ ኢየሱስ የጮኸው እርሱ ነው:: ማቴዎስ ግን በዚያኑ ዕለት ሁለት ሰዎች መፈወሳቸውን ነው የሚነግረን:: ጌርጌሴኖን ውስጥ በአጋንንት በተያዙት በሁለት ሰዎች ላይ ያደረገውም ይህንኑ ነው (ማቴ 9):: ይህም የማቴዎስ የዐይን ምስክርነት ዝርዝር ባሕርዩ ነው::

በርጤሜዎስና ጓደኛው መንገድ ዳር ተቀምጠው ይለምኑ ነበር:: በዚያ ዘመን አንድ ዐይነ ስውር ኑሮውን የሚገፋው በዚህ ዐይነት መንገድ ብቻ ነበር:: ሰዎቹ ዐይነ ስውሮች ቢሆኑም ለመስማት ይችላሉ:: ተጓዡ በሚያልፍበት ወቅት ሁከታ ሰሙ:: ወደ ኢየሩሳሌም የሚያቀናው ሕዝብ መንፈሳዊ ተጓዦችን፣ ሲራራ ነጋዴዎችን፣ በዚህ ቍልፍ ከተማ ላይ የሚሰፍሩ የሮም ወታደሮችን፣ በፋሲካ ፌስታ ላይ የማይቀረውን ፈንጠዝያ ተተግነው ጥቅም የሚያድኑትን ሰዎች ያካተተ ነበር::

---

103 ማቴዎስና ማርቆስ ኢየሱስ ሰዎቹን ያዳናቸው ኢያሪኮን ለቅቆ በሄደ ጊዜ ነው ይላሉ:: ሉቃስ ደግሞ ወደ ኢያሪኮ ሲገባ ነው ይላል:: ይህ ግልጽ ልዩነት በቀላሉ ይፈታል:: ያኔ የኢያሪኮ ሁለት ስፍራዎች ነበሩ (Josephus, *War* 4.459):: የሚራራቁት አንድ ምዕራፍ (ማይል) ያህል ብቻ ነበር:: ስለዚህ ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች የፈወሳቸው ወደ አዲሲቱ ከተማ ከመግባቱ በፊት አሮጌዪቱ ከተማ ውስጥ ነው:: ማቴዎስና ማርቆስ በመፈራረስ ላይ ወደነበረችው የብሉይ ኪዳንን ስፍራ አመላከቱ፤ በግሪክ ሥልጣኔ የተገራው ሉቃስ ግን በታላቁ ሄሮድስ ዳግም የተሠራችውን ውብ ስፍራ አመለከተ::

ሌላው መፍትሄ ሉቃስ የበርጤሜዎስንና የዘኬዎስን ታሪክ የጻፈው፣ ኢየሱስ ኢያሪኮን የጎበኘው በዘኬዎስ ታሪክ በኩል የትረካው ጣራ (ከፍተኛ ደረጃ) በደረሰበት የጊዜ ቅደም ተከተል ሳይሆን፣ በርእሰ ጉዳዩ አንጻር ነው:: ስለዚህ የማያስፈልግ መምታታት እንዳይኖር በማሰብ፣ ኢየሱስ ሰዎቹን ያዳናቸው ከከተማዋ ሲወጣ ሳይሆን ወደ ከተማዋ ሲገባ መሆኑን አመለከተ:: ያም ሆነ ይህ ማር 10፥46 ኢየሱስ ወደ ከተማዋ ሲገባና ከከተማዋ ሲወጣ ሁለቱን ሁኔታዎች ያወሳል:: ሉቃስ የጥቅሱን የመጀመሪያ ክፍል ሲከተል፣ ማቴዎስ የጠቀሰው ሁለተኛውን ግማሽ ብቻ ነው::

ነገሩ ምን መሆኑን ለማወቅ በርጤሜዎስ አንዱን ሰውየ ጠየቀ:: ኢየሱስ በከተማቸው በኩል በማለፍ ላይ መሆኑ ተነገረው:: ይህ ዐቢይ ዜና ነው! ሹክሹክታው ከበርጤሜዎስ ንቁ ጆሮዎች አላመለጠም:: ከዐሥራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር በላይ ርቃ በምትገኘው ቢታንያ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት የማስነሳቱ ወሬ ተዳርሶአል:: በእግዚአብሔር ላይ ስድብ አሰምቶአል፤ ለሕግጋቱም አይገዛም በሚል ሰበብ የፍርድ ሸንጎው ይከታተለዋል የሚል ወሬም ተሰምቶአል:: በርጤሜዎስ ስለዚህ ሁሉ ወሬ ደንታ የለውም:: የሚያውቀው ነገር የሞተውን ያስነሣ ሰው ብርሃኑን ሊሰጠው የሚችል መሆኑን ነው! ይህ ለእርሱ ይበቃዋል::

«የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረኝ!» በማለት መጮኽ ጀመረ:: ከአንድ ዓመት በፊት የገሊላው ዐይነ ስውር ብርሃኑን ለማግኘት የተጠቀመበት ሐረግ ይህ ነው (ማቴ 9÷27-31):: ይህ ሐረግ ሁለቱም ታሪኮች ውስጥ አገልግሎት ላይ በመዋሉና ሁለት ዐይነ ስውሮችን የሚመለከት በመሆኑ የአንዱ ፈውስ ሁለት ገለጻዎች ናቸው በማለት አንዳንዶች ሐሳብ ሰንዝረዋል:: ይህ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የማይሆን ጉዳይ ነው:- (1) ማቴዎስ ለሁለቱም ታሪኮች የዐይን ምስክር ነው፤ በመሆኑም ሊያምታታቸው አይችልም:: (2) ድርጊቶቹ ከአንድ ዓመት በላይ በመለያየት፣ በተለያየ ቦታ የተከናወኑ ናቸው:: (3) የመጀመሪያው ታሪክ ዝም ይል ዘንድ በተሰጠ ትእዛዝ ተፈጽሞአል (ማቴ 9÷30):: በርጤሜዎስ ስለ ሌላው ዐይነ ስውር ፈውስ ሰምቶ ስለ ነበር ይህን ሐረግ ሊጠቀምበት ይችላል፤ ወይም ከድምሩ ሕዝብ ይልቅ እነዚህ ሁለት ዐይነ ስውሮች፣ የኢየሱስን ማንነት በመረዳት ረገድ ብልጥች ሊሆኑ ይችላሉ:: ያም ሆነ ይህ ከዚህ በላይ የሆነ መሲሓዊ ማዕረግ



ሊኖር ይችላል (ኢሳ 10÷1፤ ኤር 23÷5-6፤ ሕዝ 34÷23-24፤ የክፍል 68 ማስታወሻን ይመ)::[104]

ከሕዝቡ ፊት ለፊት የሚጓዙት በበርጤሜዎስ ጩኸት አልተደሰቱም:: ደቀ መዛሙርቱ በሕፃናቱ ላይ እንዳደረጉት ሁሉ ዝም ሊያሰኙት ሞከሩ (ክፍል 123):: እርሱ ግን ዝም ሊያሰኙት በጣሩ ቁጥር የኢየሱስን ትኩረት እስከሚያገኝ ድረስ ጩኸቱን አስተጋባ::

**ማር 10÷49-52**
**ከሉቃ 18÷41፤**
**ከማቴ 20÷34 ጋር**

49ኢየሱስም ቆሞ፣ «ጥሩት» አላቸው:: እነርሱም ዐይነ ስውሩን፣ «አይዞህ፤ ተነሥ፤ ይጠራሃል!» አሉት:: 50እርሱም ልብሱን ጥሎ ብድግ በማለት፣ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ::

51ኢየሱስም፣ «ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?» አለው::

ዐይነ ስውሩም፣ «መምህር ሆይ (ጌታ ሆይ[ሉቃ])፤ እንዳይ እፈልጋለሁ» አለው:: (ኢየሱስም ራራላቸው፤ ዐይኖቻቸውንም ዳሰሰ፤[ማቴ])

52ኢየሱስም፣ «ሂድ እምነትህ አድኖሃል» አለው፤

**ሉቃ 18÷43**

43ሰውየም ወዲያውኑ ማየት ቻለ፤ እግዚአብሔርንም እያከበረ ኢየሱስን ተከተለው:: ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ እግዚአብሔርን አመሰገኑ::

ኢየሱስ ጉዞውን አቁሞ በርጤሜዎስ ወደርሱ እንዲመጣ አደረገ:: ሲያንቋሽሹት የነበሩት ሰዎች ወዲያው በርጠሚዮስን ማደፋፈር ጀመሩ:: በአዲሱ መደበኛ ትርጉም (አ.መ.ት.)፣ «አይዞህ»

104 «የዳዊት ልጅ» የሚለው ማዕረግ ቀድሞም አገልግሎት ላይ የዋለው በፈውስ ዐውድ ውስጥ ነው:: አይሁድ መሲሓቸውንና ንጉሣቸውን ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ማዕረጉ በእነርሱ ላይ የተሰነዘረ ነቀፋ ነው ይላል Kingsbury:: ይኸውም የተገፉት ዐይነ ስውሮች እውነተኛ ንጉሣቸውን «አዩ፤» የሃይማኖት አለቆች ግን እርሱን የማያዩ ዕውሮች ነበሩ (ከዮሐ **9÷40-41 ጋር ያነ**):: ("The Title 'Son of David' in Matthew's Gospel," *JBL* 95/4 [1976]: 591-602).

የሚለው ቃል አበረታችነቱ እስከዚህም ነው:: ይህ ቃል ከዚህ ሌላ በማንኛውም ቦታ አገልግሎት ላይ የዋለው [ታርሴዎ - *tharseo*] በሚል ፍቺው በኢየሱስ ሲሆን፣ አገልግሎት ላይ የዋለው የፈውስን ወይም የደኅንነትን ተስፋ ሲሰጥ ነው (ማቴ 9፥2:22፤ 14፥27፤ ማር 6፥50፤ ዮሐ 16፥33፤ ሐሥ 23፥11):: ይህ ሰው ዐይኑ እንደሚበራለት ጥርጥር አልነበረውም:: ልብሱን ትቶ ወደ ኢየሱስ መሮጡ ሙሉ እምነት ያለው መሆኑን ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር በጣም ውድ የሆነ ንብረቱን እነበረበት ትቶት ሄደ:: ለዐይነ ስውር ለማኝ ድርጊቱ አስፈሪ ነው:: ድርጊቱን የፈጸመው ብርሃኑን እንደሚያገኝ ርግጠኛ በመሆኑ ይመስላል::

በርጤሜዎስ ምን እንደሚፈልግ ኢየሱስ ያውቃል፤ ሆኖም ጠየቀው:: ከበርጤሜዎስ እምነት እንዲወጣ ለማድረግና ከሕዝቡም ተገቢ ምላሽ እንዲታይ ስለ ፈለገ ነው ይህን ያደረገው:: ማቴዎስ የግሉ በሆነ አገላለፅ ኢየሱስ በርጤሜዎስን እንዲሁ በመፈወስ ብቻ እንዳልረካ ይነግረናል:: ዐይኑን የዳሰሰውም ስለ ራራለት መሆኑን ይገልጽልናል (ከማቴ 9፥36፤ ከ14፥14፤ ከ15፥32፤ ከማር 1፥41 ጋር ያነ):: ከፈውሱ በኋላ በርጤሜዎስ ወደፈለገበት እንዲሄድ ኢየሱስ ፈቅዶለት ነበር:: እርሱ ግን ወደ ኢየሩሳሌም ከሚያቀናው ሕዝብ ጋር መሄድን መረጠ:: አዲስ ብርሃን የሰጠው ይህ ሰው ሲገደል ማየቱ ለበርጤዎስ ምን ያህል አስደንጋጭ ይሆንበት!

**§ 127ሀ**
**የዘኬዎስ ድነት**
**(ሉቃ 19፥1-10)**

ስለ ዘኬዎስ የሚነግረን ሉቃስ ብቻ ነው :: ለእርሱ ከኢየሱስ አገልግሎቶች ይህ



አነስተኛው ክሥተት ነው::[105] በመጨረሻዎቹ አራት ምዕራፎች ውስጥ ሉቃስ በታናናሾቹና በጠፉት ሰዎች ጉዳይ ላይ አተኮረ:: ስለ ተዋረዱትና በውጭ ስላሉት መናገሩን ቀጠለ ማለት ነው:: አሁን ደግሞ ይህን «ከፍ ያለውንና በውጭ የሚገኘውን» አድምቆ ያሳያል:: እንደ ሌሎቹ እንደ ተናቁት እርሱንም በደስታ ተቀበለው:: ሉቃስ ጽሑፉን የወንጌሉ ዋና ሐሳብ ነው በሚባለውና «የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው» በሚለው ድምዳሜ ማጠቃለሉ በእጅጉ ትክክል ነው::

**ሉቃ 19፥1-6**

1ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ በዚያ አልፎ ይሄድ
ነበር:: 2ስሙ ዘኬዎስ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤
ዋና ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ:: 3እርሱም ኢየሱስ
የተባለው የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱ አጭር ነበረና ከሕዝቡ
ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም:: 4ኢየሱስ በዚያ መንገድ ያልፍ ስለ ነበርም፣ ወደ
ፊት ሮጠ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ::
5ኢየሱስም እዚያ ቦታ ሲደርስ፣ ቀና ብሎ፣ «ዘኬዎስ ሆይ፤ ዛሬ አንተ ቤት
መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ» አለው:: 6እርሱም ፈጥኖ ወርዶ በደስታ
ተቀበለው::

ኢየሱስ በመምጣት ላይ የመሆኑ ዜና ኢያሪኮ ተደረሰ:: ርግጥ ነው በጥንቷ ከተማ ዳርቻ ላይ ሁለቱን ዐይነ ስውር ለማኞች መፈወሱ የከተማው ነዋሪዎች በኢየሱስ ላይ ያላቸውን ፍላጎት ከፍ አድርጎታል:: ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ የነበሩት ሰዎች የጉዞአቸውን የመጨረሻ ዕለት አስተላለፉት:: በዚሁ መሠረት ሕዝቡ ድርጊቱ በሚከናወንበት

[105] J.O' Hanlon, "The Story of Zacchaeus and the Lukan Ethic, *JSNT* 12 (1981): 2-26 በሚለው ጽሑፉ ይህ ሁኔታ በተለይ በኢየሱስ የጉዞ ታሪክ ምዕራፍ 18ን አሳጥሮ በማቅረብ በመስክ ላይ የተደረገውን ስብከት ያብራራል:: እንዲሁም ሉቃስ ነገረ መለኮቱን በአጠቃላይ እንዴት አሳጥሮ እንዳቀረበው ጸሐፊው ያሳያል::

ቦታ ተገኝቶ ለመመልከትና የኢየሱስን መምጣት በመጠባበቅ ኢያሪኮ ጐዳና ላይ ተሰለፉ:: ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል አይሁድ ያልሆኑ ወገኖችም ነበሩ:: የሮም ሰላም አስከባሪ ኀይሎች፣ በኢያሪኮ በኩል የሚያልፉ ዐለም ዐቀፍ ነጋዴዎችና ይህ አነስተኛ ግን ኀያል የነበረ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢም ነበሩ::

ዘኬዎስ ተራ ሠራተኛ አልነበረም፤ በኢያሪኮ ከተማ ከፍተኛ ሥልጣን በነበረው ጠቅላይ ግምጃ ቤት ውስጥ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር:: በዙሪያ ባሉት ስፍራዎች ለልዩ ልዩ ኀላፊነትና ለቀረጥ ስብሰባ ለሚሠማሩ ሰዎችም አለቃ ነበር (የቀረጥ ስብሰባን ዝርዝር ጉዳይ ለማወቅ የክፍል 47 ሀ ማብራሪያን ይመ):: ኢያሪኮም በግብፅ፣ በፓለስቲና፣ በዐረቢያና በሶርያ መካከል ባለው መሥመር ዐቢይ የንግድ ማዕከል ነበረች:: በሌላ አባባል ዘኬዎስ በሮም መንግሥት ውስጥ ዋና ተዋናይ ነበር::

እንደ ሕዝቡ ዘኬዎስም ኢየሱስን ለማየት ጓጉቶ ነበር:: ነገር ግን አጭር ከመሆኑ የተነሣ በሕዝቡ ትከሻ ላይ ተንጠራርቶ ኢየሱስን ለማየት ይቸግረው ነበር:: እንደምንም ተጋፍቶ ከፊት በመቅደም ሊያየውም አይችልም:: ቀረጥ ሰብሳቢና የሮም መንግሥት ደጋፊ በመሆኑም የተለየ አክብሮትና ክብካቤ ለማድረግ ማንም ፈቃደኛ አልነበረም:: የነበረው አማራጭ ሩጦ ጐዳናው ላይ በሚገኘው ዛፍ ላይ መውጣት ነበር:: ዛፉም የሾላ ዛፍ (የሾላ ቅጠል ኖሮት የበለስ ፍሬ የሚ ልዩ የዛፍ ዐይነት) ነበር:: እንዲያ ያለ ድርጊት ያን የመሰለ ሥልጣን ለነበረው ሰው ክብሩን ዝቅ የሚያደርግ ይሆናል:: ቢሆንም ብዙ አማራጮች አልነበሩትም፤ ጉጉት አጥብቆ በመያዝ ዛፍ ላይ እንዲወጣ ገፋፋው::

ኢየሱስ እስፍራው እንደ ደረሰ ዘኬዎስን በስሙ ጠራው:: ምናልባት በዚያ ክልል የነበሩትን አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት ኢየሱስ ያውቃቸው ይሆናል:: እውነቱ ግን ይህ የኢየሱስ መለኮታዊ



እውቀት መሆኑን ነበር የሚያመለክተው:: ከሕዝቡ አንዳንዶቹ እንዲህ ሳያስቡ አልቀረም፤ «ኢየሱስ ሆይ፤ ከማን ጋር እንደምትነጋገር ታውቃለህ!» ኢየሱስ ዘኬዎስን በስሙ መጥራቱ ከማን ጋር ይነጋገር እንደ ነበር በትክክል ማወቁን ያመለክታል:: ኢየሱስ ዘኬዎስን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ፈልጎታል («...መዋል ይገባኛል [ዴ ሜኔ - *dei meinei*]) አለ:: ዘኬዎስም በፍጥነትና በጉጉት ምላሽ ሰጠ:: እግዚአብሔር ይወዳቸው ዘንድ በሚመርጣቸው ሰዎችና እርሱም በፍጥነትና በፍቅር በሚያሳዩት ምላሽ ብዙ ጊዜ ግራ እንጋባለን እንከፋለንም::[106]

**ሉቃ 19፥7-10**

7 በዚያ የነበሩ ሰዎችም ይህን አይተው
«ከኃጢአተኛ ቤት ገብቶ ሊስተናገድ ነው» በማለት
ሁሉም ማጉረምረም ጀመሩ::
8 ዘኬዎስ ግን ቆመና ጌታን፣ «ጌታ ሆይ፤ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን
ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ ከሆነ፣ አራት ዕጥፍ አድርጌ
እመልሳለሁ» አለው::
9 ኢየሱስም እንዲህ አለው፣ «ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለሆነ፣ ዛሬ
መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤
10 ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው::»

ከሕዝብ ውስጥ ኢየሱስ እንዲያውቃቸውና በምልክትም ቢሆን እንኳን ሰላምታ እንዲሰጣቸው ይፈልጉ የነበሩት ስንት ናቸው? የእጅ ሰላምታ ወይም ፊርማውን ለማግኘት የጣሩ ስንት ናቸው? በዚህ ሁሉ መሃል የአንድ ሰው ምኞት በድንገት እውን ሆነለት:: ያን ሰው ለመጥራት ኢየሱስ ቆመ ... ዘኬዎስን! እንዲህ ያለ ክብር ከማይገባቸው

---

[106] ይህ ምንባብ ስለ መለወጣችን ውብ የሆነ ውስጠ ወይራ ቃል (እንድምታ!) ይሰጣል:- ኢየሱስ (1) ያውቅሃል፤ (2) ይፈልግሃል፤ ይጠራሃልም፤ ደግሞም (3) ታስፈልጋለህ::

ሰዎች ሁሉ እርሱ የመጀመሪያ ነው:: በመሆኑም ይህ ድርጊት አስፈሪ ስሕተት ነው!

ሕዝቡ ከዘኬዎስ ቤት ውጭ በመገረም ቆመዋል:: ይህ ቀናተኛና አጉረምራሚ ሕዝብ በዚያ ሁኔታ ይቆይ ዘንድ ተገቢው ነው:: በዚህ ጊዜ ዘኬዎስ ተጨባጭ በሆነ መልኩ ንስሐ በመግባት ላይ ነው:: በክርስቶስ አምኖ ክርስቲያን መሆኑ በማታወሻ ደብተሩ ላይ ሊመዘገብ ይችላል::[107]

በመጀመሪያ ላጭበረበራቸው ሰዎች አራት ዕጥፍ በመክፈል የሙሴን ሕግ ተከተለ (ዘፀ 22÷1፤ ከሉቃ 3÷13 ጋር ያነ):: ከዚያም ለድኾች ክብካቤ ይሆን ዘንድ ግማሽ ሀብቱን በመስጠት የክርስቶስን ሕግ አከበረ/ፈጸመ («የፍቅር ሕግ» ገላ 6÷2፤ ያዕ 2÷8):: ኢየሱስ እርሱ ድኗል አለ፤ የዳነውም በፈጸመው መልካም ሥራ ሳይሆን ከአብርሃም ጋር ከነበረው ግንኙነት የተነሣ ነው (ገላ 3÷29):: መልካም


[107] ይሁን እንጂ A.C. Mitchell, "Zacchaeus Revisited: Luke 19:8 as a Defense" *Biblica* 71 (1990) 153-176 በሚለው ጽሑፉ ውስጥ ኢየሱስ ዘኬዎስን በብጤዎቹ ፊት እውነተኛ የአብርሃም ልጅ ነው ይበለው እንጂ ዘኬዎስ ንስሐ የገባ ኀጢአተኛ አይደለም በማለት ክርክሩን ያቀርባል:: ከዚህም በላይ ሉቃስ 19÷8 የዘኬዎስን የዘወትር የቸርነት ሥራ ይገልጻል:: ይህ ደግሞ የንስሐ ምልክት (ድርጊት) አይደለም:: ይህን በማለት ዘኬዎስ ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ከመለወጥ ይልቅ ታማኝ አይሁድ መሆኑን ይፋ ያደርጋል:: ጸሐፊው ትክክል ከሆነ፣ ኢየሱስ «የጠፉትን» ሊፈልጋቸውና ሊያድናቸው መጣ የሚለው ቃል ቢያንስ ማኅበረ ሰባዊ መገለል የደረሰባቸውንም ያካትታል:: ስለዚህ እኛ አዘውትረን «መጥፎ» ሰዎች ስለምንላቸው ሰዎች የምንሰጠውን የተለመደ ሽውራራ አስተያየት ኢየሱስ እንደ ገለበጠው ያመለክታል እንጂ ይህ ታሪክ የመለወጥ ታሪክ አይደለም:: በተጨማሪም የA.C. Mitchell, "The Use of *Sukophantein* in Luke 19:8 Further Evidence for Zacchaeus's Defense" *Biblica* 72 (1991): 546-547; R.C. White, "A Good Word for Zacchaeus, *LexTQ* 14 (1979): 89-96; and D.A. Ravens, "Zacchaeus: The Final Part of a Lucan Triptych?" *JSNT* 41 (1991) 19-32 ይመልከቱ:: ዲ. ሀም የተባለው ጸሐፊ ግን ዘኬዎስ ንስሐ የገባ ኀጢአተኛ ነው የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት በመደገፍ አሳማኝ ክርክር ያቀርባል ("Luke 19:8 Once Again: Does Zacchaeus Defend or Resolve?" *JBl* 107/3 [1988]: 431-437)::



ሥራው የእምነት መግለጫና ማስረጃ ብቻ ነው (ያዕ 2፡14-26):: ዘኬዎስ ከሀብታሙ ወጣት አለቃ በተነጻጻሪነት ይገኛል (ሉቃ 18፡18-30፤ ከሉቃ 12፡33 ጋር ያነ)::

ኢየሱስ ነገሩን በራሱ የተልእኮ ዓላማ ይደመድማል (ቍ 10):: የጠፋት ይገኙ ዘንድ ይፈልጋል:: እንደ ለምጻሞቹ «የተዋረዱና የተገፉ» ወይም እንደ ዘኬዎስ «የከበሩና የተገፉ» ቢሆኑም ኢየሱስ የመጣው የጠፉትን ለመፈለግና ለማዳን ነው:: የጠፉትን ለመድረስ ሳይሳካለት በቀረው ራስ ተኮር ሃይማኖታዊ ፕሮግራማችንና ቀልብጭ ባሉት መቅደሶቻችን (ማደሪያዎቻችን) ይህን ያህል የሚደሰት አይደለም::

**§ 127ለ**
**የምናኑ ምሳሌ**
**(ሉቃ 19÷11-28፤**
**ከማቴ 25÷14-30**
**ጋር ያነ)**



ይህ ምሳሌ ከአምስት ቀን በኋላ በመጨረሻው ሳምንት ማክሰኞ ዕለት ደብረ ዘይት ተራራ ላይ ዐሥራ ሁለቱን ለብቻቸው ባስተማራቸው ጊዜ ከሚነግራቸው ምሳሌ ጋር በጣም ይመሳሰላል (ማቴ 25፡14-30):: በምሳሌዎቹ መካከል አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ ተመሳሳይነቶቻቸው ይበልጥ ድምቀት አላቸው::[108] ሁለቱም ምሳሌዎች የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በዕርገቱና በዳግም ምጽአቱ መካከል ማድረግ የሚገባቸውን እንዴት ማከናወን እንደሚኖርባቸው ይገልጻሉ::

[108] ልዩነቶች:- (1) ንጉሥ ከሀብታሙ ሰው አንጻር ይገኛል፤ (2) የገንዘብ መጠንና ሽልማት እናም (3) ንጉሡን መጥላት:: ተመሳሳይነቶች:- (ሀ) መጥፎው አገልጋይ ገንዘቡን እንዲያተርፍ ከማድረግ ይልቅ አስቀመጠው፤ (ለ) ንጉሡ፣ «አንተ ታማኝ አገልጋይ መልካም አድርገሃል» አለው፤ ደግሞም፣ «ላለው ሁሉ ይጨመርለታል» አለ፤ (ሐ) ትርፉ ገንዘብ ብዙ ላተረፈው አገልጋይ ተሰጠው፤ (መ) ሁለቱም ምሳሌዎች በፍርድ ተደመደሙ::

***ሉቃ 19÷11-15***

[11]ሕዝቡ ይህን እየሰሙ ሳሉ፣ በምሳሌ
መናገሩን ቀጠለ፤ ምክንያቱም ወደ ኢየሩሳሌም
በመቃረቡና ሰዎቹም የእግዚአብሔር መንግሥት
የሚገለጥ ስለ መሰላቸው ነው:: [12]ስለዚህም እንዲህ
አለ፤ «አንድ መስፍን የንጉሥነትን ማዕረግ ተቀብሎ
ለመመለስ ወደ ሩቅ አገር ሄደ:: [13]ከአገልጋዮቹም
መካከል ዐሥሩን ጠርቶ ዐሥር ምናን″ ሰጣቸውና
«ተመልሼ እስክመጣ ድረስ በዚህ ገንዘብ ነግዱበት» አላቸው::
[14]የአገሩ ሰዎች ግን ስለ ጠሉት፣ «ይህ ሰው በላያችን እንዲነግሥ
አንፈልግም» ብለው ከኋላው መልእክተኞችን ላኩበት::
[15]ይሁን እንጂ ይህ መስፍን ንጉሥ ሆኖ ወደ አገሩ ተመለሰ፤ እነዚያ
አገልጋዮቹም እርሱ በሰጣቸው ገንዘብ ነግደው ምን ያህል እንዳተረፉ ለማወቅ
አስጠራቸው::

*″13 አንድ ምናን የሦስተ ወር ደመወዝ ያህል ነበር::*

ኢየሱስ ወደ ዋናይቱ ከተማ በተቃረበ መጠን መሲሓዊ የሆነውን ንግሥና አሁን ያከብራል የሚለው ተስፋ ከዳር እስከ ዳር እየበረታ መጣ:: ገሐዳዊና የዚህ ዓለም መንግሥት በእርሱ እውን ይሆናል የሚለውን ሐሳብ ደቀ መዛሙርቱ እንኳ ሳይቀሩ ይዘውት ነበር (ማቴ 24÷1-3፤ ሐሥ 1÷6):: ስለዚህ ይህን የተሳሳተ ተስፋ ለማስተካከል ኢየሱስ የምኑን ምሳሌ ተናገረ::

የትረካው ክር (የታሪክ መዋቅሩ) ቀላል ነው:- አንድ ሀብታም ሩቅ ከሚገኝ መንግሥት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በማድረግ ንጉሥ ለመሆን ጥረት አደረገ:: በሚሄድበት ጊዜ ለአንዳንድ መጋቢዎቹ በገንዘቡ ጉዳይ ላይ ኀላፊነት በመስጠት እርሱ በሌለበት ወቅት ትርፍ እንዲያስገኙለት ተስፋ አደረገ:: ነገር ግን የተጠላ ሰው ስለ ነበር፣ ይህ



ሰው ንጉሥ እንዳይሆን በሩቅ ላለው መንግሥት አቤቱታ ያቀርብ ዘንድ የአካባቢው ምክር ቤት የዲፕሎማሲ መልእክተኛ ላከ::

ኢየሱስ ይህን ምሳሌ በተናገረ ጊዜ አድማጮቹ ትዝታ ውስጥ ገቡ:: እንግዲህ ልብ በሉ ይህ ጉዳይ እውን የሆነው ከሃያ አምስት ዓመት በፊት ነው:: አርኬላዎስ በአባቱ በታላቁ ሄሮድስ እግር ተተካ:: የይሁዳ፣ የሰማርያና የኤዶምያስ ንጉሥ ሆነ:: ይሁን እንጂ በዚህ አልረካም:: ስለዚህ ኢያሪኮ ያለውን ቤተ መንግሥቱን ትቶ የንጉሥነት ሹመት ለመጠየቅ ወደ ሮም ተጓዘ (6 ዓ.ም.):: አይሁድ ጠልተውት ነበርና አርኬላዎስ በላያቸው እንዳይነግሥ አቤቱታ አቅራቢ መልእክተኞችን ወደ ቄሣር ላኩ:: ከዚህ የተነሣ አርኬላዎስ ከሥልጣን ወረደ:: አይሁድም ድል አገኙ:: በምሳሌው ውስጥ ያለው መስፍን በዚህ ሁኔታ ንጉሥ ሆኖ መመለሱንና የአካባቢውም ሰዎች ሳይሳካላቸው የቀሩ መሆናቸውንበሰሙ ጊዜ ሕዝቡ ደነገጡ!

እዚህ ላይ ሁለተኛ ታሪካዊ ጉድኝት አለ፤ ኢየሱስ ራሱ:: ከዚህ ሕዝብ መካከል ብዙዎቹ ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ «ስቀለው!» እያሉ ይጮኻሉ:: «መስፍኑ» ንጉሥ እንዳይሆንባቸው በማይፈልጉት ወገኖቹ ተጠልቶ ነበር:: ተቃውሞአቸው የሚቆየው ንጉሡ ርቆ እስከቆየ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው:: በሚመለስበት ጊዜ ዜጎቹና (ቊ 27) የራሱ አገልጋዮች ይጠየቁበታል (ቊ 15)::

***ሉቃ 19÷16-23***

[16]«የመጀመሪያው አገልጋይ ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤
የሰጠኸኝ ምናን ዐሥር ምናን ትርፍ አስገኝቶአል'
አለው::
[17]«ጌታውም፣ 'አንተ ታማኝ አገልጋይ፤ መልካም አድርገሃል፤ በትንሹ ነገር
ታማኝ ሆነህ ስለ ተገኘህ፣ በዐሥር ከተሞች ላይ ሥልጣን ተሰጥቶሃል' አለው::

18«ሁለተኛውም ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ የሰጠኸኝ ምናን አምስት ምናን ትርፍ
አስገኝቶአል' አለው::

19«ጌታውም፣ 'አንተ ደግሞ በአምስት ከተሞች ላይ ሥልጣን ተሰጥቶሃል'
አለው::

20ሌላውም አገልጋይ ቀርቦ እንዲህ አለው፤ 'ጌታ ሆይ፤ በጨርቅ ጠቅልዬ
ያቆየሁት ምናንህ ይኸው፤ 21አንተ ያላስቀመጥኸውን የምትወስድ፣ ያልዘራኸውን
የምታጭድ ጨካኝ ሰው ስለ ሆንህ ፈራሁህ::'

22«ጌታውም እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ! በራስህ ቃል
እፈርድብሃለሁ፤ ያላስቀመጥሁትን የምወስድ፣ ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው
መሆኔን ካወቅህ፣ 23መጥቼ ገንዘቤን ከነትርፉ እንድወስድ፣ ለምን ለሚሠራበት
ሰዎች አልሰጠህም?'»

ዐሥር አገልጋዮች ለእያንዳንዳቸው ምናን ተሰጣቸው (የሦስት ወር ደመወዝ የሚሆን):: ለመስፍኑ ትንሽ ገንዘብ ነው፤ የአገልጋቹን ችሎታ ለመመዘን ግን በቂ ገንዘብ ነበር:: ከዐሥሩ አንዱ ዐሥር ምናን አተረፈ:: አስደናቂ ትርፍ ነው 100%:: ሌላው አገልጋይም 500% በማትረፍ ድንቅ ነገር አከናወነ:: ሁለቱም አድናቆትን በማግኘት ላተረፉበት ለእያንዳንዱ ምናን በመላዪቱ ከተማ ውስጥ አለቆች ሆኑ:: በትንሽ ነገር በመታመናቸው ብዙ ተሰጣቸው (ሉቃ 16÷10)::

ሦስተኛው አገልጋይ ግን መልካም አልሠራም:: ሙከራ እንኳን አላደረገም:: የተቀበለውን ነገር ደበቀ! ምክንያቱ ፍራቻ ነበር:: የራሱን ደካማነት አምኖ በመቀበል ፈንታ፣ ንጉሡ የራሱ ያልሆነውን በመውሰድ «ጨካኝ ሰው» እንደ ሆነ በሌሎችም ጉልበት የሚኖር እንደሆነ በማመልከት ወቀሳ መሰንዘር ጀመረ:: ያቀረበው ምክንያት ግን ሚዛን የሚደፋ ዐይነት አልነበረም:: ይህ ሰው በእውነት ጌታውን የሚፈራ ቢሆን፣ አለቅየውም አገልጋዩ እንዳለው ጨካኝ ሆኖ ቢገኝ፣



እንግዲያውስ የተሰጠው ገንዘብ ወለድ ያስገኝ ዘንድ በሥራ ላይ ባለማዋሉ አገልጋዩ በእጅጉ ቂል መሆን አለበት:: ሊባል የሚቻለው ነገር ሰውየው አሳዳሪውን የጠላ እና ንጉሥ ሆኖ እንደማይመለስም እርግጠኛ መሆኑን ነው:: እንዲያ ቢሆንና የመስፍኑ ንብረት ቢከፋፈል የተሰጠውን ምናን ለራሱ ማስቀረት ይችላል::

**ሉቃ 19÷24-28**

24«ጌታውም እዚያ የቆሙትን 'ምናኑን
ውሰዱበትና ዐሥር ምናን ላለው ስጡት' አላቸው::

25«እነርሱም፣ 'ጌታ ሆይ፤ እርሱ እኮ ዐሥር ምናን አለው' አሉት::

26«እርሱም እንዲህ አለ፣ 'እላችኋለሁ፤ ላለው ሁሉ ይጨመርለታል፤ የሌለው
ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል:: 27ነገር ግን እኔ በላያቸው እንዳልነግሥ
የፈለጉትን እነዚያን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡና በፊቴ ዕረዷቸው'»::

28«ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ቀድሞአቸው
ይሄድ ነበር»::

አሁን መስፍኑ ንጉሥ ነው፤ በንጉሥ ሥልጣኑም ሥራ ይጀምራል:: በመጀመሪያ ሀብቱን በጥበብ አከፋፈለ:: በጣም ሀብታም የሆነው መጋቢ ትርፉን ምናን በመቀበሉ አገልጋዮቹ ተቃውሞ አሰሙ:: ይህ ሚዛናዊነት ላይሆን ይችላል፤ ግን ጥበብ የሞላበት የንግድ ሥራ ነው:: ገንዘብን «በጥበብ» ልማት ላይ በማዋል ፈንታ በዘፈቀደ የሚያደርግ ማነው? ያለንን ጥሬ ገንዘብ ከፍተኛ ወለድ በሚያስገኝ ሥራ ላይ የምናውል ከሆን፣ ታዲያ እግዚአብሔር ሀብቱንና ብድራቱን «የመንግሥቱን ልማት» በሚያስደንቅ ታማኝነት ለሚያከናውኑ መስጠቱ ምን ቅር ያሰኛል? (1ጴጥ 4÷10፤ ከሉቃ 16÷10፤ ከክፍል 117ሀ ማብራሪያ ጋር ያነ):: ይህ ምሳሌ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚናገር ከሆነ፣ አንድ ሰው በመንግሥተ ሰማይ የሽልማት ደረጃዎች አሉ ብሎ ሊያስብ ይችላል::

ሁለተኛ ንጉሡ ሲመጣ የሚችለውን ማንኛውንም ዐመፅ ጸጥ ማድረግ አለበት:: ይህ አስከፊ ሊሆን ይችላል:: ውሎ አድሮ ግን ንጉሡ የዐመፁን መሪዎች በመግደል የብዙ ሰው ሕይወት ያተርፋል:: እንዲሁም ኢየሱስ ሲመጣ መጋቢዎች ነን በሚሉት ላይና በገሐድ በሚቃወሙት ላይ ፍርድና ቅጣት ይኖራል:: በዚህ ምሳሌ ውስጥ የንጉሡን አሳዘኝ ጉዳይ ሁሉ ከኢየሱስ ጋር እንዲገጣጠም ማድረጉ ስሕተት ነው:: ኢየሱስ ለዘላለም አንድ ጉንጩን ሲመታ ሌላውን ይሰጣል ብሎ ማሰቡም ስህተት ይሆናል:: እርሱ መልካም፣ መሀሪና ይቅር ባይ ነው:: ሆኖም እነዚህ ባሕርያት ከፍትሐዊነቱ፣ ከብርቱነቱና ከቅድስናው ጋር የተመጣጠኑ ናቸው:: እርሱ ሊሞከር ወይም እንደ ተራ ነገር ሊታይ የሚገባው አይደለም (ከማቴ 24÷27-30፤ ከራእ 1÷13-18፤ ከ19÷11-18 ጋር ያነ):: መዝሙረ ዳዊት 2÷9-12 ውስጥ እንደሚለው ነው:-

> አንተም በብረት በትር ትቀጠቅጣቸዋለህ፤ እንደ ሸክላ ዕቃ ታደቃቸዋለህ:: ስለዚህ እናንተ ነገሥታት ልብ በሉ፤ እናንተ የምድር ገዦችም ተጠንቀቁ:: እግዚአብሔርን በፍርሃት አገልግሉት፤ ለእርሱ መፈድም ደስ ያሰኛችሁ:: እንዳይቈጣና በመንገድ እንዳትጠፉ ዝቅ በሳችሁ ልጁን ሳሙት፤ ቍጣው ፈጥኖ ይነዳልና:: እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ የተባረኩ ናቸው::

**§ 128ሀ እና 141 ቢታንያ መድረስና በቢታንያ መቀባት (ማቴ 26÷6-13፤ ማር 14÷3-9፤ ዮሐ 11÷55፤ 12÷11)**

ዮሐ 11÷55 የአይሁድ ፋሲካ እንደ ተቃረበም፣
በዓሉ ከመድረሱ በፊት የመንጻት ሥርዐት ለማድረግ
ብዙዎች ከአገር ቤት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ::
56 ኢየሱስንም ይፈልጉት ነበር፤ በቤተ መቅደስ ቆመው፣
«ምን ይመስላችኋል? ለበዓሉ አይመጣ ይሆን?» ተባባሉ::
57 የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ኢየሱስን ይይዙት



ዘንድ የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው እንዲጠቁም ሰጥተው ነበር::

እውነት ነው ኢየሱስ የተወለደው ለመሞት ነው:: የሕይወቱ ፍጻሜ እየቀረበ ስለሆነ ዐበይት ተዋንያኑ ወደ ቦታቸው ተንቀሳቅሰዋል:: ብዙ ሰዎች ወደ መጨረሻው የኢየሩሳሌም ጉዞው አጅበውት በመንገዝ ላይ ሲሆኑ፣ የቀሩት ቀድመው ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ተጉዘዋል:: ለፋሲካ በዓል ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ ለሥርዐታዊ መንጻት ቀደም ብለው ደርሰዋል::

ካህናቱ ለዓመቱ ቅዱስ በዓል ሲጣደፉ ሳለ፣ የቤተ መቅደሱ ኮረብታ በደስታ ፍንደቃ በማሸብረቅ ላይ ነው:: የዚህ ዓመቱ ፍንደቃ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የደመቀ ነበር:: ከተለመደው የፋሲካ ዝግጅት ሌላ ስለ ኢየሱስ የማያቋርጡ ጥያቄዎች ነበሩ:: ሕዝቡም «ኢየሱስ ይመጣ ይመስላችኋል?» በመባባል እርስ በርስ ይጠያየቁ ነበር:: ከዚህ በፊት በነበረው የፋሲካ በዓል ሳይገኝ ቀርቶ ባለፈው የበልግና የክረምት ወቅት በዳስ በዓልና በቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ላይ በተከታይ ተገኝቶአል:: ይህ እየሆነ ሳለ የሃይማኖት አለቆች ኢየሱስ እንዲያዝ ማዘዣ አስተላልፈዋል:: ብዙ አስደናቂ ታምራት ቢያደርግም እንኳ፣ ይህን ሁሉ በግልጽ በመካድ እግዚአብሔርን የሚሳደብና ችግር ፈጣሪ ነው አሉት:: ትልቁ ችግራቸው አልዓዛርን ማስነሣቱ ነው:: ይህ ሊክዱት የማይችሉት ወይም ሊያስተባብሉት የማይቻላቸው ተአምር ነው:: ስለዚህ ኢየሱስንና አልዓዛርን በመግደል ታምሩ እንዳልተደረገ ለማድረግ ዐቀዱ:: ሕዝቡ ግን ለእምነት ባይነሣሡም «ከሞት ተነሥቶአል» የሚባለው ሰው ወሬ ጉጉት አሳድሮባቸዋልና ኢየሱስንና አልዓዛርን ለማየት ናፈቁ::

ዮሐ 12÷1-2
ከማቴ 26÷6፤
ከማር 14÷3 ጋር

የፋሲካ በዓል ስድስት ቀን ሲቀረው ኢየሱስ፣
ከሞት ያነሣው አልዓዛር ወደሚኖርበት፣ ወደ ቢታንያ
መጣ:: 2በዚያም ለኢየሱስ ሲል ራት ተዘጋጀ:: ማርታ
ስታገለግል፣ አልዓዛር ከእርሱ ጋር በማእድ ከተቀመጡት
አንዱ ነበር::

ይህ ድግስ ቅዳሜ ቢፈጸም እንኳ፣ ኢየሱስ በሰንበት ረጅም ጉዞ አይጓዝምና ዓርብ ዕለት ቢታንያ ሳይደርስ አልቀረም:: «የሰንበት ጉዞ» የአንድ ምዕራፍ (ማይል) ሦስት አምስተኛ መሆን አለበት ቢባልም፣ ኢየሱስ በሰንበት ዕለት በማረፍ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትእዛዝ አሁንም አከበረ:: ስለዚህ ዮሐንስ 12÷1 ውስጥ የተጠቀሰውን ስድስት ቀን በሮማውያን፣ «ልዩ» አቈጣጠር እናሰላለን:: በዚሁ መሠረት ኢየሱስና ተከታዮቹ ዓርብ ዕለት ቢታንያ ደርሰዋል ብለን እናስባለን:: ይህ ሲባል ግን ድግሱ የተካሄደው እርሱ በደረሰበት ዕለት ነው ማለት አይደለም:: ዝግጅቱ ሁሉ ሰንበት ከመጀመሩ በፊት ተከናውኖ ዓርብ ዕለት ሊካሄድ ይችላል:: ወይም የሰንበት ዕረፍት ጀምበር ከጠለቀች በኋላ እንደ ተፈጸመ ቅዳሜ ሊፈጸም ይችላል::

ከዚህ ድግስ ጐን ለጐን በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ ኢየሱስ እዚያ መኖሩን ዐውቀው እርሱንና አልዓዛርን ለማየት መምጣታቸውን እንገምታለን (ዮሐ 12÷9):: ይህ መቼ ተከናወነ? እሑድ ዕለት የተከናወነው ሆሣዕና በማግሥቱ መሆኑን እናውቃለን (ዮሐ 12÷12):: ስለዚህ ክንውኖቹን እንደሚከተለው እናቀናብራቸዋለን:- ኢየሱስ ዓርብ ዕለት ቢታንያ ደረሰ፤ በለምጻሙ በስምዖን ቤት አቀባበል ሲደረግለት ሕዝቡ በቢታንያ የሚቆዩበት ምክንያት የለም:: ከደብረ ዘይት ተራራ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቃ ወደምትገኘው ኢየሩሳሌም ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ለኢየሩሳሌም ኗሪዎች ኢየሱስ የት እንዳለ ወሬ የደረሳቸው ዘግይቶ ነው:: ስለዚህ ወደ ቢታንያ ለመመለስ እስከ ቅዳሜ ምሽት



ቆዩ:: ከዚያም በድል በገባበት (የሆሣዕና) ዕለት ከኢየሱስ አጃቢ ሕዝብ ጋር እሑድ ዕለት ተደባለቁ:: በዚህ ሁኔታ እንግዲህ ድግስ የተካሄደው ዓርብ ቀን ወይም ቅዳሜ ምሽት መሆን አለበት::[109]

ቢያንስ ሁለት ቤተ ሰቦች ኢየሱስን ለማክበር የተባበሩ ይመስላል፤ የአልዓዛርና የስምዖን ቤተ ሰቦች:: በትውፊት ደረጃ «ስምዖን» የአልዓዛር ሌላው ስም ነው ለማለት ይቻላል:: ነገር ግን አልዓዛር በኢየሩሳሌም አይሁድ ዘንድ ዝነኛ ነበር (ዮሐ 11÷45-47) ብለን የምንገምት ከሆነ የማይመስል ግምት ነው:: ፈውስ ያገኘ ሰው ቢሆንም፣ አንድ ለምጻም እንኳን እንዲህ ያለውን ክብር ማግኘቱ የማይመስል ነው:: ማርታ በድግሱ ላይ ስታሳልፍ ስለ ነበር፣ የእርሷ ባል ነው ወይም አባቷ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምትም አለ:: አንዲት ሴት የራሷ ባልሆነው ቤት ማስተናገዷ ያልተለመደ ነገር አልነበረም:: በጣም የሚመስለው ጉዳይ አልዓዛርና ስምዖን ሁለቱም ከኢየሱስ ፈውስን አገኙ፤ እርሱን ለማክበርም በልዩ ግብዣ ላይ ተባበሩ::

3ማርያምም ዋጋው ውድ የሆነ ግማሽ ሊትር
(የአልባጥሮስ ቢልቃጥ[ማር]) (በማእድ ላይ ተቀምጦ
ሳለም[ማቴ]) ንጹሕ የናርዶስ ሽቱ አምጥታ (ቢልቃጡንም
ሰብራ ሽቱውን በራሱ ላይ አርከፈከፈችው[ማር]):: በኢየሱስ

ዮሐ 12÷3
ከማር14÷3፤
ከማቴ 26÷7 ጋር

[109] ማቴዎስና (26÷2) ማርቆስ (14÷2) ሁለቱም ይህን ሁኔታ የሚያወሱት የፍርድ ሸንጎው ኢየሱስን ለመያዝ ካካሄደው ሤራና ይሁዳ አውጥቶ አውርዶ ካደረገው ክሕደት ጋር ሲሆን፣ ይህም የተከናወነው ከፋሲካ በዓል ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ነው (በአይሁድ አቈጣጠር ሮብ ዕለት ማለት ነው):: ማቴዎስና ማርቆስ መቀባቱ የተካሄደው ሮብ ዕለት ነው ማለታቸው አይደለም:: ይልቁን ትረካቸውን ያዋቀሩት ቀደም ሲል በነበረው ሳምንት በተካሄደው ሁኔታ ርቱህ ጥያቄና «በምልሰት» ስልት ሲሆን፣ አቀራረቡም የደቀ መዛሙርቱን አለማስተዋል በሚገባ አጉልቶ ያሳያል::

እግር ላይ አፈሰሰች፤ እግሩንም በጠጉሯ አበሰች፤
ቤቱንም የሽቱው መዓዛ ሞላው::

ይህ ቤተ ሰብ ለኢየሱስና ለተከታዮቹ ምግብ ሲያዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው አለመሆኑን ልብ ማለት አለብን (ከሉቃ 10÷38-42፤ ከክፍል 104 ጋር ያነ):: ማርያም በእግሩ ሥር በመቀመጥ እንደ ጎበዝ ተማሪ እርሱን እያደመጠች ለመጀመሪያ ጊዜ አከበረችው:: በዚህ ጊዜ ደግሞ እጅግ ውድ በሆነና ፍቅር በተሞላበት ስጦታ ታከብረዋለች:: ይህ የአልባስጥሮስ ብልቃጥ በአንገቷ ላይ ሳይንጠለጠል አልቀረም:: ከአንጸባራቂ ድንጋይ የተበጀ ሲሆን እጅግ ውድ በሆነ ዕቃ ተቀርጾ የታሸገ ነበር:: ቅባቱን ለማንቆርቆር አንድ ሰው የብልቃጡን አንገት መስበር አለበት::

በውስጡ ቃል በቃል «ከርቤ» ተብሎ የሚጠራ የናርዶስ ሽቱ ሞልቷል:: ሄንድሪክሰን የተባለ ጸሐፊ «ይህ ልዩ ቅባት ድንቅ መዐዛ ካለው ዕፅ የተገኘ ሲሆን፣ በትቤትና በህንድ መካከል በሚገኘው ከፍተኛ የግጦሽ መሬት ላይ ያድጋል» ይላል:: ሦስት መቶ ዲናር የሚያወጣ ሲሆን፣ ገንዘቡ በጊዜው ለአንድ ሰው የአንድ ዓመት ደመወዝ ነው:: ውሃ (ብሎም መታጠቢያ) ውድ በሆነበት ቦት ሽቱ በጣም አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን ሙሉ ብልቃጥ ሽቱ እጅግ ውድ ሳይሆን አይቀርም:: በጣም ብዙ ስላላት ከራሱ ጀመረችና (ማቴ እና ማር) እስከ እግሩ ድረስ አንቈረቈረችው (ዮሐ):: ማንም ሙሉ ብልቃጥ ሽቱ አያስፈልገውም! ካልሞተ በቀር:: ሬሳን በእጅጉ መቀባትና የሰውነት መፍረስን ተከትሎ የሚመጣን ሽታ ለመከላከል በመግነዝ ጨርቅ ዕጥፋት ላይ ሌሎች ቅመማ ቅመሞችና ሽቱዎች ማድረግ የተለመደ ነበር:: ይህ እጅግ ውድ የሆነ ክንዋኔ ትክክል ሊሆን የሚችለው በቅርብ ቀን ከሚሆነው የኢየሱስ ሞት አንጻር ሲታይ ብቻ ነው::



በሰው ደረጃ ሲታይ እንዲያ ውድ በሆነ ወጪ ኢየሱስን ማምለኳ ተገቢ አይደለም:: አባካኝነት ነው:: ይበልጥ አስፈላጊ ለሆኑ ዓላማዎች ሊውል ይችል ነበር:: ከዚህም በላይ ጠጉሯን በአደባባይ ፈታችው፤ ይህም በባህሉ መሠረት ተገቢ አይደለም:: ያም አልበቃት፤ የኢየሱስን እግሮች በጠጉሯ በማበስ ራሷን አዋረደች::[110] ከዚህም የተነሣ ደቀ መዛሙርቱ አጕረመረሙ::

ዮሐ 12÷4-6
ከማቴ 26÷8፤
ከማር 14÷4-5 ጋር

4 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ (ደቀ
መዛሙርቱ[ማቴ])፣ ኋላ አሳልፎ የሚሰጠው የአስቆሮቱ
ይሁዳ ግን በመቃወም እንዲህ አለ (በዚያ ከነበሩት
አንዳንዶቹ በድርጊቱ
ተቈጥተው እንዲህ ይባባሉ ነበር[ማር]) 5 «ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ገንዘቡ
ለድኾች ለምን አልተሰጠም» የአንድ ዓመት ደመወዝ ያህል ነው» (ሴትየዋንም
ነቀፏት[ማር]):: 6 ይህን የተናገረው የገንዘብ ከረጢት ያዥ በመሆኑ፣ ከሚቀመጠው ስሩቱ
የሚጠቀም ሌባ ስለ ነበር እንጂ ለድኾች ተቈርቍሮ አልነበረም::

ማር 14÷6-9
ከዮሐ 12÷7 ጋር

6 ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ «ተዉአት፣
ለምን ታስቸግሯታላችሁ? መልካም ነገር አድርጋልኛለች::
(«ይህ ሽቱ ለቀብሬ ቀን የታሰበ ስለ ሆነ»[ዮሐ]) 7 ድኾች
ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤ በፈለጋችሁ ጊዜ
ልትረዷቸው ትችላላችሁ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም፤ 8 እርሷ ማድረግ
የምትችለውን ያህል አድርጋለች፤ ለመቃብሬ እንዲሆን ሰውነቴን አስቀድማ
ቀብታለች:: 9 እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበከበት በማንኛ
ውም ስፍራ እርሷ ያደረገችው መታሰቢያ ሆኖ ይነገርላታል::»

[110] ብዙዎች ይህ ትዕይንትና ሉቃስ 7÷36-50 ውስጥ ያለው ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች አምሮ ቀረበ እንጂ የተመሠረተው ከአንድ ዐይነት ታሪክ ነው ይላሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህን አንድ ወጥ ታሪክ አድርጎ ለማየት ትረካዎቹ መካከል ያሉት ልዩነቶች በጣም ጉልሕ ከመሆናቸው የተነሣ አያስኬድም::

ደቀ መዛሙርቱ በአስቆሮቱ ይሁዳ ተመርተው የማርያምን ተግባር ተቃወሙ፤ ስለ ድርጊቷም ገሠጿት:: ይሁዳ የተነሣሣው በሥሥት ነው:: ከገንዘብ ከረጢቱ ያጭበረብር ስለ ነበር ከዚህ ላይ ዕድል ያመለጠው መሆኑን አስተውሎአል:: ሌሎቹ ግን ይህን ያደረጉት አርቆ ካለማስተዋልና ከንጹሕ አስተሳሰብ ነው:: ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ለድኾች ሲያስብ ስለ አዩት በዚህ ጉዳይ የእርሱን ልብ የወከሉ መስሎአቸዋል:: ኢየሱስ ግን አሁንም በታሪኩ ላይ አስገራሚ አንድምታ አከለ:: ማርታ በማርያም ላይ ያላትን ወቀሳዊ ጠባይ እንደ ገሠጸ ሁሉ (ሉቃ 10÷40-42)፣ እዚህም ላይ ደቀ መዛሙርቱን ገሠጸ::

ደቀ መዛሙርቱ ይህ ተግባር የቱን ያህል ውብ እንደ ሆነ ማስተዋል ነበረባቸው:: ኢየሱስ ከስድስት እስከ ስምንት የሚደርሱ ኢርቱዕ አገላለጾችን ጨምሮ ቢያንስ ስድስት ጊዜ ስለ ሞቱ በቅድሚያ በግልጽ ተናግሮአል:: በደንብ አልሰሙትም ማለት ነው:: ማርያም ግን በደንብ ሰምታዋለች:: ሥራዋ በቀብር ወቅት የቅባት ሥርዓት ማከናወን ይመስላል:: ኢየሱስ የቀብር ወቅት መቀባት ነው ብሎአል:: ስለዚህ እርሷም ድርጊቱ የቀብር ወቅት መቀባት ነው ብላ ተቀብላለች ተብሎ ሊታሰብ ይችላል:: ኢየሱስ በርግጥ የሚሞት መሆኑን ያመኑት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ደቀ መዛሙርት ምናልባት እርሷና ይሁዳ ሳይሆኑ አይቀሩም:: ምላሻቸው ግን እጅግ የተራራቀ ነው:: ምናልባት አርቆ አስተዋይ ላትሆን ትችላለች፤ ነገር ግን አንዲት ዕድለኛ ሴት ብትኖር፣ ማርያም ናት:: ከደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ይልቅ ኢየሱስን በታላቅ ጥንቃቄ አድምጣዋለች:: አስተዋይነቷንና መስጠቷን ..ስመልክቶም ኢየሱስ ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ እንደምትታወስ ቃል ገብቶላታል

አሁን ደግሞ ድኾች ምንጊዜም እንደማይታጡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አስታወሰ:: ኢየሱስን ለማገልገል ያለው ዕድል ግን ጥቂት



ቀን ነው:: ስለዚህ ይህ የተትረፈረፈና ልግስና የበዛበት ስጦታ ብክነት አይደለም::

ድኾችን ለማገልገል ያለው ዕድል ማለቂያ የለውም:: ኢየሱስን ለማገልገል ያለው ዕድል ግን የተወሰነ ነው:: ዛሬስ ይህ ጉዳይ ምን ይመስላል? ውብ ሕንጻዎች በመሥራትና ለሰባኪዎች በቂ ደመወዝ በመክፈል ረገድ ምንም ስሕተት የለም:: እነዚህ ግን በግል ለኢየሱስ ከሚደረጉት ስጦታዎች ጋር አይወዳደሩም:: አሁን እርሱ ሄዶአል:: ወቅቱ ድኾችን ለማገልገል ጥረታችንን ዕጥፍ ድርብ የምናደርግበት ነው:: ኢየሱስ ድኾችን በረዳ ጊዜ አገልግሎቱን የግሉ አድርጎ ይመለከት ስለ ነበር (ማቴ 25÷40፤ ከዘዳ 15÷11 ጋር ያነ) ይህ በእርግጥ የሚታሰብበት ጉዳይ ነው::

9በዚህ ጊዜ ብዙ አይሁድ ኢየሱስ በዚያ — ዮሐ 12÷9-11
መኖሩን ሰውቀው መጡ፤ የመጡትም ኢየሱስን ብለው
ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ከሙታን ያስነሣውን አልዓዛርንም
ለማየት
ነበር:: 10ስለዚህ የካህናት አለቆች አልዓዛርን ጭምር ለመግደል ተማከሩ፤ 11ይህም
በእርሱ ምክንያት ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሱስ እየሄዱ ያምኑበት ስለ ነበር ነው::

ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ካስነሣው ሁለት ወር ያህል ሆኖታል:: ይህ ሰው ከኢየሱስ ጋር ቁሞ መታየቱ ከአይሁድ ወገን ለብዙ ሰው በኢየሱስ «ማመን» ምክንያት ሆኖአል:: እነዚህ ሁሉ እሩቅ አገር የተከናወኑ ተረት ተረቶች አይደሉም:: ቢታንያ አጠገባቸው ትገኛ ለች፤ አሁን ደግሞ የዚህን ሊታመን የማይቻል ታሪክ እውነትነት ራሳቸው ሊያረጋጡ ችለዋል:: ይሁን እንጂ ሊቃነ ካህናቱ አሁንም አልተበገሩም:: ስለ እነዚህ ልዩ ልዩ የታምራዊ ታሪኮች ግድ የላቸውም:: ግድ ያላቸው ስለ ሹመታቸው አስተማማኝነትና ስለ ተጽዕኖአቸው መጠን ነው:: ኢየሱስና አልዓዛር ለእነዚህ ነገሮች

ዕንቅፋት በመሆናቸው መወገድ አለባቸው:: የእነዚህ የአይሁድ አለቆች ዕውርነትና ግብዝነት በጣም ከፍተኛ ነው:: ሆኖም አለመታደል ሆነና ሹመትና ሥልጣን የእግዚአብሔርን ዐላማና ዕቅዶች በሚፈታተኑበት ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ውስጥ ሁሉ፣ ያ የአይሁድ አለቆች አዚም አሁንም አለ::



# ምድብ ዐሥር
# የመጨረሻው ሳምንት

በአራቱም ወንጌላት ከተዘገቡት የኢየሱስ ሕይወት ሁነቶች ታሪክ ይህ ሁለተኛው ነው:: የመጀመሪያው ሁነት አምስት ሺውን የመገበበት ነው:: አንድ ጉልህ የሆነ ነገር ሊከናወን እንደሆነ ደቀ መዛሙርቱ አውቀዋል:: ወደሚሄድባቸው ስፍራዎች ሁሉ ኢየሱስ የሚንቀሳቀሰው በእግሩ ነበር:: አሁን ግን ከመጨረሻው ግቡ ከአምስት ኪሎ ሜትር ባነሰ ርቀት ላይ ሆኖ በአህያ ጀርባ ይጓዝ ጀመር?! አህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሲገባ[1] ይህ ገጠሬ የፓለስቲና ገበሬ የሆነ ሰው በድንገት ድል አድራጊ ንጉሥ መሰለ:: ሕዝቡ ጓጉተው ነበር፤ ምን ነበር ጉጉታቸው?

## *1. ዝግጅት*

**§ 128ለ**
**በድል አድራጊነት መግባት**
**(ማቴ 21፥1-11:14-17፤ ማር 11፥1-11፤ ሉቃ 19፥29-44፤ ዮሐ 12፥12-19)**

**ማር 11፥1-7ን ከማቴ 21፥2፤ ሉቃ 19፥33-34**

ወደ ኢየሩሳሌም በደብረ ዘይት ተራራ አጠገብ
ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፣
ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ በማለት
ላካቸው፤ 2«በፊታችሁ ወዳለው መንደር ሂዱ፣ ሰው
ተቀምጦበት የማያውቅ የአህያ ውርንጫ እዚያ ታስሮ
ታገኛላችሁ፤ ፈታችሁ አምጡት፤ 3ማንም *ምን
ማድረጋችሁ ነው*? ቢላችሁ፣ *ለጌታ ያስፈልገዋል፤
በቶሎም መልሶ ይልከዋል* ብላችሁ ንገሩት»
4እነርሱም ሄዱ፤ በአንድ ቤት በራፍ አጠገብ
ላይ የአህያ ውርንጫ ታስሮ አገኙት፤ ፈቱትም:: 5በዚያ

---

[1] ከዘካርያስ 14 እና በ P.B. Duff "The March of the Divine Warrior and the Advent of the Greco-Roman King: Mark's Account of Jesus' Entry into Jerusalem" *JBL* 111/ 1 (1992): 55-71 ጋር ያነጻጽሩ::

ከቆሙት አንዳንድ ሰዎች፣ «ውርንጫውን የምትፈቱት ለምንድን ነው?» አሏቸው::
6ደቀ መዛርቱም ኢየሱስ ያላቸውን ለሰዎቹ በነገሯቸው ጊዜ ፈቀዱላቸው::
7ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አምጥተው ልብሳቸውን በጀርባው ላይ አደረጉ፤ እርሱም
ተቀመጠበት::

ኢየሱስ በስተ ምሥራቅ አምስት ኪሎ ሜትር ከምትርቀው ከቢታንያ ተነስቶ ኢየሩሳሌም ደረሰ:: በሁለቱ ከተሞች መካከል ከባህር ወለል በላይ የ2600 ጫማ ከፍታ ያለው የደብረ ዘይት ተራራ ይገኛል:: ተራራው በተለይ ከቤተ መቅደሱ አደባባይ 300 ጫማ ያህል በቀጥታ ዝቅ ብሎ ለሚገኘው ስፍራ ደስ የሚያሰኝ ግርማ ያለው እይታ ያጐናጽፈዋል:: በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ኢየሱስ በዚህ ተራራ ላይ ብዙ ትዝታዎችን ሲያወጣና ሲያወርድ ይቆያል:: ለኢየሩሳሌም ያነባል፣ የተራራው ስብከቱን ያስተላልፋል፣ በጌቴሴማኒ ይጸልያል፣ ወደ ሰማይም ያርጋል::

በምሥራቅ በኩል ወደ ደብረ ዘይት ተራራ በሚያስወጣው አቀበት ቤተ ፋጌ የተባለች አነስተኛ መንደር አለች:: እዚያ ስፍራ ሆኖ ኢየሱስ በስም ያልተጠቀሱ ሁለት ደቀ መዛሙርት (ጴጥሮስና ዮሐንስ ሳይሆኑ አይቀሩም) አንዲት አህያ ከነውርንጫዋ[2] እንዲፈልጉ ላካቸው:: ማቴዎስ የተላኩት ሰዎች ያመጧቸው ሁለት እንስሳትን እንደ ነበር

[2] J.D.M. Derrett "Law in the New Testament: The Palm Sunday Colt," *NovT* 13 (1971): 241-258 በሚለው መጽሐፋቸው መንግሥት እንስሳትን ከአጠቃላዩ ኅብረተሰብ ነጥሎ ለራሱ አገልግሎት ሊያውላቸው ይችላል ብለዋል:: 1ሳሙ 8÷17 ይህን መሳይ ልምድ በብሉይ ኪዳን ድጋፍ እንዳለው ይገልጻል:: ከዳዊት የዘር ሐረግ እንደ መምጣቱና መሲሕም እንደ መሆኑ፣ ኢየሱስ በእርግጥ ይህ መብት ነበረው:: በአንዳንድ የተወሰኑ ሁኔታዎች መሠረት መምህራንም (ረቢዎችም) ይህ መብት ነበራቸው:: ይሁን እንጂ መንግሥት እንደሚያደርገው ሳይሆን፣ ኢየሱስ በእንስሳው ለመጠቀም ፈቃድ ጠየቀ:: እንደሚመልሰውም ቃል ገባ:: በመሆኑም ሐዋርያቱ በዘፀ 22÷14-15 የተሰጣቸውን እንስሳ ተውሶ የመመለስ ሕጋዊ ኀላፊነት ያከበሩ ይመስላል::



ይገልጻል::[3] ማርቆስ ደግሞ ይህ ለምን እንደሆነ ገልጧል:: በውርንጫው ላይ ማንም ጋልቦበት አያውቅም::[4] ኢየሱስ ተስፈንጥሮ እንዳይወድቅ ከተፈለገ በተለይ ሁካታ በበዛበት አጀብ ውስጥ ውርንጫው ይረጋጋ ዘንድ የውርንጫውን እናት ይዘዋት ቢመጡ ይሻላቸዋል::

ኢየሱስ ለማይቀረው ጉዳይ አዘጋጅቷቸዋል - መቼም አንድ ሰው እንስሳውን ለምን እንደሚወስዱበት መጠየቁ አይቀርም:: የሚሰጡትም ምላሽ «ለጌታ ያስፈልገዋል» የሚል ይሆናል:: *ጌታ* የሚለው ቃል ምናልባት ኢየሱስን ተከትሎ የወጣውን የእንስሳውን ባለቤት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል::[5] ሆኖም ሉቃስ *ባለቤቶቹ* በዚያ ቆመው ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ውርንጫውን ምን እያደረጉት እንደሆነ ሲጠይቁ እንደነበረ ስገለጸ *ጌታ* የሚለው ቃል በይበልጥ *ኢየሱስን* የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ ባለፉት ስድስት ወራት በፓርያና በይሁዳ ቆይቶ እንደነበረ ማስታወስ ይገባናል:: አልዓዛርን ከመቃብር አስነስቶታል፤ እንዲሰብኩ የላካቸውም ሰባዎቹ በዚያ አካባቢ በመቶዎች ምናልባትም በሺዎች የሚቈጠሩ በሽተኞችን ፈውሰዋል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ በዚያ ስፍራ ታዋቂ እንዲሁም ተወዳጅ ነበር:: ስለሆነም ኢየሱስ ሁለት ደቀ መዛሙርቱን እንስሳውን

[3] ማቴዎስ ዘካ 9÷9 ውስጥ ያለውንና በተከታዮቹ ስንኞች በተነጻጻሪ ሐረጎች ምናልባት አንድ ጊዜ ብቻ ተገልጾ ሳለ ሁለት እንስሶች እንደነበሩ መግለጹ (በማቴ 21÷5 ሲጠቅሰው) ክፍሉን እንደሚገባ ባያነበው ነው የሚል ነቀፋ እንዲቀርብበት አድርጓል:: ይሁን እንጂ ከማንም ይልቅ ማቴዎስ ትንቢታዊ ቅኔዎች እንዴት መነበብ እንደሚገባቸው ያውቃል:: እርሱ ያቀረበው ትረካ የተሳሳተ የሥነ አፈታት ውጤት ሳይሆን ትክክለኛ የዓይን ምስክር ዝርዝር ገለጻ ነው::

[4] ማንም ያልጋለበባቸው በሬዎች፣ አህያዎችና ውርንጫዎች አንዳንድ ጊዜ ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር (ዘኍ 19÷2፤ ዘዳ 21÷3፤ 1ሳሙ 6፡7)::

[5] J.M. Ross "Names of God: A Comment of Mk 13:3 and Parallels" *BT* 35/4 (1984):443.

በውስት እንዲያመጡለት የላካቸው ከአካባቢው ደጋፊዎቹ ወደ አንዱ ነበር ብሎ መገመት አግባብ ይሆናል::[6]

## 2. ትንቢት

ማቴ 21÷4-5

[4]ይህ የሆነውም በነቢዩ እንዲህ በማለት የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው::

[5]ለጽዮን ልጅ እንዲህ በሏት፤ እነሆ ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ፣ በአህያይቱና በግልገሏ በውርንጫይቱም ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል»″

″5 ዘካ 9÷9

ትንቢተ ዘካርያስ ስለ መሲሑ በአስደናቂ ግልጽነት ይተነብያል::[7] በተለይም ይህ ምንባብ በብዙ መምህራን (ሩቢዎች) ስለ መሲሑ እንደሚነገር ተደርጐ ተተርጉሟል:: ማቴዎስ ይህ በድል አድራጊነት መግባት እንዴት የዘካርያስ 9÷9 ፍጻሜ እንደ ሆነ ያመለክታል::[8] ኢየሱስ በነቢያት ትንቢት የተነገረለት መሲሕ ቢሆንም ሕዝቡ ይጠብቀው የነበረው መሲሕ እንዳልነበረም አሳይቷል:: ንጉሡ በጦር ፈረስ ላይ ተቀምጦ እየጋለበ ኢየሩሳሌም[9] እንደሚገባ ነበር

---

[6] ብሌንኪንሶፕ ውርንጫውን የመፍታቱ ተግባር ስለ ይሁዳ የተነገረውን ንግርት (ዘፍ 49÷10-11) መሠረት ያደረገ የራሱ የሆነ አስፈላጊነት እንደሚኖረው ይጠቁማል:: ("The Oracle of Judah and the Messianic Entry," *JBL* 80 [1961]: 55-64).

[7] በተለይም ዘካ 9÷9፤ 11÷13፤ 12÷10፤ 13÷7፤ 14÷4

[8] መግቢያው ላይ ያለው ሐረግ በኢሳ 62÷11 ላይ «ለጽዮን ሴት ልጅ፣ እነሆ አዳኝሽ መጥቶአል፤...» ለሚለው የቀረበ ነው:: በኢሳ 62÷11 ያለው ዓውድ ከምንባባችን ጋር አግባብነት ስላለው ማቴዎስ ያላቸውን ግንኙነት እንድንመለከት አቅዶ ሊሆን ይችላል::

[9] የጽዮን ሴት ልጅ» የሚለው በብሉይ ኪዳን በተለይም ዘግየት ብለው በተነሡት ነቢያት (ኢሳ 1÷8፤ 52÷2፤ 62÷11፤ ኤር 4÷31፤ 6÷23፤ ሰቆ.ኤር 2÷4:8:10:13፤ ሚክ 4÷8፤ ሶፎ 3÷14፤ ዘካ 2÷10) «የኢየሩሳሌም ከተማ በሰውኛ የተገለጸችበት ነው» በማለት ቴኒ በመጽሐፋቸው (ገጽ 127) ላይ ገልጸዋል::



የሚጠብቁት (ከራእ 6÷4፤ 19÷11 ጋር ያነ):: የተሰጣቸው ተስፋ የነገሥታትና የሰላም ተምሳሌት በሆነው በአህያ ላይ እየጋለበ (መሳ 5÷10፤ 1ነገ 1÷33) የሚመጣ የሰላም ልዑል ነበር (ኢሳ 9÷6)::

ይህን መሳይ የትንቢት አጠቃቀም እስከ ወንጌላቱ ፍጻሜ የሚቀጥል ይሆናል:: ምንም እንኳ በወንጌላት ሁሉ ኢየሱስ ትንቢትን የመፈጸሙን ሃሳብ ቀደም ሲል ያወቅን ቢሆንም፣ በዚህ የመጨረሻ ሳምንት ምን ይህል ትንቢቶችን እንደሚጽም ስናስተውል በጣም እንደነቃለን:: ከነዚህ የትንቢት ፍጻሜዎች አብዛኞቹ የሚያስተላልፉት መልእክት:- ኢየሱስ በነቢያቱ የተተነበየለት መሲሕ እንጂ ሕዝብ ይጠብቀው የነበረ መሲሕ እንዳልነበረ ነው::

## 3. ምስጋና

ማቴ 21÷8
ከሉቃ 19÷38፤
ዮሐ 12÷12፤
ማር 11÷8 ጋር

[36]ሰዎችም እርሱ በሚሄድበት መንገድ ላይ ልብሳቸውን ያነጥፉ ነበር::

ሉቃ 19÷37

[37]በደብረ ዘይት ተራራ ቁልቁል ወደሚወስደው መንገድ በተቃረቡ ጊዜ፣ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆነ ደቀ መዛሙርት ስላዩት ታምራት ሁሉ ደስ እያላቸው ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ጀመር፤

ማቴ 21÷9
ከሉቃ 19÷38
ማር 11÷10 ጋር

[9]ከፊቱ የቀደሙትና ከኋላው የተከተሉትም በታላቅ ድምፅ፤ እንዲህ ይሉ ነበር፣ ሆሳዕና! በጌታ ስም የሚመጣ (ንጉሥ[ሉቃ]) የተባረከ ነው!″ (የምትመጣው የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት[ማር]) (በሰማይ ሰላም፣ በአርያምም ክብር ይሁን[ሉቃ]) ሆሳዕና[ሰ] በአርያም::

*″9 ትርጉሙ *አድን* የሚል የዕብራይስጥ አገላለጽ ሲሆን ምስጋናን በግነት ለመግለጽ ይውላል በመ 15ም ላይ ተጠቅሷል::*

[9] መዝሙር 118÷26

ኢየሱስ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ በመውጣት ላይ ሳለ ሕዝቡ መሲሕና ንጉሥ እንደሆነ አዋጅ ሊናገሩለት ተዘጋጅተው ነበር:: ይህ ነገር ሲከናወን ሁለተኛ ጊዜው ነበር:: ከአንድ ዓመት በፊት ኢየሱስ አምስት ሺዎቹን (ወንዶች) በመገበ ጊዜ የሕዝብ አጀብ በኃይል ሊያነግሠው ተዘጋጅቶ (ዮሐ 6÷15) ነበር:: ይህ የሆነው ገሊላ ውስጥ ነው:: ይሄኛው ቤተ መቅደሱ በራፍ ላይ ነበር::

ሕዝቡ እንዲያ መሰብሰቡ አጋጣሚ አልነበረም:: ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡ ተሳላሚዎች በዚሁ ተራራ ላይ በመጓዝ ላይ ናቸው:: በፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ግለት ተሞልተው ነው የመጡት:: በተለይ በዚህ ዓመት ይህ እውነት ነው:: ባለፉት ስድስት ወራት በይሁዳና በፔርያ እየተዘዋወረ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል:: የሚከተሉት ደቀ መዛሙርት አጀብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል:: ከዚህም ባሻገር ስለ አልዓዛር የሚናፈሰው ዜና ጉምጉምታ አስነስቷል:: እንዲያውም በየጉዳናው ላይ የሚሰማው ወሬ የካህናት ሸንጎ ኢየሱስንና አልዓዛርን ለመግደል መፈለጋቸው ነው:: ሕዝቡ በሚሆነው ነገር እየተደነቀ አንድ ነገር እየጠበቀና በደስታ እየፈነደቀ ነበር:: መሲሑን በከፍተኛ ደረጃ ይፈልጉታል:: ታምራት የማድረግ ችሎታ ያለው ይህ ሰው ለዚህ ጉዳይ ተቀዳሚ እጩአቸው ነው::

ከተሰበሰበው ሕዝብ አንዳንዶች ልብሳቸውን መሬት ላይ አንጥፈዋል:: ሌሎቹ ደግሞ የዘንባባ ተክሎች በመገንጠል ውርንጫው እንዲረማመድበት መሬት አንጥፈዋል::[10] እነዚህ ሁለቱም ፖለቲካዊና

[10] በዛሬው ዘመን ያሉት የዘንባባ ዛፎች የሚገኙት በኢያሪኮ ነው:: ከዚህም የተነሣ አንዳንዶች የዘንባባ ዝንጣፊዎቹ የመጡት ወደ 30 ኪሎ ሜትር ራቅ ብላ ከምትገኘው ከኢያሪኮ ነበር እንዲሉ ገፋፍቷቸዋል:: ይህ ከድንኳን በዓል አከባበር አንዱ ክፍል ሳይሆን አይቀርም:: ሆኖም ምንባቡ የዘንባባ ዝንጣፊዎቹን ከዚያው ስፍራ ቆርጠው እንዳመጧቸው የሚያመለክት ይመስላል:: ስለሆነም የዘንባባ ዛፎች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ይበቅሉ የነበሩ



ነንድ የአገር መሪ የሚደረጉ እርምጃዎች ናቸው:: በሌላ አነጋገር የሱስን በቅድስት ከተማ እንደ ንጉሥ ተቀብለውት ነበር (2ነገ 13)::

ኢየሱስ ከደብረ ዘይት ተራራ ቁልቁል በመውረድ ላይ ሳለ ፑተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ድምፁ በከተማው ሁሉ እስኪያስተጋባ ኒስታ ሁካታ አሰማ:: ከፍተኛው ድምፅ በራሱ የሰዎችን ሁሉ ኩረት ሲስብ መሲሐዊ አንደምታው ደግሞ ሐሴትን ፈጥሯል:: መምህራኑ (ረቢዎች) ዘንድ መሲሐዊ ተደርጎ ከሚወሰደው ከመዝ 18÷25-26 *ሆሣዕና* እና *የሚመጣ የተባረከ ነው* የሚሉትን ረጐች ተውሰዋል::[11] በእነዚህም ላይ *ዳዊት*፣ *መንግሥት*፣ ሰላም በሰማይ ሰላም* የሚሉትን መሲሐዊ ቃላት ጨምረውባቸዋል:: ዐልእክታቸው ጉልቶና ጥርት ብሎ ይሰማል:: የካህናቱ ጉባዔ ጉዳዩ ንደሚጨነቅ ይጠበቃል:: ለእነርሱም ጉዳይ ኢየሱስ በቅርቡ መልስ ሰጥበታል::

ከካህናቱ ጉባኤ በተጨማሪ ይህ የምስጋና ወጀብ ያለ ጥርጥር ሮማውያኑን የጥበቃ ኃይላት ትኩረት ይስባል:: እነርሱ ሰላም ስጠባቂ ኃይላት ሆነው በኢየሩሳሌም ተመድበዋል:: የአይሁድ ፖለቲካና የሃይማኖት ስሜታዊ ትኩሳት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሚደርስባቸው በአይሁድ በዓላት በተለይ የጥበቃ ኃየላቱ በተጠንቀቅ ሆናሉ:: ይህን መሳዩን የምሥራች በማስተጋባት ወደ ከተማ እየጋለበ

ቢሆንም፣ ከአካባቢው ጨርሶ እንዲወገዱ እንደ ተደረገ ግልጽ ነው (ከB.A. Mastin, "The Date of the Triumphal Entry," *NTS* 16 [1969-70]: 76-82 ጋር ያነ)::

ሆሣዕና የሚለው ቃል ቁም (የቃል በቃል) ትርጉሙ፣ «አሁን አድን» ማለት ነው:: ሆኖም ኢየሱስ በነበረበት ዘመን «ሆሣዕና» የሚለው ቃል በአብዛኛው ጥንታዊ ትርጉሙን አጥቶ እኛ ዛሬ «አሜን» የሚለውን ቃል እንደምንጠቀምበት ዓይነት እንዲሁ የምስጋና መግለጫ ብቻ ሆኖ ነበር:: ይሁን እንጂ በፋሲካ ሳምንት የመጀመሪያው ቀን ሕዝቡ ያሰማ የነበረው 'ሆሣዕና ጩኸት አንድ የሆነ ትንቢታዊ ድባብ ነበረው::

የሚገባውን ሰው በጥንቃቄ ይመለከቱታል:: ከተራራው ግርጌ እስከ ጫፉ ባለው የመንገዱ ግራና ቀኝ ያለውን የሰዎች ሰልፍ በዓይነ ሕሊናችን ልንስል ከምንችልበት ወቅት ምናልባት ብዙም የራቅን አይለንም:: ኢየሱስ ከተራራው በመውረድ ላይ ሳለ ሕዝቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚሄድና ግርማ ባለው ሰልፍ ሆነው ከበስተኋላው እየተመሙ በቀጥታ ወደ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ይጓዛሉ::

### *4. የደቀ መዛሙርቱ አለማወቅ*

ዮሐ 12÷16-18

16ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሁሉ በመጀመሪያ
አላስተዋሉም፤ ስለ እርሱ የተጻፉትንና ለእርሱም
የተደረጉትን ልብ ያሉት ኢየሱስ ከከበረ በኋላ ነበር::
17አልዓዛርን ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን ባስነሳበት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩ
ሰዎች ይህን ታምራዊ ምልክት ማድረጉን ለሰው ሲቀበሉት ወጡ::

ደቀ መዛሙርቱ እንደ ሕዝበ ሁሉ ተመሳሳይ በሆኑ የተሳሳቱ ምክንያቶች ደስ ተሰኝተው ነበር:: እነርሱም በሕዝቡ ዘንድ ስለ መሲሑ ተስፋፍቶ የነበረውን የተሳሳተ ግንዛቤ ተጋሩ:: እንዲያውም ኢየሱስ እስከሚከብርበት (ማለትም እስካረገበት ጊዜ) ይህን ጉዳይ አጥርተው ማየት አልቻሉም:: የዚህ ክንውን ውበቱ ከሚያመራበት አቅጣጫ ምድራዊው መንግሥት) ሳይሆን የመጣበት አቅጣጫ (የበሉይ ኪዳን ትንቢቶች) ነው::

### *5. ፈሪሳውያን*

ሉቃ 19÷39-40

39በሕዝቡ መካከል የነበሩ አንዳንድ
ፈሪሳውያንም ኢየሱስን «መምህር ሆይ፤ ደቀ
መዛሙርትህን ገሥጻቸው እንጂ» አሉት::
40እርሱም፤ አላቸኋለሁ፤ «እነርሱ ዝም ቢሉ፤
ድንጋዮች ይጮኻሉ» አላቸው::



ዮሐ 12÷19

19ስለዚህም ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው፣
«እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል አያችሁ! ዓለሙ ሁሉ
ግልብጥ ብሎ ተከትሎታል» ተባባሉ::

ፈሪሳውያን በዚህ ጉዳይ ትኩረታቸው ይሳባል:: የሕዝቡን ድርጊትና የንግግራቸውንም አንድምታ ይረዳሉ:: ኢየሱስ ዙፋን ላይ የመውጣት እንቅስቃሴ የሚያደርግ (ድራማ እንደሚያሳይ) ይመስላል:: ሕዝቡም በዚህ እንቅስቃሴው ይተባበሩት ነበር:: በፈረሳውያን አስተሳሰብ የደቀ መዛርቱ ደስታ ከመጠን አልፎ ወደ ገሃድ አብዮት ከመፈንዳቱ በፊት እንዲያቆሙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት::

እንኳን ሊያስቆማቸው ኢየሱስ እንዲያውም:- «ምስጋና ማቅረባቸው አግባብነት ያለውና ሊቀር የማይገባው ነው:: እነርሱ ቢያቆሙ እንኳ ድንጋዮች ማመስገን ይጀምራሉ» አለ:: በሕዝቡ ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርግባቸው ኢየሱስን ጠየቁት:: እርሱ ግን ከነሱ ጋር ግንባር ለግንባር ተፋጥጦ ክንዳቸውን እንዲያነሱ ይገዳደራቸው ነበር:: ያን ዕለት ብርታት አጥተው ነበር:: አንዳች ነገር ማድረግ የሚያስችላቸው ከሕዝቡ ዘንድ የቀረበ አቤቱታም ሆነ ሕጋዊ ሥልክጣን ስላልነበራቸው ዝም ብለው መቆምና ማየት ነበረባቸው:: ለጠብ የሚጋብዘው ሁኔታ ተመቻችቷል እነርሱም ለረጅም ጊዜ ቻል ብለው አይቆዩም::

### *6. ኢየሱስ ለኢየሩሌም አለቀሰ*

ሉቃ 19÷41-44

41ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ
ከተማዋን አይቶ አለቀሰላት፤ 42እንዲህ አለ፤ «ሰላምሽ
የሚሆነውን ምነው አንቺ ዛሬ በተረዳሽ ኖሮ፣ አሁን ግን
ከዐይንሽ ተሰውሯል፤ 43ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ቅጥር
ሠርተው ከአየቀጣጫውም ከበው አንቺን
የሚያስጨንቁበት ጊዜ ይመጣልና፤ 44አንቺንና በቅጥርሽ

ነጥ የሚኖሩትንም ልጆችሽን ከዐፈር ይደባልቃሉ፣
ጋይም በድንጋይ ላይ አይተዉም፤ የመጐብኛሽን ጊዜ
ዐቀሽምና።»

ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ድል በማድረጉ ደስታችንን ለመግለፅ ፈተናለን:: ኢየሱስ ግን አለቀሰ እንጂ አልፎከረም:: ቃሉ (*አለቀሰ* ጊለው) የሚገልጸው መንሰቅሰቅን ነው:: የእርሱ ፍላጐት ክርክርን ርታት ሳይሆን፣ ሕዝቡን መማረክ ነበር:: ላይ ላዩን ሲታይ ይህን ላጐቱን ያሳካ ይመስላል:: ሆኖም የሕዝቡን ልብ ያውቃል:: በአምስት ናት ውስጥ እነዚያ *ሆሣዕና* እያሉ ሲጮሁ የነበሩ ሰዎች ማሬያቸውን ቀይረው *ስቀለው* ይላሉ:: አሁን ነፃ-አውጪ ንጉሣችን ው ብለው ራሳቸውን ለኢየሱስ ሰጥተዋል:: እንደ ዓመፀኛ ተቆጥሮ ሚታሰርበት ጊዜ አደገኛ ሁከት ቀስቃሽ እንደሆነ በመቍጠር ሳልፈው ይሰጡታል::

በከተማዪቱ ከፍ ባለ ስፍራ ቆሞ ምናልባትም ወደ ቤተ ቅደሱ ቅጥረ ግቢ በቀጥታ እየተመለከተ ለከተማይቱ ሰላም ማልዳል:: ሁከት ተቀስቅሶ ደም ከፈሰሰ በኋላ በስተመጨረሻ ሚመጣውን የፖለቲካ ሰላም ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምታገኘው ሰላም ነበር የማለደው:: የኢየሱስ የመጨረሻ ግብ ይህ በር፤ ሆኖም ለዚህ ጉዳይ የሕዝቡ ዓይን ታውሮ ነበር:: ኢየሱስ ነርሱ የሚፈልጉት ዓይነት መሲሕ ለመሆን እምቢ በሚልበት ጊዜ ገድሉታል:: ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር በቀል ሙሉ በሙሉ ከተማይቱ ግንቦች ላይ ይወድቃል:: በአርባ ዓመታት ውስጥ ማውያን ድንጋይ በድንጋይ ላይ እስከማይነባበር ድረስ ጨርሰው ፈራርሷታል:: ከሦስት ቀናት በኋላ እዚሁ ስፍራ ላይ ሆኖ (ማቴ 24፤ ግር 13፤ ሉቃ 21) ይህንኑ ጉዳይ በዝርዝር ይገልጸዋል:: ለጊዜው ግን ህ ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ እንባውን እንዲያፈስ አድርጐታል::



ከመካከላቸው ልብ የሚል ሰው ካለ በእርግጥ ይህ ነገር በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ ትልቅ ግራ መጋባት የሚፈጥር ነው::

## 7. ወደ ቤተ መቅደስ መግባት

[10]ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜም ከተማዋ በመላ፣
«ይህ ማነው?» በማለት ታወከች::
ማቴ 21፥10-16
[11]ሕዝቡም «ይህ ከገሊላ
ከምትገኘው ከናዝሬት የመጣው ነቢዩ ኢየሱስ ነው»
አሉ::

[14]በቤተ መቅደስም ውስጥ ዓይነ ስውሮችና ሽባዎች ወደ እርሱ ቀረቡ፤
እርሱም ፈወሳቸው:: [15]ነገር ግን የካህናት አለቆችና የኦሪት ሕግ መምህራን
ያደረጋቸውን ታምራትና «ሆሣዕና፤ ለዳዊት ልጅ» እያሉ የሚጮኹትን ሕፃናት ባዩ
ጊዜ በቍጣ ተሞሉ::
[16]እነርሱም፣ «እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን ትሰማለህ» አሉት:: ኢየሱስም፣
«አዎን እሰማለሁ፤ እንዲህ የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?» «ከልጆችና ጡት
ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ ምስጋና አዘጋጀህ::ʺ»

ʺ16 መዝሙር 8፥2

[11]ኢየሱስም ኢየሩሳሌም ደረሰ፤ ከዚያም ወደ
ቤተ መቅደስ ገባ፤ በዙሪያው ያለውንም ሁሉ
ተመለከተ፤ ቀኑም ስለመሸ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ወደ
ቢታንያ ወጣ::
ማር 11፥11
ከማቴ 21፥17 ጋር

ኢየሱስ በከተማይቱ በር ባለፈበት ጊዜ ሰው ሁሉ ስለሱ ያንሾካሹክ ነበር:: አዲሱ መደበኛ ትርጉም:- «ከተማዋ በመላ ... ታወከች» በማለት ለቍ 10 የሰጠው ትርጉም እንደሚገባ የሚገልጸው አይመስልም:: *ታወከች* (ተናወጠች) የሚለው ቃል በሌሎች

ስፍራዎች የመሬት መንቀጥቀጥን ለመግለጽ (ማቴ 27÷51፤ ራእ 6÷13) የዋለ ቃል ነው። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችና ለፋሲካ በዓል የመጡ ተሳላሚዎችና በሰልፉ ግንባር ቀደም የነበሩት፣ «ይህ ማነው?» በማለት ይጠይቁ ነበር። ይጠብቁት የነበረውና የጠረጠሩት መልስ፡- «ከናዝሬት የመጣው ኢየሱስ ነው» የሚል ነው።

የከተማዋ በሽተኞች እንዲገቡ እስከሚፈቀድላቸው እስከ ቤተ መቅደሱ የውጭ ደጃፍ ድረስ ዘልቀው ነበር። በሽተኞችና ሽባዎች ቤተ መቅደሱ ደጃፍ ላይ ተቀምጠው ወደ ውስጥ ከሚገቡ ሰዎች ምፅዋት መለመናቸው የተለመደ ነበር (ከሐዋ ሥራ 3÷2 ጋር ያነ)። እንደምንም ብለው በሚጋፉት ሰዎች መሀል ተሹለክልከው ኢየሱስ ዘንድ ይደርሳሉ። እስካሁን ምንም አስደናቂ ነገር እንዳልተከናወነ ሁሉ ኢየሱስ ገና ይፈውሳቸው ነበር። ሕፃናቱ እንኳ የወላጆቻቸውን ምስጋና ለማስተጋባት የመዘምራን ቡድን አቋቁመው ነበር።

ቀደም ሲል ሲያጠምዱት ዳር ዳር ሲሉ የነበሩት አሁን በሰዱቃውያን ይበልጥ ተበረታቱ። ኢየሱስ በቤተ መቅደስ የነበራቸውን ግዛት እየወሰደ አስደናቂ ነገሮችን ማድረጉ እውነት ቢሆንም፣ ለቆላቸው እንዲወጣ መጠየቅ ነበረባቸው! የኢየሱስን የፈውስ አገልግሎት የሃይማኖት መሪዎች መቃወማቸው እንግዳ ነገር ይመስል ይሆናል። ይሁን እንጂ ፈውስ ከመሲሕነት ማስረጃዎች (ከኢሳ 35÷46 ጋር ያነ) አንዱ እንደሆነ መረዳት ይገባናል። እንዲያውም ስለ አገልግሎቱ እንዲጠይቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ መልእክተኞችን በላከ ጊዜ ረዘም ያለ የሙግት ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ኢየሱስ «የማደርገውን ተመልከቱ» አለ። እነዚህ መሲሕ የሚፈጽማቸው አስደናቂ ፈውሶች ናቸው» ነበር ያለው (ማቴ 11÷2-6)።

ኢየሱስ፡- «አላነበባችሁምን?!» በማለት መልስ ሰጠ። ይህ አባባል ሰባኪ የሆነውን ሰው ዮሐንስ 3÷16ን አታውቅም ብሎ



እንደመክሰስ ነው። መዝሙር 8÷2ን መሠረት በማድረግ በሕፃናቱ ለሚቀርበው ምስጋና ይበልጥ ንቁ ሊሆኑ ይገባቸው ነበር። ይህ ምንባብ በጣም ዝነኛ ስለሆነ ሳይሆን ይህ ሁኔታ ግን በጣም ግልጽ ነው። እንዴት የሚያስገርም ንጽጽር! በአንድ በኩል የሕዝቡን ምስጋና እንመለከታን፣ ሕዝቡ ይፈወሳል ልጆችም እግዚአብሔርን ያመልካሉ። በሌላ በኩል ከቊጥጥራቸው ውጪ ስለሆነ የሃይማኖት መሪዎቹ ይህ ሁኔታ እንዲገታ ይፈልጋሉ።

ይህን መሳዩ ግብዝነት ከዚህ መለስተኛ ተግሳጽ ይበልጥ ሊቀርብለት ይገባል። ሆኖም እስከሚቀጥለው ቀን መጠበቅ ይኖርበታል። ከነበረው ቀትር በኋላ ጊዜ በርካታውን በድል ለመግቢያ አከባበርና ለፈውስ አገልግሎት አውሎታል። ችግሮቹን እንዲሁ ተቋቁሟቸዋል ከቅርብ ተከታዮቹ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ተመልሶ መኝታው ላይ ያሰላስለዋል። ትልቁ ፍንዳታ የሚሆነው ግን ሰኞ ዕለት ነው!

**§ 129ሀ**
**የበለሲቱ ዛፍ መረገም**
**(ማቴ 21÷18-19፤ ማር 11÷12-14**

እዚህ ነጥብ ላይ ማቴዎስ ትረካውን ሰብሰብ ያደርገዋል። ይህን ማድረጉ ሁለት ውጤቶች አሉት። በመጀመሪያ የቤተ መቅደሱ መንጻት እሁድ ከቀርት በኋላ የተከናወነ ሲመስል ማርቆስ ግን ይህ የተከናወነው ሰኞ ዕለት እንደሆነ ያብራራል። ሁለተኛ ሁኔታው ከበለሲቱ ዛፍ መረገም ጋር እንደሚመሳሰልና ከዚህም የተገኘው ትምህርት ያኔ እንደ ተፈጸመ ዓይነት አድርጎታል። እንደገና ማርቆስ በሁለቱ ክንውኖች መካከል የሃያ አራት ሰዓት ልዩነት እንደነበረ ገልጿል።

ማርቆስ የጠቀሰው የሃያ አራት ሰዓት ቆይታ የጊዜውን ቅደም ተከተል ለመረዳት ብቻ ሳይሆን በምንባቡ ለተገለጸው ሥነ መለኮትም ጭምር ዋጋ አለው። ታስተውላላችሀ? ኢየሱስ የበለሲቱን ዛፍ

የረገማት ሰኞ ዕለት ነበር:: እስከ ማክሰኞ ደቀ መዛሙርቱ ይህን አላስተዋሉም:: በእነዚህ ሁለት ሁነቶች መካከል ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ያነጻል:: በመሆኑም የጠወለገችው የበለስ ዛፍ የእስራኤል የወደፊት ገጽታ ምሳሌ እንደነበረች እንረዳለን:: በተውኔት የቀረበ ተምሳሌት ዓይነት ነው::

**ማር 11÷12-14 ከማቴ 21÷18-19 ጋር**

12በማግሥቱ (ማስዳ[ማቴ]) ከቢታንያ ሲወጡ
(ወደ ከተማ በመመለስ ላይ ሳለ[ማቴ]) ኢየሱስ ተራበ::
13ቅጠል ያላት የበለስ ዛፍ (በመንገድ ዳር[ማቴ]) ከሩቅ
አየ፤ ምናልባት ፍሬ ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ ወደ
እርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና
ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም:: 14ከዚያም ዛፏን
«ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ»
አላት:: ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲናገር ሰሙ:: (የበለሷ
ዛፍ ወዲያውኑ ደረቀች)

ሰኞ ማለዳ በቤተ መቅደስ ያላጠናቀቀውን አንድ ተግባር ለማጠናቀቅ ኢየሱስ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ:: ኢየሱስ እስከዚህ ወቅት ተርቦ ሊሆን አይችልም:: በተለምዶ አይሁድ በቀን ሁለት ጊዜ ነው የሚመገቡት፤ ጥዋት 4:00 እንዲሁም ምሽት ከ12:00 እስከ 1:00:: ለቁርስ በጣም የቀደመ ጊዜ ነበር:: ምናልባት ቀደም ባለው ቀን በነበረው ደስታ ምክንያት ኢየሱስ ራቱን ,በላ ቀርቷል:: የሚሠራው ሥራ ኖሮት ምግብ ሳይበላ ሲቀር ያ የመጀመሪያው አልበረም (ማር 3÷20፤ 6÷31)::

ከፊት ለፊቱ ከመንገዱ በስተዳር በኩል ቅጠሏ ያጀፈጀፈ አንዲት በለስ ተመለከተ:: ጊዜው እንኳ የበለስ ወራት አልነበረም:: ይህ አስተያየት ነጥቡን የሳተ ነው:: አረንጓዴ ቅጠሎቿ በዛፊቱ ላይ ፍሬ



እንደሚኖር የሚያበስሩ ነበሩ:: ሆኖም ፍሬ አልነበረም:: የባሰው ነገር እንቡጡ አሁን ፍሬ ከሌለው ኋላ የበሰለ በለስ አይኖርም::

ኢየሱስ መለኮታዊ ኃይሉን በመጠቀም በግልፍተኛነት[12] ግዑዝ የሆነን ነገር በማጥፋቱ ከፉኛ ትችት ቀርቦበታል:: ይህም ነጥቡን የሳተ ነገር ነው:: ኢየሱስ በአታላይዋ ዛፍ ላይ በቀሉን በመወጣት ላይ አልነበረም:: በተለይ በቤተ መቅደሱ ያደርግ ከነበረው ድርጊት አንጻር፣ ይህን አጋጣሚ ለደቀ መዛሙርቱ ዋጋ ያለው ትምህርት ለማስተማሪያነት እየተጠቀመበት ነበር:: ለኢየሱስ ከዕዋቆች (ግዑዝ ነገሮች) ይልቅ ሰዎች የላቀ ዋጋ አላቸው:: ከግዑዝ ነገሮች ይልቅ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ተግባር ከፍ ያለ ግምት ነበረው:: በጌርጌሴኖን የ2000 እርያዎች ኪሣራ በደረሰ ወቅትም ይህንኑ መማር ይገባ ነበር:: ከዚህም ባሻገር ዛፊቱ ፍሬያማ አልነበረችም:: ማከናወን የሚገባትን ተግባር ሳታከናውን በእግዚአብሔር መልካም ምድር ላይ ስፍራ እያጣበበች ነው:: ምስጢራዊ ከሆነው የኢየሱስ ቍጣ የተነሣ ትልቅ ግምት የሰጣት ባልደረባውን በማጣቱ ተፈጥሮ እንባውን ያፈስ ነበር ብሎ በዓይነ ሕሊና ማሰብ ሞኝነት ነው:: እርባና የሌላት ዛፍ ነበረች::

ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ መልክ ነበራት ግን ፍሬ አላፈራችም:: ተገቢውን ፍሬ ያላፈራውን ቤተ መቅደስ ለመርገም እየተዘጋጀ እንደነበረ ሁሉ ይህችንም ፍሬያማ ያልሆነች ዛፍ ረገማት:: «ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ» ባለ ጊዜ የዚያች ምስኪን ዛፍ መጨረሻ እንደዚያ ቅጽበታዊና የከፋ ይሆናል ብሎ ማንም

12 T.W. Manson, "The Cleansing of the Temple." *BJRL* 33 (1951) በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 259 ውስጥ «እልሁን ለመወጣት ሲል ስላባከነው ተዓምራዊ ኃይል የተነገረ ታሪክ ሲሆን (ምስኪኗን ዛፍ እንድትከስም ወይም እንድትጠወልግ ለማድረግ የዋለው ልዕለ - ተፈጥሮዊ ኃይል ጠቃሚ በሆነ መንገድ በለሲቱ ያለ ወቅቷ ፍሬዎችን እንድታንዠረግግ ለማድረግ ሊውል ይችል ነበር)፣ ጉዳዩ ሲታይ ለማመን የሚያስቸግር ሆኖ ቀርቧል::»

አልጠበቀም:: ማቴዎስ ወዲያው ደረቀች ይላል:: ከሃያ አራት ሰዓት በኋላ በድጋሚ በዚሁ ስፍራ ሲያልፉ ከሥርዋ ጀምሮ እንደ ደረቀች (ማር 11፥20) ይገልጻል:: ይህ በማንኛውም መጽሐፍ «ቅጽበታዊ» የሚባል ነገር ነው!

**§ 129ለ ለሁለተኛ ጊዜ የቤተ መቅደሱ መንጻት (ማቴ 21፥12-13፤ ማር 11፥15-18፤ ሉቃ 19፥45-48 ከ § 31 ጋር ያነ**

ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ይህን የማንጻት ተግባር የሚያቀርቡት በኢየሱስ የአገልግሎት ማጠቃለያ ላይ እንደሆነ አድርገው ነው:: ዮሐንስ ግን በኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ ላይ እንደሆነ አድርጎ ያቀርበዋል:: የወንጌላት ጸሐፊዎች ሁነቶችን አንዳንድ ጊዜ ከጊዜ ቅደም ተከተል ይልቅ በርእስ ጉዳይ ሥርዓት እንደሚያስቀምጡ ማንም አይክድም:: ነገር ግን ተነጻጻሪ ወንጌላት ከተጻፉ በኋላ የጻፈው ዮሐንስ ይህን ያህል መሠረታዊ ክለሳ ማድረጉ የተሳሳተ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ስለሆነም ኢየሱስ አንድ ጊዜ በአገልግሎቱ መጀመሪያ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአገልግሎቱ ማጠቃለያ ላይ ሁለት ጊዜ ቤተ መቅደሱን አንጽቶ ሊሆን ይችላል (ከMorris ገጽ 288ና ተከታቹን ገጾች ይመ)::

**ማር 11፥15-17 ማቴ 21፥12 ጋር**

15ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ፤ ከዚያም ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ፣ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ያስወጣ ጀመር:: የገንዘብ መንዛሪዎችን ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ ገለባበጠ:: 16ማንም ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ ከለከለ:: 17ሲያስተምራቸውም «*ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ይ[illegible]»[ሀ] ተብሎ አልተጻፈምን እናንት ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት»[ለ] አላቸው::

*[ሀ]17 ኢሳይያስ 56፥7* *[ለ]17 ኤር 7፥11*



ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም በሚገባበት ጊዜ ኢየሱስ በመጀመሪያ የሚያልፍበት የመጀመሪያው በር በቀጥታ ወደ ቤተ መቅደሱ ደጃፍ ማለትም ወደ አሕዛብ ቅጥር የሚመራ ነው:: በዚያ የተመለከተው ግርግር ነበር:: ርግቦች፣ በጎች እንዲሁም በሬዎች ነበሩ (ዮሐ 2፥14):: ሳጥኖች፣ ቅርጫቶች እንዲሁም የሻጭና የገዢ ጭቅጭቅ ይሰማል:: የሮማውያን ገንዘብ ለቤተ መቅደስ ግብር[13] ለመክፈል ወደሚጠየቀው የአይሁድ መገበያያ ገንዘብ የሚለወጥበት ቢሮ ነበር:: ሁከት የሚላበትና የሚረብሽ ሁኔታ ነበር::

በመጀመሪያው የቤተ መቅደስ ማንጻት ወቅት ኢየሱስ ከቁርጥራጭ ገመዶች ጅራፍ ገመደ:: በዚህ ወቅት ግን ጅራፍ ማበጀት አለማበጀቱ አልተነገረንም:: የገንዘብ ለዋጮችን ገበታ ለመገልበጥ ጉልበት ይጠይቃል:: ማርቆስ ይህን አስገራሚ ጭምጭምታ አክሎበታል:- ኢየሱስ «ማንም ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ ከለከለ»:: ነጋዴዎች የአሕዛብን ቅጥር በምሥራቅ በኩል ወደ ደብረ ዘይት በሚያመራው መንገድ ለመሄድ እንደ አቋራጭ አድርገው ይጠቀሙበት ነበር (Josephus, *Against Apion* 2:108 and *M. Ber.* 9.5). የኢየሱስ በቀል በሚሸጡት ላይ ብቻ ሳይሆን በሚገዙትም ላይ ነበር::

የሚገርም ትዕይንት ነው:: ደርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ በመንገድ ላይ የተበተኑ ሳንቲሞቻቸውን ለመልቀም ነጋዴዎች በእንብርክካቸው ይሄዱ ነበር:: በጎች፣ በሬዎች፣ ፍየሎችና ርግቦች በተፈጠረው ሁካታ ተደናግጠው ይበረግጋሉ:: ለሚበረግጉት እንስሶችመንገድ ለመስጠት ሲሞክሩ ሰዎች እርስ በርሳቸው ይገፋፋሉ:: ነግደው እንዳያተርፉ በሥራቸው ጣልቃ ስለገባው ነገር እምብዛም ሊያደርጉት የሚችሉት

[13] J. Neusner, "Money-Changers in the Temple: The Mishnah's Explanation," *NTS* 35 (1989): 287-290.

ነገር አልነበረም:: በለተይ ቀደም ብሎ ከተካሄደው አስደናቂ ሰልፍ በኋላ ሕዝቡ ኢየሱስን ይደግፋል፣ በገሃድ በቤተ መቅደስ ይካሄድ የነበረውን ሙስና ደግሞ ጠልተውታል:: ሰዱቃውያን በጉዳዩ ጣልቃ የሚገቡ ከሆነ ሕዝቡ ኢየሱስን በመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው አይቀርም (ማር 11÷18):: ከዚህም ባሻገር የሮማውያን ወታደሮች እጆቻቸውን በሰይፎቻቸው እጀታ ላይ አድርገው በተጠንቀቅ ይጠብቁ ነበር:: ጠብ ከተነሣ ሮማውያን በፍጥነት ሊያቆሙት ይችላሉ፤ እንደዚያ ለማድረግ ነው በጉጉት የሚጠባበቁት::

ለማንኛውም ነጥቡ ቤቱ ቆሽሾ እስከሚያንፀባርቅ እንዲጸዳ መፈለጉ አይደለም:: እነዚያ ምስኪን ጸሎተኛ አሕዛብ የሚጸልዩበት ጸጥ ያለ ስፍራ አለማግኘታቸውም አልነበረም:: ኢየሱስ ቅር የተሰኘበት (ትችቱን የገለጸበት) ሁለት ጉዳይ ነበር:: በመጀመሪያ ኢሳይያስ 56÷7ን መሠረት በማድረግ ቤተ መቅደሱ ለሰዎች ሁሉ ክፍት መሆን እንዳለበት ተናገረ:: የኢሳይያስ 56÷7 ዓውድ መሲሑ ከሁሉም ወገን የሆኑ ሕዝቦች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እንደሚያሰባስባቸው ይናገራል:: ከዚህም የተነሣ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት የሚደርስባቸው «ስደት» እንዲያበቃ ያደርጋል:: በሁለተኛ ደረጃ ኤርምያስ 7÷11ን መሠረት በማድረግ የወቅቱን መሪዎች (ከኤር 7÷1-16 ጋር ያነ) ያስፈራራቸዋል:: መሪዎቹ እንደ ኤርምያስ ዘመን ቤተ መቅደሱን ይቆጣጠሩ ስለነበር ኃጢአትን በማድረግ ተደላድለው ተቀምጠዋል:: ይሁን እንጂ መንገዳቸውን ካላቃኑ ቤተ መቅደሱ እንደሚፈርስ እግዚአብሔር ተናግሯል:: ስለሆነም እንደዚያ በምሬት ለኢየሱስ መልስ መስጠታቸው አያስገርምም:: ያልተጠበቀ አልነበረም:: ሚልክያስም (3÷1-13) ይህ እንደሚፈጸም ተንብይዋል::



**ማር 11÷18**
**ከሉቃ 19÷48 ጋር**

18 የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም ይህን ሲሰሙ እንዴት እንደሚያጠፉት መንገድ ይፈልጉ ጀመር፤ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ በመገረማቸው (ይከታተሉ ስለ ነበር[ሉቃ]) ፈርተውታልና::

ጌታ ኢየሱስ ሕዝቡን ማርኮ እንደነበር ግልጽ ነው:: የሰዱቃውያን ወገን (ሊቀ ካህናት) እንዲሁም የፈሪሳውያን ወገን (የሕግ መምህራን) ሁለቱም ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር:: ከዚህም ባሻገር ለቤተ መቅደሶች በሚያደርጉት መልሶ ግንባታና ጥበቃ የአይሁዶችና የነገሥታት ስም ተከብሮ የሚቀይበት መንገድ በመሆኑ ሔሮድስ ሊወስድ ያለውን እርምጃ በግል ማንነቱ ላይ እንደ ተሰነዘረ ጥቃት ሳይቆጥረው አይቀርም::[14] ኢየሱስ በሕዝቡ ላይ አሳድሮት የነበረውን ገናናነት ፈርተውታል:: የሮም ባለሥልጣኖችም የቤተ መቅደሱን ገቢ በቅርብ ይቈጣጠሩ ስለነበር በግብር መልክ ገንዘብ ይቀነጣጥባሉ:: ስለሆነም የኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ማንጻት ከአይሁድ ድንበሮች ባሻገር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አንድምታዎች አሉት::[15] እነዚህ መሪዎች ኢየሱስ በናፍቆት የሚጠበቀው መሲሐቸው[16] ሊሆን እንደሚችል ከማሰብ ይልቅ በሥልጣናቸው ሊይዙት ስለሚችሉበት ስፍራ ይበልጥ

---

[14] H. Betz, "Jesus and the Purity of the Temple," *JBL* 116/3 (1997): 455-472.

[15] ከ J.M. Dawsey, "Confrontation in the Temple," *PRS* 11 (1984): 153-165 ጋር ያነ::

[16] በሊቀ ካህንነት የሚያገለግሉት ሹማምንት ትርፍ የሚያጋብሱ በመሆናቸው በሙስና ፍጹም ተበላሽተዋል:: በጆሴፈስ ዘገባ መሠረት ጂሰስ ቤን ገማልኤል የሊቀ ካህንነትን ሹመት በጉቦ ገዝቶ ነበር (*Ant* 20.213):: ከፍ ያለ ሹመት የነበራቸው አንዳንድ ካህናትም የማይገባቸውን አሥራት ሰርቀው ለመውሰድ ዝቅተኛ ሹመት የነበራቸውን ካህናት ይደበድቡ እንደነበረም ተናግሯል (*Ant* 28. 181 & 206-207):: ከዚህም ባሻገር ለመሥዋዕት የሚቀርበውን እንስሳ ዋጋ ሃያ አምስት እጥፍ በመጨመር ተሳላሚዎችን ያስከፍሉ ነበር:: ይህ አሠራራቸው በሕዝቡ እንዲፈሩና እንዲጠሉ አድርጓቸዋል (ከ C.A. Evans, "Jesus' Action in the Temple: Cleansing or Portent of Destruction?" *CBQ* 51 [1989]: 237-270 ጋር ያነ)::

ይጨነቁ እንደነበር በግልጽ ይታያል። ይህ ዕብሪታቸውና ራስ ወዳድነታቸው ወደ ከፋ ደረጃ እስኪያደርሳቸው ድረስ አሳውሯቸዋል።

**§ 130ሀ**
**አንዳንድ ግሪኮች ኢየሱስን ለማየት ፈለጉ**
**(ዮሐ 12፥20-36)**

ኢየሱስ ቤተ መቅደስ ማንጻቱን አጠናቋል። በተለይም በአሕዛብ ቅጥር ውስጥ የነበረውን ኮተታኮተት ጠራርጐ አስወጥቷል። ወደ ይሁዲነት የተመለሱት ተሳላሚዎች አሁን በሚገባ ለመጸለይ ይችላሉ። ኢየሱስ የእነርሱ ጀግና ነው። ስለሆነም ወደ ይሁዲነት ከተመለሱት ግሪኮች አንደኛው ወገን ኢየሱስን ለማነጋገር መፈለጉ አስደናቂ አልነበረም።

ዮሐ 12፥20-26

[20]ለስግደት ወደ በዓሉ ከወጡት መካከል
የግሪክ ሰዎችም ነበሩ። [21]እነርሱም በገሊላ ከምትገኘው
ከቤተ ሳይዳ ወደ ሆነው ሰው ወደ ፊልጶስ መጥተው፣
«ጌታው፤ እባክህን ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን»
አሉት። [22]ፊልጶስም ለእንድርያስ ሲነግረው ሄደ፤
እንድርያስና ፊልጶስም ለኢየሱስ ነገሩት።
[23]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓት
ደርሶአል፤ [24]እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች
ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። [25]ሕይወቱን የሚወድ
ያጣታል፤ በዚህ ዓለም ሕይወቱን የሚጠላ ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል።
[26]የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፤ እኔም ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፤
የሚገለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል።

እነዚያ በር ላይ ቆመው የነበሩት ግሪካውያን መሆናቸው ግልጽ ነው። ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት የሚያምኑበትን እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ነበር ሆኖም የግርዘት ሥርዓትን በመፈጸም ወደ ቃል ኪዳናዊ ኅብረት ገና አልገቡም። ወደ ፊልጶስ እንዲያተኩሩ ያደረጋቸው



አንድ ግልጽ ነገር አለ። ምናልባት ስሙ ይሆናል። ለነገሩ ከጅማሬው አንሥቶ እርሱና እንድርያስ ብቻ ነበሩ በግሪካዊ ስሞች ሲጠሩ የነበሩት። ፊልጶስ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣት ዝነኛ ወደ ነበረው ወደ እንድርያስ ወሰዳቸው (ከዮሐ 1፥41፤ 6፥8-9 ጋር ያን)።

እንድርያስ የጴጥሮስ ወንድም ነው። በዓሣ ማጥመድ ሥራ ከተሰማሩት ሦስት የቅርብ (ለኢየሱስ) ሰዎች ተነጥሎ የወጣው እርሱ ብቻ ነበር። ከእነርሱ ቀጥሎ ምናልባት ለኢየሱስ ቅርብ የነበረው እርሱ ነው። ስለሆነም ፊልጶስ ግሪኮቹን ወደ እንድርያስ ማምጣቱ አግባብ ነበር። ወደ ኢየሱስ አጅቦ በመውሰድ ከፍተኛ ውጤት ያስገኛል።

እንድርያስ እነዚያ ግሪካውያን ሊያዩት እንደሚፈልጉ ለኢየሱስ ነግሮታል፣ በጥያቄአቸው መሠረት አይተውት እንደ ሆነ ግን አናውቅም። የተሰጠን (የተገለጸልን) ነገር ቢኖር ኢየሱስ *ለእነርሱ* የሰጣቸው ምላሽ ነበር። ይሄ *ለእነርሱ* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፊልጶስና እንድርያስን ነው ወይስ የግሪኮችን ቡድን? ትርጉሙ ምንም ይሁን ምን ኢየሱስን ከበው የነበሩ አይሁድ የሰጠውን መልስ እንዳዳመጡ እናውቃለን (ቊ 29)።

ይህ ምላሽ (ኢየሱስ የሰጠው) ከግሪካውያን ጥያቄ ጋር ምንም የሚዛመድ አይመስልም። ነገር ግን በትክክል ሊሰሙ የሚገባቸው ነገር ነበር። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን መሆን ፈልገው ነበር፤ ደግሞም ይሆናሉ። ወደዚያም (ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ወገንነት) የሚካተቱት ወደ ይሁዲነት ስለተለወጡ ሳይሆን ኢየሱስ ለኃጢአታቸው ስለሞተላቸው ነው።

ባዕድ ዜጎች ኢየሱስን እንደሚፈልጉ ማወቃችን አያስደንቀንም። እንዲያውም የመቶ አለቃው (§ 55) እንዲሁም ሲሮ ፊኒቃዊቷ ሴት (§ 78) ቀደም ሲል ኢየሱስን ይከተሉ ነበር። ይህ ብቅ ያለው ቡድን ግን የዚህ መንገድ መጨረሻ ከፊት ለፊት ሲገለጥ እንዳለ ግልጽ

ምልክት ነው:: ኢየሱስ ይህን በአጭሩ ግልጽ ያደርግና እንከተልሃለን ላሉት የተመረጡ ጥቂት ሰዎች ማስጠንቀቂያዎችን በመልሱ ውስጥ ያካትታል::

የኢየሱስ መገደል የደቀ መዛሙርቱን መላ ሕይወት የሚያናጋ ነው:: ስለሆነም የኢየሱስ መሞት ልክ እንደ ስንዴ ቅንጣት መሞት አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ አለባቸው:: የስንዴ ዘር መሬት ውስጥ ካልተቀበረ የስንዴ ምርት አይኖርም:: እንደዚሁም ኢየሱስ ካልሞተና ካልተቀበረ ትንሣኤ፣ ቤተ ክርስቲያን የአሕዛብም (ወደ እግዚአብሔር ወገንነት) መካተት አይኖርም (ከኢሳ 53÷10፤ ሉቃ 9÷23-26፤ ሮሜ 3÷23-25፤ 5÷12-21 ጋር ያነ):: በኢየሱስ ላይ የሚሆነው በደቀ መዛሙርቱም ላይ ይሆናል:: እነርሱም መሞት ይኖርባቸዋል (ከማቴ 10÷37-39፤ 16÷24-26፤ ማር 8÷34-38፤ ሉቃ 9÷23-26፤ 14÷26፤ 17÷32:33 ጋር ያነ):: ለነገሩ እሱ ወደሚሄድበት እስካልሄዳችሁ ኢየሱስን መከተል አትችሉም::

**ዮሐ 12÷27-29**

[27]«አሁንስ ነፍሴ ተጨነቀች፤ ምን ልበል፧ አባት ሆይ፤ ከዚች ሰዓት ታድነኝ፧ የለም፤ ይሁን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት ነውና:: [28]አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው::»

ከዚያም፣ «አክብሬዋለሁ ደግሞም አከብረዋለሁ» የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ:: [29]በዚያ የነበሩት፣ ድምፁን የሰሙት አያሌ ሰዎች፣ «ነጐድጓድ ነው» አሉ፤ ሌሎች ደግሞ፣ «መልአክ ተናገረው» አሉ::

ኢየሱስ ሊመጣ ያለውን ያውቅ ስለነበረ ተረብሿል:: ኃዘኑን ቍ. 27 ውስጥ ገልጿል:: ይህን ጥቅስ ስንጽፍ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀማችን ልዩነት ያመጣል:: የመጀመሪያው ሐረግ በእርግጥ



ጥያቄ ነው:: ሁለተኛው ግን አዲሱ መደበኛ ትርጉም እንዳስቀመጠው ጥያቄ ከመሆን ይልቅ ገለጻ ሊሆን ይችላል:: ጥያቄ እንደሆነ አድርገን ከተረዳነው ኢየሱስ «በእርግጥ *አባት ሆይ ከዚህች ሰዓት አድነኝ* ማለት ይገባኛል? የመጣሁት ለዚህ ስለሆነ የለም፣ እንደዚህ ማለት አይገባኝም» እያለ ሲናገር ነው የምንሰማው:: ይሁን እንጂ፣ ገለጻ እንደሆነ አድርገን ከተረዳነው የዚያን ጊዜ ኢየሱስ «አባት ሆይ፤ ሊመጣ ያለውን አውቃሁ፣ እኔ ደግሞ በዚያ ውስጥ ማለፍ አልፈልግም ... ይሁን እንጂ ላከናውን የመጣሁት ይሄንኑ ነው፣ ስለዚህ እስቲ ልጋፈጠው (እንጋፈጠው)» ሲል እንሰማዋለን::

ይሄ ሁለተኛው አመለካከት የተሰጠውን ገለጻ ከጌቴሴማኒው ጸሎት (ከማቴ 26÷39፤ ማር 14÷36፤ ሉቃ 22÷42 ጋር ያነ) ጋር በጣም እንዲመሳሰል ያደርገዋል:: ኢየሱስ ቀራንዮ የሚኖረውን አስጨናቂ አንድምታ በመገንዘብ ላይ ነው:: በዚያ ውስጥ ለማለፍ አለመፈለጉ አስደናቂ አይደለም:: ይሁን እንጂ ይህን ያደረገው በግድየለሽነት ምኞት ተገፋፍቶ አልነበረም:: ከራሱ ምኞት ይልቅ ለአባቱ ክብር ይበልጥ ያስብ ነበር:: ማድረግ ባይኖርበትም እንኳ የአባቱን ዕቅድ በታማኝነት ይፈጽም ነበር::

የኢየሱስ ጸሎት ጥልቅ ነው! ጸሎቱ ለአባቱ ያለውን መስጠት በመግለጽና የኃዘን ስሜትን በሚቀሰቅስ ግላዊ አቀራረብ የታጀበ ነበር:: በዚህ ወሳኝ ወቅት እግዚአብሔር ልጁን በማክበር ጉልህ በሆነ ድምፅ አዎንታዊ መልስ ይሰጠዋል:: በኢየሱስ አገልግሎት ዘመን ጉላ ባለ ድምፅ እግዚአብሔር ሲናገር ይህ ሦስተኛውና የመጨረሻው ነው:: እነዚህ ወቅቶች እያንዳንዳቸው ወሳኝ ወቅቶች ነበሩ:: የጥምቀቱ ወቅት (ማር 1÷11)፣ መልኩ የተለወጠበት (በክብሩ የተገለጸበት) [ማር 9÷7] ደግሞም ወደ መስቀል ለመሄድ ቁርጠኛነቱን ያጠናከረበት ነው::

ከሕዝቡ ብዙዎቹ ድምፁን ስላልተረዱ የነጐድጓድ ድምፅ እንደሆነ ቈጥረውት ነበር (ከሐዋ ሥራ 9÷7፤ 22÷9 ጋር ያነ):: ሌሎቹ ደግሞ ድምፁ ከመልአክ እንደ መጣ እርግጠኞች ሆነው ነበር:: ሆኖም ኢየሱስ ጉላና ጥርት ባለ ሁኔታ ሰምቶታል «አክብሬዋለሁ፤ ደግሞም አከብረዋለሁ»:: ይህ መቼም ያለ ጥርጥር ከአብ ዘንድ የተላለፈ የእንኳን ደህና መጣህና ወቅታዊ የውሳኔ ማረጋገጫ ነው::

ዮሐ 12÷30-34

[30]ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ «ይህ ድምፅ
የመጣው ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ ነው፤ [31]ይህ
ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ አሁን ነው፤ የዚህም ዓለም
ገዥ አሁን ወደ ውጭ ይጣላል:: [32]እኔ ግን ከምድር ከፍ
ከፍ ባልሁ ጊዜ ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ::» [33]ይህን የተናገረው በምን ዓይነት
ሞት እንደሚሞት ለማመልከት ነበር:: [34]ሕዝቡም፣ «እኛስ ክርስቶስ፣ ለዘላለም
እንደሚኖር ከሕግ ሰምተናል፤ ታዲያ፣ 'የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት' እንዴት
ትላለህ? ይህስ 'የሰው ልጅ ማን ነው?'» አሉት::

እነዚህ አበባሎች ለኢየሱስ ትልቅ መጽናናት ቢሆኑለትም ከእርሱ ይልቅ አባባሎቹ በሕዝቡ ዘንድ ክፉኛ ይፈለጉ ነበር:: ከሦስትና ከአራት ቀናት በኋላ ኢየሱስ ሲሰቀል ይመለከታሉ:: እንደዚያ ዓይነቱ ቅጣት ደግሞ አስከፊ ወንጀል ለፈጸሙ ሰዎች የተመደበ ነበር:: የሰዎች የኃጢአት ፍርድ በእሱ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ኢየሱስ የሰውም የእግዚአብሔርም ቍጣ ተቀባይ ሊሆን ነው:: ለኢየሱስ ጥሩ ሆኖ አይታይም:: ለሚወዱት ሰይጣን እንዳሸነፈ ይመስላቸዋል (ከኢሳ 53÷10 ጋር ያን):: በትክክል ለመናገር ሁለቱም ቢሆኑ እውነት አይደሉም:: በእኛ ላይ ሊደርስ የሚገባውን ቅጣት በመቀበል ኢየሱስ በፈቃደኛነት ሞቷል::



ሕዝቡም እንኳ 'ወደ ላይ ከፍ ከፍ'[17] የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ስለ ሞቱ የተነገረ እንደሆነ ያውቁታል:: የመሲሑ ንጉሥነት ዘለቄታ ያለው መሆኑን ብቻ ያምኑ ነበር:: «የምትሞት ከሆነ መሲሕ መሆን እንዴት ትችላለህ» ብለው ይጠይቁ ነበር:: ከኢሳ 9÷7 (ከመዝ 110÷4፤ ሕዝ 37÷25፤ ዳን 7÷14 ጋር ያነ) አንጻር ሲታይ ያ መልካም ጥያቄ ነበር::

ዮሐ 12÷35-36

[35]ኢየሱስም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤
«ከእንግዲህ ለጥቂት ጊዜ ብርሃን አለላችሁ፤ ጨለማ
ሳይመጣባችሁ፣ ብርሃን ሳላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማ የሚመላለስ ወዴት
እንደሚሄድ አያውቅም:: [36]የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳላችሁ በዚህ ብርሃን
እመኑ::» ኢየሱስ ይህን ተናግሮ እንደ ጨረሰ ተለያቸው፤ ተሰወረባቸውም::

ኢየሱስ ብርሃን ነው (ለቍ 46 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ):: ኢየሱስን የሚቀበል ማንኛውም ሰው ሻማ እንደሚለኵስ ሁሉ ብርሃኑን ከዚያ ያገኛል:: ሆኖም ከጥቂት አጭር ቀናት በኋላ ጨለማ ይሰፍናል (ማለትም ስቅለት ይሆናል):: ኢየሱስ ከሞት ይነሣል፤ ነገር የሚገለጠው በአብዛኛው ለግለሰቦችና ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ይሆናል:: በእርግጥ ሰዎች በደቀ መዛሙርቱ በኩል ብርሃን ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ (ማለትም ኢየሱስን ይቀበላሉ) ነገር ግን እንደዚያ ማድረጉ ይበልጥ አስቸጋሪ ይሆናል:: ኢየሱስን የመከተያ ምርጡ ጊዜ እርሱ ፊት ለፊታቸው የቆመበት ጊዜ ነበር::

ይህን ከተናገረ በኋላ ወጣ ብሎ ከዝሕቡ ራሱን ሰወረ:: ይህ የሆነው ሰኞ ዕለት ከሆነ በዐሥራ ስድስት ሰዓቶች ውስጥ ከተሰወረበት ብቅ ይላል:: ሁኔታው እንደዚህ ከሆነ ይህ ቃል ኢየሱስ በአደባባይ

[17] «ከፍ ከፍ ማድረግ» የሚለው ግሥ (ሂፕሶ) በዮሐንስ ወንጌል በተለይ የተጠቀሰው የኢየሱስን ሞት ለማመልከት ነው (ዮሐ 3÷14፤ 8÷28፤ 12÷32:34)» ቴኒ (ገጽ 131)::

የተናገረው የመጨረሻ ቃል ነው:: ከዚህ ቀጥሎ በሕዝብ ፊት የሚቀርበው ዓርብ ጥዋት በጲላጦስ ፕራይቶርየም አዳራሽ ውስጥ ይሆናል:: ያኔ 'ስቀለው!' እያሉ ይጮኻሉ::

**§ 130ለ**
**ዕውር ዓይኖችና በድን ልቦች**
**ዮሐ 12÷37-50**

37 ኢየሱስ እነዚህን ታምራዊ ምልክቶች ሁሉ በፊታቸው ቢያደርግም እንኳ አሁንም አላመኑበትም፤ 38 ይኸውም ነቢዩ ኢሳይያስ «ጌታ ሆይ፤ ምስክርነታችንን ማን አመነ? የጌታ ክንድስ ለማን ተገለጠ?»[ሀ] ያለው ቃል እንዲፈጸም ነው::

39 ስለዚህ ማመን አልቻሉም፤ ይህም ኢሳይያስ በሌላ ቦታ እንዲህ ሲል እንደ ተናገረው ነው፤ 40 ዐይናቸውን አሳውሮአል፤ ልባቸውንም አደንድኖአል፤ ስለዚህ በዐይናቸው አያዩም፤ በልባቸውም አያስተውሉም፤ እንዳልፈውሳቸውም አይመለሱም::»[ለ]

41 ኢሳይያስ ይህን ያለው የኢየሱስን ክብር ስላየ ነው፤ ስለ እርሱም ተናገረ::

*[ሀ]38 ኢሳይያስ 53÷1* *[ለ]40 ኢሳይያስ 6÷10*

ይህ ክፍል መላውን የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ያጠቃልላል:: የተናገረውን ('ነኝ' ወይም 'አደርጋለሁ' ያለውን) አዘውትሮ ታምራትን በማድረግ አስመስክሯል (ዮሐ 2÷11:23፤ 3÷2፤ 4÷48:54፤ 6÷2:14:26፤ 7÷31፤ 9÷16፤ 10÷41፤ 11÷47፤ 12÷18፤ በተለይም 20÷30):: እነዚህ ሁሉ ቢከናወኑም እንኳ ሕዝቡ በአብዛኛው (ቍ 42) አላመኑም:: «... ማመናቸውን አይገልጡም ነበር» የሚለው ወደ ኢየሱስ ለመመለስ የነበራቸውን ቀጣይ እምቢተኛነት ይገልጻል:: ይህ የሆነው ታምራቶቹ እንከን ስላልነበራቸው አልነበረም:: ሙሉ በሙሉም የአይሁድ ስህተት አልነበረም:: እግዚአብሔር ልቦቻቸውን አጠንክሯል (ሮሜ 11÷25)::



የመጀመሪያው ምንባብ የተወሰደው ከኢሳይያስ 53÷1 ነው:: መጀመሪያ በተጻፈበት ዓውድ እንኳ ሲታይ ክፍሉ በመሲሑና በያህዌ መካከል ይደረግ የነበረ ንግግር ይመስላል:: ምንም እንኳ ኢየሱስ እውነትን እየተናገረ በታምራት ቢያረጋግጥም፣ አይሁድ ግን ለማመን አሻፈረኝ ብለዋል:: ሁተለኛው ምንባብ የተወሰደው ከኢሳይያስ 6÷10 ሲሆን የኢሳይያስ የስብከት ተልዕኮ የተነገረበት አንድ ክፍል ነው:: በአዲስ ኪዳንና በሁለት ሌሎች ስፍራዎችም ተጠቅሷል (ማቴ 13÷14-15 [ከማር 4÷12፤ ሉቃ 8÷10 ጋር ያነ] እንዲሁም የሐዋ ሥራ 28÷26-27):: በመጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሰባቸው በአራቱም ስፍራዎች የአይሁድን የልብ መደንደን አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: በማቴዎስ ወንጌል ለመደንደኑ ተጠያቂነቱ (ባለ ውለታ የተደረገው) የወደቀው በሰባኪው እግር ሥር ነው:: ይህም ማለት የሃይማኖት መሪዎች መልእክቱን እንዳይረዱ ኢየሱስ በምሳሌ ያስተምር ነበር ማለት ነው:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደግሞ ተጠያቂነቱ (ባለ ውለታ የተደረገው) የወደቀው በአዳማጩ እግር ሥር ነው:: ከእግዚአብሔር ለመጣው መልእክት ምላሽ ለመስጠት ዕድሉ ሁሉ ነበራቸው፤ ግን አልሰጡም:: እዚህ ላይ ደግሞ ተጠያቂነቱ (ባለ ውለታ የተደረገው) የወደቀው በእግዚአብሔር እግር ሥር ነው:: ይህም ማለት የልብ ድንዳኔው በእግዚአብሔርና በሰዎች በሂደት እየጨመረ በሄደ ትብብር የተከሰተ ነው:: ሰዎች ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር ሲሰጡ፣ እርሱ መንፈሱን ከእነርሱ ይወስድባቸዋል:: ስለሆነም ንስሐ ለመግባትና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ያላቸው ዕድል አነስተኛ ነው:: ይህ የሚያስደነግጥ ውል ነው (በማቴ 13÷14-15፣ §64 ለ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ)::

ቍ 41 ኢየሱስና ያህዌ እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ አስደናቂ መግለጫ ነው:: ኢሳይያስ የኢየሱስን ክብር እንዳየ ይናገራል:: ሆኖም

ወደ ኢሳይያስ 6፥1 መለስ ብሎ «... እግዚአብሔርን ከፍ ባለና በከበረ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፤ የልብሱም ዘርፍ ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር» ይላል። ምዕራፉ በሥጋ ከመገለጡ በፊት ለነበረው ክርስቶስ የሚቀርበውን ምስጋና መግለጹን ይቀጥላል። ዮሐንስ ኢየሱስን እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ አድርጐ ነበር የሚመለከተው።

ዮሐ 12፥42-46

[42]ይህም ቢሆን ከአለቆች መካከል እንኳ ሳይቀር ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ይሁን እንጂ ፈሪሳውያን ከምኵራብ እንዳያስወጧቸው ስለ ፈሩ ማመናቸውን አይገልጡም ነበር፤ [43]ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ከመመስገን ይልቅ በሰው መመስገንን ስለ ወደዱ ነው።

[44]ከዚያም ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤ «ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ ብቻ ሳይሆን በላከኝም ማመኑ ነው፤ [45]እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። [46]በእኔ የሚያምን በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።

ይህ አንቀጽ ስለ ኢየሱስ አገልግሎትና አስተምህሮ በአግባቡ የቀረበ ማጠቃለያ ነው። በመጀመሪያ በመሪዎቹ መካከል እንኳ ምንጊዜም ቅይጥ የሆነመሻል ነበር (ቍ 42)። አብዛኞቹ የተቃወሙት ቢሆንም ያልተቃወሙት ብዙዎች ነበሩ። ከምኵራብ እንዳይባረሩ በኢየሱስ ያመኑት ብዙውን ጊዜ ጸጥ ብለው (እንደበታቸውን ዘግተው) ይቀመጡ ነበር። እኛ ፈሪዎች እንላቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ ከምኵራብ በመባረራቸው ሥራቸውን፣ ቤተሰባቸውንና በኅብረተሰቡ ዘንድ የነበራቸውን ክብር ልንገነዘብ ይገባናል። ይህም ከፍተኛ ቅጣት ነው። ቍጥር 43 ግን ለእነርሱ ታላቅ ግምት የነበረው ምን እንደነበረ ይገልጽልናል፣ በሰዎች ዘንድ መመስገን። እርግጥም የሰዎችን ምስጋና መፈለግ አደገኛ ነገር ነው። ዋጋ ቢስና ብዙ እንድናደርግ የሚጠብቅብን፣ ብዙውን ጊዜም የእግዚአብሔርን ቃልና አደራረጉን እንድንክድ የሚያደርገን ነው።



በሁለተኛ ደረጃ ለአደባባይ አገልግሎቱ ልዩ እውቅና ያስገኙለትን ሁለት የግል ባሕርያት አጉልቶ አሳይቷል፦ (1) ከአብ ጋር ያለው የቅርብ ኅብረት (ከዮሐ 1፥14፤ 3፥35፤ 5፥18-23፤ 5፥26፤ 5፥36-37፤ 5፥45፤ 6፥27፤ 6፥32፤ 6፥45፤ 7፥16፤ 8፥16፤ 8፥18-19፤ 8፥27-28፤ 8፥41፤ 10፥30፤ 10፥38፤ 12፥49-13፥1 ጋር ያነ) እንዲሁም (2) ወደዚህ ዓለም ያመጣው ብርሃን (ማቴ 4፥16፤ ሉቃ 2፥32፤ ዮሐ 1፥4-5፤ 1፥7-9፤ 3፥19-21፤ 8፥12፤ 9፥5፤ 11፥9-10፤ 12፥35-36፤ 12፥46)። የእነዚህ የሁለቱም ባሕርያት አንድምታ ግልጽ ነው። በኢየሱስ በምናምንበት ጊዜ እኛም ከአብ ጋር የመቀራረብ ልምምድ ይኖራል ደግሞም በብርሃን እንመላለሳለን እንጂ ከዚያ በኋላ በጨለማ ውስጥ አይኖርም።

ዮሐ 12፥47-50

[47]ቃሌን ሰምቶ በማይፈጽመው ላይ የምፈርደው እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁምና። በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል፤ ምክንያቱም [49]እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤ ነገር ግን የላከኝ አብ ምን እንደምናገርና እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ። [50]የእርሱ ትእዛዝ ወደ ዘላለም ሕይወት እንደሚያደርስ ዐውቃለሁ፤ ስለዚህም የምለው ሁሉ አብ እንድናገረው የነገረኝን ብቻ ነው።

ይህ አንቀጽ ቀደም ብሎ ይነሱ ከነበሩ ጉዳዮች አንደኛውን ያነሳል ኢየሱስ የመጣው እኛ ላይ ለመፍረድ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ያለውን እውነት ሊነግረን ነው (ከዮሐ 5፥24:25-47፤ 8፥31:37:51፤ 14፥23-24 ጋር ያነ)። እንዲያውም የተናገራቸው ቃላት የራሱ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው (በ7፥16 ላይ የሰጠውን ማብራሪያ

ይመ ከ3÷11፤ 8÷26:28:38፤ 14÷10 ጋር ያነ):: ስለሆነም አንድ ሰው ኢየሱስን በሚቃወምበት (በምትቃወምበት) ጊዜ እሱ ወይም እሷ እግዚአብሔርን በመቃወም ላይ ናቸው:: ስለሆነም የሚፈርድባቸው ኢየሱስ ሳይሆን ራሳቸው የእግዚአብሔርን ቃል በመቃወማቸው ነው:: በግልባጩ ሲታይ የኢየሱስን ቃል መከተል ወደ ዘላለም ሕይወት ይመራል::

**§ 131**
**ከደረቀችው በለስ የተገኘ ትምህርት**
**(ማቴ 21÷19-22፤ ማር 11÷19-25 ሉቃ 21÷37-38)**

(ማር11)19«በመሸም ጊዜ ከከተማይቱ ወጥተው ሄዱ::

20በማግሥቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፉ፤ በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ:: 21ጴጥሮስ ነገሩ ትዝ ስለውና ኢየሱስን፣ «መምህር ሆይ፤ እነሆ፤ የረገምካት በለስ ደርቃለች» አለው:: 22ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ በእግዚአብሔር እመኑ::

(ማቴ21)21«እውነት እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ፣ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ተራራ፣ ከዚህ ተነቀለህ ባሕር ውስጥ ግባ ብትሉት እንኳ ይሆናል፤

(ማር11)24ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል:: 25እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማይ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ::

ማክሰኞ ጥዋት የሐዋርያቱ ቡድን ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም ተר ተጓዙ:: ከነስሯ የደረቀችውን የበለስ ዛፍ ለማስተዋል ጴጥሮስ የመጀመሪያው ነው:: እዚህ ላይ በቃል ያልተገለጸው የኢየሱስ ትምህርት እምነት የሌላቸውን የሃይማኖት መሪዎች አቋም ይመለከታል:: የማርቆስን የትረካ አወቃቀር መሠረት ካደረግን የበለሷ ዛፍ የአይሁድ መሪዎች ተምሳሊት እንደ ሆነች አድርገን



እንደመድማለን (ከኤር 8÷13፤ ሆሴ 9÷10፤ ሚክ 7÷1-6፤ ከናሆ 3÷12 ጋር ያነ):: አቀራረባቸው አሳሳች ነበር:: ከውጭ ሲታዩ ፍሬያማ ዛፍ ይመስላሉ፣ ትክክል የሆነውን ነገር ሁሉ ያደርጋሉ፣ ቀረብ ብለው ሲመለከቷቸው ግን እውነተኛ ፍሬ የለባቸውም:: እሁድ ከቀትር በኋላ (ሉቃ 19÷41-44) ቃል በቃል ስለ ተፈጸመው የኢየሩሳሌም ውድቀት እንደተነበየ ሁሉ፣ እዚህም ላይ በተምሳሊት ስለ በለሷ ዛፍ ተናገረ::

ኢየሱስ ገልጾ ያስተማረው ስለ ጸሎት ነው:: በበለሲቱ ላይ የጸለየው ጸሎት አስደናቂ ውጤት ያስገኝ ነበር:: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም በዚያው ኃይል መጸለይ ይችላሉ:: ነገር ግን ስለ ወጤታማ ጸሎት በሚናገረው በዚህ ምንባብ ዙሪያ ሁለት አንጻሮች አሉት እምነትና ይቅር ማለት (ከማቴ 6÷14-15፣ §54ረ):: በእግዚአብሔር ላይ እምነት ከሌለንና የበደሉንን ይቅር የማንል ከሆንን፣ ጸሎታችን ብርታት የጐደለው ይሆናል::

ይህ ማለት በእምነት ለሚጸልዩ ሁሉ ጸሎት የፈለግነውን ልንጽፍ የምንችልበት ነጭ ወረቀት ነው ማለት ነው? አይደለም የበለሲቱ ዛፍ መረገም የቤተ መቅደሱን መንጻት የሚያመለክት ሥዕል እንደሆነ አድርገን በመገመታችን ትክክል ከሆንን ኢየሱስ ይናገርባቸው የነበሩም ጸሎቶች በተለይ እምነት ስለ ጐደላት እስራኤል ነው ብለን እንገምት ይሆናል:: ምንም እንኳ የአይሁድ መሪዎች አለማመን የማይወጡት ተራራ ቢመስልም በእምነት ጸሎት ሊወገድ ይችላል::[18] ኢየሱስ ሃሳቡን ለመግለጽ እጁን እያወዛወዘ ወደ ደብረ ዘይት እንዲያውም ወደ ጽዮን ተራራ አመልክቶ ሊሆን ይችላል::

ይህንን ምንባብ ነጥለን ከወሰድነው እንደ ቅንጦት ለሚቈጠሩ ወይም ቀም ነገር ለሌላቸው አንዳንድ ነገሮች (ከማር 10÷35 ጋር ያነ)

---

[18] ኤም. ሙልቶን ስለ ጸሎት የተሰጠው ትምህርት ከቤተ መቅደሱ መረገም ጋር መያያዝ አለበት የሚለውን አቋም ይደግፋል:: "Jesus' Goal for Temple Tree: A Thematic Revisit of Matt 21:12-22," *JETS* 41/4 (1998): 561-572.

ልንጸልይ እንችላለን:: ከዚህ ጋር የሚነጻጸሩ ሌሎች ምንባቦች በጸሎታችን ዙሪያ አንዳንድ ድንበሮችን ያስቀምጣሉ:: ለምሳሌ ያህል ስንጸልይ:-

1. በእምነትና (ማቴ 21÷22) በመታዘዝ (1ዮሐ 3÷22)
2. በጽናት (ሉቃ 11÷9፤ 18÷1-6)
3. እንደ ኢየሱስ ፈቃድ (ማለትም፣ «በስሜ»)፣ (ዮሐ 14÷13-16፤ 15÷16፤ 16÷23-26፤ 1ዮሐ 5÷14-15)፣ በእርሱ በመኖር (ዮሐ 15÷7)
4. ከሌሎች አማኞች ጋር በመተባበርና ጥምረት በመፍጠር (ማቴ 18÷19)
5. በራስ ወዳድነት ላይ ባልተመሠረተ መነሳሳት (ያዕ 4÷23) መጠየቅ ይኖርብናል:

**የምንጸልየውም:-**

1. እግዚአብሔር ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ (ማቴ 9÷38)
2. ለመንፈስ ቅዱስ (ሉቃ 11÷13)
3. ፍሬ ለማፍራት አስፈላጊ ለሆነው ነገር (ዮሐ 15÷16)
4. ለጥበብ (ያዕ 1÷5) ሊሆን ይገባል::

ለአንድ የከረመ ነገር ዝም ብለን መጠየቅ እንደምንችል የማናምን ብንሆንም የጸሎትን ኃይል መካድ የለብንም:: ኤፌሶን 3÷20 «እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው ...» ይላል:: ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች በጣም እውን የሆነው አደጋ የቅንጦት ጥያቄ ሳይሆን ጭራሹኑ አለመጠየቃቸው ነው::



ሉቃ 21÷37-38

[37]ኢየሱስም ቀን ቀን በቤተ መቅደስ
እያስተማረ፣ ሌሊት ግን ደብረ ዘይት ወደ ተባለ ተራራ
ወጥቶ ያድር ነበር:: [38]ሕዝቡም ሁሉ ሊሰሙት ማልደው
ወደ ቤተ መቅደስ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር::»

የሉቃስ አቀራረብ ባለፈው ሳምንት በየምሽቱ ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ያድር እንደ ነበር ያስመስለዋል:: በፓለስታይን የነበረው ሞቃት የአየር ጠባይ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ቢሆንም ከዚያ ይልቅ የደብረ ዘይትን ተራራ ቁልቁል በመወረድ በማርያም በማርታና በአልዓዛር መስተንግዶ ሊያገኝ ወደሚችልበት ወደ ቢታንያ ሳይመለስ አይቀርም:: በየዕለቱ በማለዳ ለማስተማር ወደ ቤተ መቅደሱ ደጃፍ ይመለስ ነበር:: እዚያም በደረሰ ጊዜ ቀጥሎ ምን እንደሚናገር ለመስማት በመጓጓት ዙሪያውን ይከቡታል::

**§ 132ሀ**
**የኢየሱስ ሥልጣን በካህናት ሸንጐ ተጠየቀ**
**ማቴ 21÷23-27**
**ማር 11÷27-33**
**ሉቃ 20÷1-8**

ያለፉት ሁለት ቀናት ኢየሱስ በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ተወዳጅነት ለመገምገም መልካም ነበሩ:: በድል አድራጊነት የገባበት እሁድ ዕለትና ቤተ መቅደሱን ያጸዳበት ሰኞ ዕለት ብዙ ትኩረትን ስበዋል:: በቤተ መቀደስ ይህ ወቅት ማክሰኞ ማለዳ ነው:: ሕዝቡ ቀደም ብለው ኢየሱስን ከበውታል:: የአይሁድ መሪዎች አንድ ነገር ማድረግ አለባቸው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ተቀባይነት እንዲያጣና እነርሱም ተከታዮቻቸውን ወደ ራሳቸው ለመመለስ ያደርጉ የነበሩትን ጥረት እንመለከታለን::

(ማር11)[27]እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ
ውስጥ በሚዘዋወርበት ጊዜ፣ (ሲያስተምርና ወንጌልን ሲሰብክ[ሉቃ]) የካህናት ስለቆች፣
ጸሐፍትና የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀርበው፣ [28]እነዚህን ነገሮች የምታደርገው

በምን ሥልጣን ነው? (ንገረን) እነዚህን እንድታደርግስ ይህን ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው» አሉት፡፡

29ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «እስቲ እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ መልሱልኝ፤ እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ፡፡ 30የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? መልሱልኝ፡፡»

ከሕንፃው ቋሚዎች ትይዩ በኢየሱስ ፊት ለፊት የካህናት ሸንጎ መሰብሰቢያ ነበር፡፡ በጥያቄዎችና በሙግቶች የተሞላ አንድ ሙሉ ቀን እንደሚሆን ከወዲሁ መገመት ትችላላችሁ፡፡ እንዲያውም ከሌሎቹ ቀናት ይልቅ በኢየሱስ የሕይወት ዘመን በዚህ ቀን ስለ ተፈጸመው ብዙ ዝርዝር መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ማቴዎስ ከጻፈው ወንጌል ወደ አንድ ስድስተኛ የሚሆነውን ለዚሁ ጉዳይ አውሎታል፡፡

ከሦስቱም የካህናት ሸንጎ ቅርንጫፎች የተውጣጡ ወኪሎች ሊቀ ካህናት (ሰዱቃውያን)፣ የሕግ መምህራን (ፈሪሳውያን) እንዲሁም ሽማግሌዎች («ያልተካኑ» መሪዎች) ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ገራገርና ተገቢ የሚመስል ጥያቄ ይዘው ነበር የቀረቡት: «እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው?»፡፡ ለነገሩ ቀደም ባለው ቀን ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አንጽቷል፡፡ በሌላ አነጋገር በካህናት ሸንጎ ሥልጣን ሥር የነበረውንና ቤተ መቅደሱ ያለበትን ተራራ ተዳፍሯል፡፡ ከእነርሱ ተግባር አንደኛው ክፍል በፋሲካ ወቅት በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚካሄዱትን ነገሮች መቈጣጠር ነበር፡፡ በተለይም ሮማውያን ከአንቶንዮስ ማማ ላይ ሆነው ወደ ታች በመመልከት ሊፈነዳ ያለ የአይሁድ ሁከት ካለ እሩምታ በመላክ ጸጥ ለማድረግ በጉጉት ይጠብቁ ስለነበረ ይህ ሁኔታ እውነት ነበር፡፡ ስለሆነም የአይሁድን ሃይማኖትም ሆነ የሕዝባቸውን ማኅበራዊ ሰላም ማስጠበቅ የእነርሱ ተግባር ነበር፡፡

ጥያቄአቸው ምክንያታዊና ተገቢ እንዲመስል ሆነ ተብሎ የቀረበ ነው፡፡ ኢየሱስ ግን የተነሳሱበትን ዓላማ ተመለከተ፡፡ በንግግሩ



ሊያጠምዱት፣ እግዘአብሔርን ተሳድቧል ብለው ሊከሱት እንዲሁም ሕዝቡ ለእርሱ ያለውን (በጐ) አመለካከት ለማስለወጥ ዕድል ለማግኘት ገና ይጠባበቁ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ኢየሱስ በአግባቡ ጥያቄአቸውን በጥያቄ መለሰ፡፡ ይህ አደራረጉ ለእኛ ኢየሱስ ጥያቄአቸውን ሊያድበሰብስ የሞከረ ሊመስለን ይችላል፡፡ ነገር ግን መምህራን (ረቢዎች) በሚሟገቱበት ጊዜ ጥያቄን በጥያቄ መመለስ የተለመደ ነበር፡፡ እነርሱ ይሄን ከጥያቄው እንደ መሸሽ ሳይሆን አቅጣጫ እንደማሳየት ነበር የወሰዱት፡፡ ሁኔታው የታየው ኢየሱስ ጥያቄአቸውን እንደሚመልስላቸው ሆኖም መጀመሪያ ውይይቱን በሌላ አቅጣጫ ሊመራው እንደ ፈለገ ነው የሚታየው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለኢየሱስ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ ለራሳቸው ጥያቄ መልስ ይሆናል፡፡ ለኢየሱስ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ራሳቸው ይፈልጉት የነበረውን መልስ ያገኛሉ፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ የኢየሱስ መንገድ ጠራጊ በመሆኑና መልእክቶቻቸውና ዓላማዎቻቸው አንድ በመሆኑ ሥልጣኖቻቸውም አንድ ይሆናል (ዮሐ 1፥19፡26-27፤ 3፥25-30፤ ማቴ 11፥7-10)፡፡ ስለሆነም ኢየሱስ ይህን አንጻራዊ ጥያቄ ጠየቀ፡፡ የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? በሌላ አነጋገር የዮሐንስ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘ ነው ወይስ ያደርግ የነበረው 'የራሱን ነገር' ነበር? ኢየሱስ በዮሐንስ ጥምቀት ላይ ያተኮረው መላ አገልግሎቱ በትክክል የኢየሱስን አገልግሎት ስለሚገልጽና የአይሁድ መሪዎችም የእሱን (የኢየሱስን) ትምህርት ለመከተል አሻፈረኝ ያሉት በዚህ ነጥብ ስለሆነ ነው (ሉቃ 7፥30)፡፡

ማቴ 21፥25-27
ሉቃ 20፥6
ማር 11፥32

እነርሱም እርስ በርስ በመነጋገር እንዲህ ተባባሉ፤ 'ከሰማይ ነው' ካልን 'ታዲያ ለምን አላመናችሁበትም?' ይለናል፤ 26'ከሰዎች ነው' ካልን

ደግሞ፣ 'ሕዝቡ ዮሐንስን (እውነተኛ[ማር]) ነቢይ ነው' ብሎ ስለሚያምን (በድንጋይ ይወግረናል[ሉቃ]) እንፈራለን» ::

[27]ስለዚህ «አናውቅም» ብለው ለኢየሱስ መለሱለት::

እርሱም፣ «እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም» አላቸው::

በድንገት አዳኞቹ ታዳኞች ሆኑ:: ምንም ይበሉ ምን የሚናገሩት ነገር በራሳቸው ላይ ምስክር ይሆንባቸዋል:: «የዮሐንስ ሥልጣን ከሰማይ ነው» ቢሉ ኢየሱስም ሥልጣኑን ያገኘው ከዚያው ነው:: ከዚያም የባሰው ነገር ደግሞ ዮሐንስንም ለመከተል እምቢ ብለዋል:: ስለሆነም ይሄ መልስ ገሃድ የወጣ ግብዝነታቸውን የሚያጋልጥ ይሆናል:: በሌላ በኩል «ዮሐንስ ሥልጣን ከሰው ነው» ቢሉ እዚያው በነበሩበት ስፍራ በድንጋይ ይወገሩ ይሆናል:: ይሄ ለመሳሰም የመጣ ሕዝብ[19] የምር በዮሐንስ ያምናል:: በሄሮድስ በመገደሉ እስካሁንም እልሁ ያንቀጠቅጣቸዋል:: ከዚህም በላይ ልክ ከሁለት ቀን በፊት ዮሐንስን የሚተካውን ኢየሱስን በድል አድራጊነት ሲገባ ንጉሥ ነህ ብለው አወድሰውታል:: እነዚህ የካህናት ሸንጐ ተወካዮች ዮሐንስን (ኢየሱስንም) ከተቃወሙ ይህን ግራ የተጋባ ሕዝብ በራሳቸው ላይ ማነሳሳት ሊሆንባቸው ይችላል::

ስለሆነም ራሳቸውን አገለሉ:: «እኛ አናውቅም» አሉ:: ኢየሱስም በእነርሱ አንጻር መለሰ:: ሆኖም ልብ በሉ እሱ «አላውቅም» አላለም ነገር ግን «እኔም አልነግራችሁም» ነበር ያላቸው:: ሳያውቁ ቀርተው እንዳልሆነ ኢየሱስ ያውቃል:: እውነቱን ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም:: ቀደም ብለው ያልተቀበሉትን እውነት ባሁኑ ጊዜ

---

[19] በቍጥር 1 ላይ ሉቃስ ይህንን የሰዎች ስብስብ «ሕዝብ» [በግሪክኛ «ላኦስ» 205] በማለት ይገልጸዋል:: ሌፌልድ (በገጽ 1013) በሉቃስ ወንጌል ይህ ቃል ምንጊዜም የኢየሱስን ትምህርት የሚቀበለውን ስብስብ የሚወክል እንደሆነ ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር ደጋፊዎቹ ነበሩ ማለት ነው::



የሚቀበሉት አይመስልም:: ስለሆነም ኢየሱስ በከንቱ መናገር አልፈለገም:: የሚፈልጉት መልስ ሳይሆን አመቺ ዕድል ነበር:: ጌታ ግን (ይህን ምቹ ዕድል) ሊሰጣቸው ፈቃደኛ አልነበረም::

**§ 132ለ**
**ኢየሱስን ስለ መቀበል/ መቃወም የተነገሩ ሦስት ምሳሌዎች**
**(ማቴ 21÷28-22÷14፤ ማር 12÷1-12 ሉቃ 20÷9-19**

የአይሁድ መሪዎች የዮሐንስን ሥልጣን (ከ §132ሀ ጋር ያነ) አስመልክቶ ኢየሱስ ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኞች አልነበሩም:: ኢየሱስ ለዝምታቸው ሦስት አግባብ ያላቸው ምሳሌዎችን በመናገር መልስ ሰጣቸው:: ማቴዎስ ብቻ ሦስቱንም ምሳሌዎች ያካተተ ሲሆን፣ ማርቆስና ሉቃስ የወይኑን እርሻ ምሳሌ ብቻ አቅርበዋል::[20] ያም ሆነ ይህ እንጂ የተደረጉት ሦስቱም ምሳሌዎች በኢየሱስ በኩል የተገለጸውን የእግዚአብሔር ሥልጣን አይሁድ እንዴት እንደተቃወሙ ለማሳየት የታቀዱ ነበሩ::

በእያንዳንዱ ምሳሌ ተቃውሞውና የሚከለተው ቅጣት ይበልጥ እየከረረ ይሄዳል:: በመጀመሪያው ምሳሌ ኢየሱስን የሚቃወሙት አባቱ የነገረውን ባላደረገው ዓመፀኛ ልጅ ተመስለዋል:: በሁለተኛው ምሳሌ

---

[20] ይህ ምሳሌ አጠር ባለ መልኩ በቶማስ ወንጌልም ውስጥ ይገኛል:: አንዳንዶች ይሄኛው በጣም «ጥንታዊ» የሆነው አቀራረብ እንደ ሆነ ይናገራሉ (ከJ.D. Crossan, "The Parable of the Wicked Husbandmen," *JBL* 90 [1971]: 451-465; እንዲሁም J.A.T. Robinson, "The Parable of the Wicked Husbandmen: A Test of Synoptic Relationships," *NTS* 21 [1974-75]: 443-461 ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ የአርትኦት ለውጦች ቀደም ብለው የተላለፉ የአፈ ታሪክ ቅርሶች ከሚባሉ ይልቅ ኖስቲክ ኑፋቄዎች ተብለው ቢገለጹ የተሻለ ነው (ከ W.R. Schoedel, "Parables in the Gospel of Thomas: Oral Tradition or Gnostic Exegesis," *CTM* 43 [1972]: 548-560; በተጨማሪ K.R. Snodgrass, "The Parable of the Wicked Husbandmen: Is the Gospel of Thomas Version the Original?" *NTS* 20 [1974-75]: 142-144 ጋር ያነ)::

ተቃዋሚዎቹ ልጅዬውን በመግደላቸው ተገቢ ብድራታቸውን በሚቀበሉት ክፉ ባሪያዎች ተመስለዋል። በሦስተኛው ምሳሌ የንጉሡን ግብዣ ባለመቀበላቸው በመሲሐዊው ግብዣ ላይ እንዳይሳተፉ በሚከለከሉት ተመስለዋል።

**የሁለቱ ልጆች ምሳሌ:-**

ማቴ 21÷28-32

28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ምን
ይመስላችኋል? ሁለት ወንዶች ያሉት አንድ ሰው ነበረ፤
ወደ መጀመሪያው ልጁ ሄዶ፣ 'ልጄ ሆይ& ዛሬ ወደ
ወይኑ ቦታ ሄደህ ሥራ፣' አለው። 29«ልጁም፣
'አልሄድም' አለው፤ ኋላ ግን ተጸጸቶ ሄደ።
30«ወደ ሁለተኛው ልጁ ሄዶ እንደዚያው አለው፤ ልጁም 'እሺ እሄዳለሁ'
አለው፤ ነገር ግን ሳይሄድ ቀረ።
31«ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው የትኛው ነው?»
እነርሱም፣ «የመጀመሪያው ልጅ» አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እውነት
እላችኋለሁ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሟችኋል፤
32መጥምቁ ዮሐንስ የጽድቅን መንገድ ሊያሳያችሁ ወደ
እናንተ መጣ፤ እናንተ አላመናችሁትም፤ ቀረጥ
ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች ግን አመኑት። የሆነውን
ካያችሁ በኋላ እንኳ ንስሐ ገብታችሁ አላመናችሁትም።

ይህ ቀላል ምሳሌ ነው። ኢየሱስ:- «እግዚአብሔርን የሚያከብሩት ትክክለኛውን ነገር የሚናገሩት ሳይሆኑ ትክክለኛውን አኗኗር የሚኖሩት ናቸው» ነበር ያለው። ይህ ለእኛ ግልጽ ቢሆንም እንኳ ለእነርሱ አልነበረም። አስተውሉ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ባህል



አንድ ልጅ ለአባቱ መልስ መስጠት ነውር ነው። ምናልባትም ካለመታዘዝም የባሰ ነውር ነው። ስለሆነም የኢየሱስ ምሳሌ የሚያቀርበው ምርጫ በጥሩና በመጥፎ መካከል ሳይሆን በሁለት ክፉ ነገሮች መካከል ነው።[21]

ኢየሱስ ከምሳሌዎቹ አንደኛውን በግልጽ ከአይሁድ መሪዎች ጋር አዛምዶ (ካርሰን ገጽ 449) ሲናገር ይህ የመጀመሪያው ነው። በአባባሉ ግራ ተጋብተዋል። ቀራጮችና ጋለሞታዎች ከሃይማኖት ሰዎች ቀድመው ለምን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት[22] ይገባሉ? እንደ ታሪኩ ከሆነ እግዚአብሔር አድርጉ ያላቸውን በማድረግ ንስሐ ስለገቡ ነው። ፈሪሳውያን ለእግዚአብሔር እየሠሩ አለመሆናቸውን ኢየሱስ በመጠቆሙ ይደነግጣሉ። ሕይወታቸው ለእሱ ማለትም ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው ወይም እነርሱ እንደዚህ እንደሆነ ያስባሉ።

እግዚአብሔር የሚጠይቀው *ሥራ* ያን ያህል 'ቤተ ክርስቲያን ነክ ጉዳይ' ሳይሆን በክርስቶስ መታመንን ነው። በኢየሱስ አገላለጽ:- «እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣ ይህ የእግዚአብሔር *ሥራ* ነው» (ዮሐ 6÷29)። በመጀመሪያ በአስከፊ አኗኗራቸው ቀራጮና ጋለሞታዎች የእግዚአብሔርን ዕድቅ ተቃወሙ። ነገር ግን ዮሐንስን ባዳመጡ ጊዜ ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው ተጠመቁ፤ ከዚያም ኢየሱስን ተከተሉት። ይሁን እንጂ መሪዎቻቸው ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ይናገራሉ ግን ለፈቃዱ ታዛገኞች አይደሉም። ምክንያቱም ዮሐንስ የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ ሲመጣ ያንን ለመቀበል አሻፈረኝ ብለዋል

[21] W. Langley, "The Parable of the Two Sons (Mt 21:28-32) against Its Semitic and Rabbinic Backdrop," *CBQ* 58/2 (1996): 228-243.

[22] Proago (ፕራአጎ) የሚለው ቃል እንደዚሁ «ቀደም ብሎ መግባትን» ብቻ ሳይሆን «ተቀዳሚ መሆንን» ሊያመለክት ይችላል። ስለሆነም የቃሉ አንድምታ ኃጢአተኞች በፈሪሳውያን «ምትክ» ይገባሉ እንደሚል ተደርጐ እስከ መወሰድ ይደርሳል።

(ሉቃ 7÷30):: አሁን ደግሞ ኢየሱስ ፊት ለፊታቸው ሲቆም ሊገድሉት የሚችሉበትን መንገድ ለማሰላሰል ይሞክራሉ::

## የወይን እርሻው ምሳሌ

ማቴ 21÷33-39
ከሉቃ 20÷9-16፣
ማር 12÷2-5 ጋር

[33]ሌላም ምሳሌ ስሙ፤ አንድ የወይን እርሻ ባለቤት ነበር፤ በእርሻው ዙሪያ አጥር አጠረ፤ ለወይኑ መጭመቂያ ጉድጓድ ቈፈረ፤ ለጥበቃ የሚሆን ማማ ሠራ፤ ከዚያም እርሻውን ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ:: [34]የመከር ወራት ሲደርስ (ከወይኑ[ማር]) ፍሬውን ለመቀበል አገልጋዮችን ወደ ገበሬዎቹ ላካቸው::

[35]«ገበሬዎቹም አገልጋዮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት (ባዶ እጁንም ሰደዱት[ማርሉቃ])፤ ሌላውን ገደሉት፤ ሌላውን ደግሞ በድንጋይ ወገሩት:: [36]እርሱም ከፊተኞቹ የሚበልጡ አገልጋችን ላከ፤ ገበሬዎቹም ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸሙባቸው:: (ከሌሎች ከብዙዎቹ መካከል አንዳንዶቹን ደበደቡ፤ አንዳንዶቹንም ገደሉ[ማር]) [37](የወይኑ አትክልት ባለቤትም፣ 'እንግዲህ ምን ላድርግ'?) በመጨረሻም(የሚወደው[ማር]) 'ልጁን ያከብሩታል' በማለት ልጁን ላከ:: [38]ነገር ግን ገበሬዎቹ ልጁን ባዩት ጊዜ፣ 'ይህማ ወራሹ ነው፤ ኑ እንግደለውና ርስቱን እንውረስ' ተባባሉ:: [39]ይዘውም ከወይኑ እርሻ ውጭ አውጥተው ገደሉት:: (ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ 'እንዲህ ያለውን አያምጣው' አሉ[ሉቃ])::

የወይን እርሻን መንከባከብ በኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ዘመን ይካሄዱ ከነበሩት የእርሻ ሥራዎች መካከል አንደኛው ነበር:: ብዙውን ጊዜ አንድ የመሬት ባቤት የእርሻውን ቦታ ካዘጋጀ በኋላ ለጭሰኞች በኮንትራት ይሰጣቸዋል:: ጭሰኞቹ የወይኑን እርሻ አልምተው ከተገኘ ው ምርት ወይም ፍሬ የተወሰነ መቶኛ (የተለመደው ከ25-30% ነው) ለባለቤቱ ይሰጣሉ:: ከዚህም ባሻገር የወይን እርሻ በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ተምሳሌት በመሆን ተዘውትሮ የሚጠቀስ ነው (ኢሳ 5÷1-7፤ መዝ 80÷6-16፤ በተጨማሪም ኤር 2÷21፤ 6÷9፤ 8÷13፤ 12÷10፤



ሕዝ 15÷1-8፤ 19÷10-14፤ ሆሴ 10÷1):: ኢየሱስ የወይኑ እርሻ ሕዝባቸውን እንደሚወክል አድርጎ እንደ ተናገረ እነዚህ ፈሪውያን በንቃት እንዳስተዋሉ ምንም ጥርጥር የለውም::

ኢየሱስ በሚከተለው ሁኔታ በደንብ የተዘጋጀን የወይን ቦታ ይገልጻል:- (1) ከእንስሳትና ከሌቦች እህሉን የሚከልል ቅጥር፤ (2) የወይን ፍሬው ባለበት ቦታ ወይን ይሆን ዘንድ የሚጨመቅበት የወይን መጭመቂያ፤ (3) ሠራተኛው የእሳት አደጋን ወይም ዘራፊዎችን የሚጠብቅበት ማማ::

የወይኑ ዕርሻ ከተዘጋጀና ከሠራተኞቹም ጋር ውል ከተደረገ በኋላ ባለቤቱ ሰፋ ያለ የዕረፍት ጊዜ ለመውሰድ ይችል ነበር:: መኸር ሲደርስ የእርሱን ድርሻ እህል ይወስዱ ዘንድ አገልጋዮቹን ላከ:: ብሉምበርግ የተባለ ጸሐፊ ከዚህ ላይ የኢየሱስ ቋንቋ የዮሐንስን ይመስላል ይላል:- «ለንስሐ የሚገባ ፍሬ (ማቴ 3÷8፤ ከ3÷10፤ 7÷16-20፤ 12÷33፤ 13÷8:24-26፤ 21÷19):: ይህ ኢርቱዕ በሆነ መልኩ መዝሙር 1÷3ን ሊመለከት ይችላል::

የተከራይ ገበሬዎች ጠባይ አሳፋሪ ነው! ያለባቸውን ዕዳ በመክፈል ፈንታ ሰብሳቢዎቹን ደበደቡ (ቃሉ ቆዳን መግፈፍ ወይም አካልን መግረፍ ማለት ሊሆን ይችላል)፤ ገደሏቸውም:: ይህ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ የተደረገ ስለ ሆነ ባለቤቱ ትዕግሥቱ ተሟጦ አልቋል:: ምን ሊያደርግ ይችላል? የራሱን ልጅ ለመላክ ወሰነ![23] እርግጥ ነው እርሱ በተገኘበት ንስሐ ገብተው ግዴታቸውን ይፈጽማሉ::

---

[23] «የምወደውን» [*አጋፔቶስ - agapetos*] ሉቃ (20÷13) የሚለው ቃል በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ውስጥ አንዳንድ ጊዜ «አንድያ» («ብቸኛ») [*መኖጀኔስ - monogenes*] ከሚለው ቃል ጋር ይገኛል:: ስለዚህ በዚህ ምንባብ ውስጥ ከኢየሱስ የጥምቀት ትረካ ጋር ተያይዞ (ማቴ 3÷17፤ ሉቃ 3÷22) ከዮሐ 3÷16 እና ከውላጤ ራእዩ ተመክሮ ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ልናይ እንችላለን::

ነገር ግን ሲመጣ ሲያዩት ስለ ጉዳዩ እርስ በርሳቸው ተወያዩ:: ባለቤቱ ሞቶ ልጁ ውርሱን ለመሰብሰብ[24] መምጣቱ ይሆናል አሉ:: ስለዚህ ልጁን ከገደሉ የወይኑን ዕርሻ የሚወስድባቸው ማንም አይኖርም:: ንብረቱና ከንብረቱ የተገኘው ፍሬ ሁሉ የእነርሱ ይሆናል:: በዚሁ መሠረት ልጁን ገድለው ወይኑ ዕርሻ ውስጥ ጣሉት::[25] በኢየሱስ ዙሪያ የቆሙት ሰዎች በድንጋጤ ተነፈሱና፤ «ይህ ከቶ አይፈጸም!» አሉ:: ነገር ግን ይፈጸማል የሚፈጸመውም ካሰቡት በላይ ፈጥኖ ነው::

**ማቴ 21፥40-42**

40«ታዲያ የወይኑ ዕርሻ ባለቤት ሲመጣ እነዚያን ገበሬዎች ምን የሚያደርጋቸው ይመስላችኋል?»

41እርሱም፣ «እነዚያን ክፉዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሎ ከወይኑ እርሻ ተገቢውን ፍሬ በወቅቱ ለሚያስረክቡት ለሌሎች ገበሬዎች ያከራያል» አሉት::

42ኢየሱስም እንዲህ ተባሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን አላነበባችሁምን? አላቸው፤

«ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
የማእዘን ራስ[ፐ] ሆነ፤
ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው::

[ሀ42] *ወይም የማእዘን ድንጋይ* [ለ42] *መዝ 118፥22-23*

---

[24] *ክሌሮኖሚያ* - *Kleronomia* የሚለው ቃል እንደውም አንዳንድ ጊዜ የንብረት መብት መንጠቅን ለመግለጥ ነው (ሰብዓ ሊቃናት ትርጉም 3ነገ 20፥15-15 (የእኛው 1ነገ 21፥15-16)፤ Josephus *Ant.* 8:359-360; *Wars* 2:249. K. Snodgrass, "Recent Research on the Parable of the Wicked Tenants: An Assessment," *BBR* 8 (1998): 187-216.

[25] ማቴዎስና ሉቃስ ልጁ በመጀመሪያ ከወይኑ ዕርሻ ውጭ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ መገደሉን ጽፈዋል (ማቴ 21፥39፤ ሉቃ 20፥15)፤ ማርቆስ ግን በወይኑ ዕርሻ ውስጥ መገደሉን ነው የገለጠው (ማር 12፥8):: አንድ ሰው የዕርሻንም ቦታ የእስራኤል ተምሳሌት ከማድረግ ይልቅ የኢየሩሳሌም ተምሳሌታዊ መገለጫ ነው ካላለ በቀር በትርጉም ረገድ ልዩነት የለም:: በዚህ መሠረት ኢየሱስ በመጀመሪያ ከከተማዋ እንዲወጣ ተደረገ፤ ከዚያም ተገደለ:: ይሁን እንጂ ይህ ዐይነቱ ትርጓሜ ማርቆስ ካሰባው በላይ በጽሑፉ ላይ የሌለ ትርጉም ማንበብ ነው::



ማንኛውም የመሬት ባለቤት እንዲህ ያለውን ጠባይ ሊታገሥ አይችልም:: ኢየሱስ፣ «ታዲያ ... እነዚያን ገበሬዎች ምን የሚያደርጋቸው ይመስላችኋል?» ባለ ጊዜ መልሱ የታወቀ ነው:: ያጠፋቸዋል፤ የወይኑን ዕርሻ ባለቤት በሚያከብሩና ዕዳቸውንም በሚከፍሉ ገበሬዎች ይተካቸዋል::

ቀደም ያለውን ምሳሌ ትርጓሜ እንዳወቁ ሁሉ፣ የዚህምንም ትርጓሜ ያውቃሉ፤ ትግበራው ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አልተሳካላቸውም:: ክፉ ዐራሾች እነርሱ ናቸው:: እነርሱ የደበደቧቸውንና የገደሏቸውን ነቢያት እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ወደ እነርሱ ልኳቸዋል (ኤር 20፥1-2፤ 26፥20-23፤ 1ነገ 18፥4:13፤ 2ዜና 24፥20-21፤ ማቴ 23፥34፤ ዕብ 11፥37):: አሁን ደግሞ እግዚአብሔር የራሱን ልጅ ልኮላቸዋል::[26] ነገር ግን የራሳቸውን ሹመትና ክብር ለመጠበቅ ሲሉ እርሱን ለመግደል በማሤር ላይ ናቸው (ከዮሐ 11፥45-54፤ ከክፍል 119 ጋር ያነ):: መዝሙር 118፥22ን ለመፈጸም ተቃርበዋል:: ኢየሱስን በመግደል ሳይቀበሉት ይቀራሉ:: በዚህ ክንዋኔ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የማእዘን ድንጋይ ይሆናል::

ኢየሱስ «አላነበባችሁምን?» (ማቴ 12፥3፤ 19፥4፤ 21፥16፤ ማር 12፥10) በሚለው የወቀሳ ቃል መዝሙር 118፥22ን አስተዋወቀ:: ሰዎች ብዙ ትኩረት ያላደረጉበት እውቅ መሲሐዊ መዝሙር ነበር:: ለምን እንደ ሆነ ማስተዋል ትችላላችሁ:: የተናቀ የማእዘን ድንጋይ ውብ ሐሳብ ነው:: ይህ «የማእዘን ድንጋይ» ለሦስት ልዩ ልዩ ግንባታ ሊያገለግል ይችላል:: *የማእዘን* ድንጋይ ሊሆን ይችላል:: ይህም አንድ ሕንፃ መሠረቱ ሲጣል የመጀመሪያውና በጣም አስፈላጊ የሆነ ድንጋይ

---

[26] ኢየሱስ በይፋ «የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ» ሲል ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ሊሆን ይችላል:: ቀያፋ ይህን ያስታውሰዋል፤ አስታውሶም ከሦስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ሲከሰስ፣ ወንጀል አድርጎ ያቀርበዋል::

ነው:: ያ በትክክል ከተጣለ ሙሉው ሕንጻ ትክክል ይሆናል:: ሁለተኛ የማእዘን ራስ የሕንፃው ራስ ነበር፤ ምሰሶዎችንም በቦታቸው አጣምሮ ይይዛል:: ሦስተኛ ቊልፍ የሆነው ድንጋይ በቅስቱ መካከል ላይ የሚቀመጥ የመጨረሻ ድንጋይ ነበር:: ድንጋዩ በቦታው እንደ ተቀመጠ መረባርቦቹ ሁሉ ይወገዳሉ:: እንግዲህ የማእዘን ድንጋይ ሐሳብ ከቊጥር 44 መጀመሪያ ክፍል ጋር በደንብ ይገጣጠማል፤ በዚህ ድንጋይ ላይ መውደቅ ሀልውናህን ይወስነዋል:: የማእዘን ራስ ወይም ቊልፍ የሆነው ድንጋይ ከቊጥር 44 ሁለተኛ ክፍል ጋር በደንብ ይገጣጠማል:: ይህ ድንጋይ ቢወድቅብህ ያደቅሃል:: ኢየሱስ መንታ እሳቤ ያለውን ዘይቤ ኢየሱስ በዚህ ሳያቅድ አልቀረም::

ይህ ዘይቤ የመጣው ከመዝሙር 118÷22 ሲሆን፣ ከመነሻው የሚያመለክተው የአይሁድን ሕዝብ ነበር:: ሌሎች ሕዝቦች ቢያስቃዩዋቸውም እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ውድ ሕዝቦች ነበሩ:: እዚህ ላይ ኢየሱስ የሕዝቡ ተወካይ ወይም መላ ሕዝቡን በአካልነት የምወክል ነኝ ይላል::[27] በሕዝብነት በእስራኤል ላይ የደረሰው ሁሉ በግለሰብነቱና በመሲሕነቱ በኢየሱስ ላይም ደርሶአል:: የመዝሙረ ዳዊት ክፍል መሲሓዊ ነው ማለታችን በእርግጥ ትክክል ነው:: የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ማድረጓ እርግጥ ነው (ሐሥ 1÷11፤ ሮሜ 9÷33፤ 1ጴጥ 2÷7):: መዝሙር 118÷22ን በከበቡ ቊጥሮች «የድነት ንግግር»ን እናነባለን (ከ21:25 ጋር ያነ):: ቊጥር 26 ውስጥ «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው»[28] በሚለው ቃል ወደ ኢየሱስ በድል መግባት ፊታችንን እናዞራለን::


[27] F.F. Bruce, "New Wine in Old Wine Skins: III. The Corner Stone," *ExPT* 84 (1972-73): 231-235.

[28] Blomberg (p. 325) እንደሚያሳስበው እስከ ሕፃንነት ትረካ ድረስ ማቴዎስ አያሌ ጥቅሶችን አንድ ምዕራፍ ውስጥ አላቀረበም (ምዕ 1-2)፤ በቀረው የወንጌሉ ክፍል ግን ከዳር እስከ ዳር ተሠራጭተው ይገኛሉ::



መዝሙር 118÷22 ውስጥ ስለ አለው ቃል አንድ የመጨረሻ ማስታወሻ ይህን ተከትለው 23-24 ውስጥ የመጡት ቃሎች ቀጥሎ ያሉት ያቸው፤ «እግዚአብሔር ይህን አደረገ፤ ለዐይችንም ድንቅ ናት:: እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤ በእርሷ ሐሤት እናድርግ፤ ደስም ይበለን::» የኢየሱስ ሞት የእግዚአብሔርን ድርጊት ዘግናኝ ኢፍትሐዊነት ቢያስመስለውም እንኳ፣ የድነታችንም ምንጭ ነው:: አስከፊ ቢሆንም እንንከባከበዋለን:: እርግጥ ውበቱ በደም የተሸፈነ ነው::

**ማቴ 21÷43-46**
**ከማር 12÷12 ጋር**



43«ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን ለሚያፈራ ሕዝብ
ትሰጣለች፤ 44በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይሰባበራል፤
ድንጋዩ የሚወድቅበት ሰው ግን ይደቅቃል::»[ሀ]
45የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምሳሌዎቹን
በሰሙ ጊዜ፣ ስለ እነርሱ የሚናገር መሆኑን ዐወቁ::
46ነገር ግን ይዘው ሊያስሩት ቢፈልጉም ሕዝቡ ኢየሱስን እንደ ነቢይ አድርጎ ይመለከት
ስለ ነበር ፈሩ:: (ነገር ግን ... ትተውት ሄዱ::[ማር])

*[ሀ]44 አንዳንድ ቅጆች ቁር 44 የላቸውም::*

የእግዚአብሔር የዕርሻ ቦታ ከእነዚህ ክፉ ዐራሾች ተወስዶ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ክብር ለሚሰጡ ሰዎች ይሰጣል:: ሲጀመር እነዚህ ዐራሾች ቀራጮችና አመንዝራዎች ሆነው እናገኛቸዋለን:: ውሎ አድሮ ግን አሕዛብን ሳይቀር ያካትታሉ::[29] ኢየሱስን ለሚቀበሉት

[29] A.A. Milavec, "Mark's Parable of the Wicked Husbandmen as Reaffirming God's Predilection for Israel," *JES* 26/2 (1989): 289-312 በሚለው ላይ እንዲህ ይላል፤ በማር 12÷1-12 እና በኢሳ 5÷1-7 ክፍል መሠረት ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው ስለ ኢየሱስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በቀጣይነት እስራኤልን ስለ መወድዱ ነው:: የእርሱ ትንታኔ ፊር የያዘ ባይሆም እንኳ፣ ይህን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ጸረ አይሁዳዊ (ጸረ ሴማያዊ) አቋም እንዳይኖር ሚላቬክ ያስጠነቅቃል:: የማቴ 21÷43 ቀዳሚ ሐሳብ የአሕዛብ መጨመር ሳይሆን፣ እምነት በኢየሱስ ነው::